አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ-ምረቃ መርሐ ግብር

# የወየታና የቱከራ ግጥሞች ክዋኔና የይዘት ትንተና በደብረታቦር ከተማ

በ

በሪሁን መንግስቱ

2004 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የወየታና የፋከራ ግጥሞች ክዋኔና የይዘት ትንተና በደብረታቦር ከተማ


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርሊናዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድህረ-ምረቃ መርሐ ግብር

ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


በ

በሪሁን መንግስቱ


2004 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ-ምረቃ መርሐ ግብር

# የወየታና የቶክሪ ግጥሞች ክዋኔና የይዘት ትንተና በደብረታቦር ከተማ

በ

በሪሁን መንግስቱ

2004 ዓ.ም

## የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| የአማካሪ ስም | ፊርማ |
| [illegible] | [illegible] |
| የውስጥ ፈታኝ ስም | ፊርማ |
| [illegible] | [illegible] |
| የውጭ ፈታኝ ስም | ፊርማ |
| [illegible] | [illegible] |

# ምስጋና

ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን ሰውተው መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ ሁሉ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው። መረጃ አቀባዮችን በማፈላለግና ሌሎችንም ጠቃሚ መረጃዎችን በመስጠት በመስክ ሥራ ጊዜ ከጎኔ ላልተለዩኝ ጓደኞች ሲሳይ ንብረቱ፣ ውብሸት ደምሴ፣ ፋንታሰም አዱኛው፣ ደስታው ካሣዬ እና አዳነ ጌታነህ ምስጋናዬ እጥፍ ድርብ ነው።

ለደብረታቦር ከተማ ወረዳ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሃላፊዎች፣ ደቡብ ጎንደር አስተዳደር ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ሃላፊዎች በተለይም አቶ መኮንን ክፍሌና፣ ለሰዋ ገበያ፣ ለእጀባርና ለአራዳ እድር ሃላፊዎች ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው።

ትምህርቴን በነፃ እንድማር ስፖንሰር በማድረግና ለምርምር ገንዘብ በመስጠት ለረዳኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ደመወዜን በመፍቀድ እንድማር ላደረጉኝ ለምስራቅ እስቴ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት እና ለ ምስራቅ እስቴ ወረዳ ሚሊሻ ጽ/ቤት ከፍ ያለምስጋና አቀርባለሁ።

መረጃ በመሰብሰብ ቆይታዬ የገንዘብና የሞራል ድጋፍ ያደረጋችሁልኝ አይን አበባ ጫኔ፣ መኳንንት ደምሴ፣ አያሌው ደምሴ፣ ታደሰ ዮሐንስ፣ ምኞቴ ዮሐንስ፣ ህይወቴ መንግስቴና እህትነሽ መንግስቴ ዛሬም ነገም እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ይሁን። ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል ጽሑፌን በመተየብ ለረዳችኝ አማረች አለልኝ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው።

# ማውጫ

ገጽ


ምስጋና ... i

ማውጫ ... ii

አጠቃሎ ... vi

1. መግቢያ ... 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ... 2

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ... 3

1.3 የጥናቱ ዓላማዎች ... 3

1.3.1 አጠቃላይ ዓላማ ... 4

1.3.2 ዝርዝር አላማዎች ... 4

1.4 የምርምር ጥያቄዎች ... 4

1.5 የጥናቱ ወሰን ... 5

1.6 የጥናቱ ጠቀሜታ ... 5

1.7 የአጠናን ዘዴዎች ... 6

1.7.1 የመረጃ አሰባሰብ ሂደት ... 6

1.7.2 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች ... 8

1.7.2.1 ምልከታ ... 9

1.7.2.2 ቃለ መጠይቅ ... 10

1.7.2.3 የቡድን ውይይት ... 11

1.8 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ..................... 12

1.8.1 የገንዘብ እጥረት ..................... 12

1.8.2 የክዋኔው ጊዜ ማጠር ..................... 12

1.8.3 የመረጃ ባለቤቶች ፈቃደኛ አለመሆን ..................... 13

1.8.4 የመብራት መጥፋት ..................... 14

1.9 የመስክ ቆይታ ውጤት ..................... 14

1.9.1 ክዋኔዎች ..................... 14

1.9.2 ከዋኞች ..................... 15

1.9.3 ታዳሚዎች ..................... 15

1.9.4 መረጃው እና መረጃ ሰጭዎች ..................... 16

2. ክለሳ ድርሳን ..................... 17

2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ..................... 17

2.2 የንድፈ ሐሳብ ቅኝት ..................... 22

2.3 ክዋኔ ..................... 24

2.4 ለቅሶ ..................... 27

2.5 ቃል ግጥም ..................... 28

2.6 ሙሾ ..................... 32

2.7 ወዮታ ..................... 34

2.8 ፉከራ ..................... 36

3. ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢያዊ ዳራ ..................... 39

3.1 መልክዓምድራዊ ገጽታ ..................... 39

3.2 የከተማዋ አመሰራረትና ስያሜ ..................... 40

3.3 ኢኮኖሚያዊ ገጽታ ........ 40
3.4 ባህላዊ፣ ማህበራዊ እና የክብረ በዓላት ክዋኔ ........ 40
4. ትንተና ........ 44
4.1 የወዮታ ግጥሞች ይዘት ትንተና ........ 46
4.1.1 ማብላት ማጠጣትን የሚገልፁ ግጥሞች ........ 46
4.1.2 ቁጨትን የሚገልፁ ግጥሞች ........ 49
4.2 የቆከራ ግጥሞች ይዘት ትንተና ........ 52
4.2.1 የጦር ሜዳ ጀግንነትን የሚገልፁ ግጥሞች ........ 52
4.2.1.1 ሂች ያደገበትን፣ ጀብድ የፈፀመበትን ቦታና ማህበረሰብ የሚገልፁ ግጥሞች ........ 53
4.2.1.2 የሂችን ሰብዕና የሚገልፁ ግጥሞች ........ 56
4.2.2. የስራ ጀግንነትን የሚገልፁ ግጥሞች ........ 61
4.2.2.1 የስራ ታታሪነትን የሚገልፁ ግጥሞች ........ 61
4.2.2.2 የስራ ውጤትን የሚገልፁ ግጥሞች ........ 65
4.2.2.3 እንግዳ ተቀባይነትን የሚገልፁ ግጥሞች ........ 68
5. ማጠቃለያ ........ 71

ዋቢ ጽሑፎች

የመረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

አባሪዎች

አባሪ፡ 1 የግጥሞች ስብስብ

አባሪ፡ 2 የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች

አባሪ፡ 3 ፎቶዎች

አባሪ፡ 4 ካርታዎች

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት ሁለት ዓበይት ዓላማዎች አሉት፡፡ አንደኛው በደብረታቦር ከተማ የወየታና የቆከራ ግጥሞች ከዋኔ ምን እንደሚመስል ማሳየት ሲሆን ሁለተኛው የግጥሞቹን ይዘት መተንተን ነው፡፡ ለጥናቱ መረጃ የተሰበሰበው በተሳትፎ ምልከታ፣በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት ነው፡፡ ለጥናቱ አስፈላጊ ናቸው የተባሉ መረጃዎች በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካይነት ተሰብስበዋል፡፡

የሙሾ፣ የወየታና የቆከራ ግጥሞች የመከወኛ አጋጣሚያቸው አንድ ይሁን እንጅ የአከዋወን ሂደታቸውና በታዳሚ ላይ የሚፈጥሩትን ስሜት እንደሚለያይ ጥናቱ አመልክቷል፡፡ የወየታ ግጥሞች በእድሜ፣ በፆታ በማህበራዊ ደረጃ ልዩነት ላይ ተመስርተው የሚገጠሙ ሲሆን የቆከራ ግጥሞች ደግሞ ለጀግና ወንዶች የሚገጠሙ መሆናቸው በጥናቱ ታይቷል፡፡ የሙሾ ግጥሞች በቡድን የሚከወኑ በመሆናቸው ግለሰብ ተኮር አይደሉም፡፡ ይልቁንም በአጠቃላይ የሰው ልጅን ከንቱነት በማሳየት በሰው ልጅ ላይ ሞትን ያመጣውን ፈጣሪን የሚያማርሩ ናቸው፡፡ በሙሾ፣ በወየታና በቆከራ ግጥሞች መካከል በአከዋወን ሂደታቸው፣ በከዋኞቹ፣ በሚከወንላቸው ሰዎች ልዩነት መኖሩን ጥናቱ ያሳያል፡፡ የግጥሞቹ አከዋወን ሂደት ይለያይ እንጅ አጠቃላይ ይዘታቸው የማህበረሰቡን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ማንነቱን ማንፀባረቅና መጠበቅ መሆኑን ትናቱ አመላክቷል፡፡ በመሆኑም አጠቃላይ የለቅሶ ቃል ግጥሞችን የሙሾ ግጥሞች ብሉ ጨፍልቆ ከማጥናት ይልቅ እያንዳንዳቸው ተለይተው መጠናት እንዳለባቸው ጥናቱ ፍንጭ ሰጥቷል፡፡

# 1. መግቢያ

ሃዘን ምክንያቱ በርካታ ነው። ሰው ሲታመም፣ ሲቸገር፣ ከወዳጁ ጋር ሲጣላ፣ አይዞህ ባይ ሲያጣ፣ ከወገኑ ሲለይ ያዝናል። ሞት ደግሞ ትልቁ የሃዘን ደረጃ ነው። በማህበረሰቡ አባላት ውስጥም ከፍተኛ የስነ-ልቦና እና የማህበራዊ ቀውስን ይፈጥራል። ይህን የተቃወሰ ስሜት በባህል ማለዘብ፣ መግራት እና ሥርዓት ማስያዝ የተለመደ ነው። አንዱ ማህበረሰብ ከሌላው ማህበረሰብ ከሚለይባቸው አበይት ፎክሉራዊ ክዋኔዎች መካከል አንዱ ሀዘኑን የሚገልፅበት ሥርዓት እና የቃል ግጥም ክዋኔው ነው። በዚህም ቀሪውን ማህበረሰብ ከማፅናናቱም ባሻገር ሟች እንደ እምነቱ ፅናት እስከወዲያኛው ድረስ መልካም ነገር ይገጥመው ዘንድ ይመኛል። በማህበረሰቡ መካከል የማህበራዊ ደረጃ ልዩነትንም ይፈጥራል። ማህበረሰቡ የሃዘን ስሜቱን ከሚገልፅባቸው ቃል ግጥሞች ውስጥ የወየታ፣ የፋከራ እና የሙሾ ግጥሞች ይጠቀሳሉ። የቃል ግጥምን ምንነት አስመልክቶ ፈቃደ አዘዘ (1991፣86) "የቃል ግጥም ማለት አደራረሱ፣ አከዋወኑ፣ ተስተላልፎውና አቀራረቡ ብዙ ጊዜ በመዜም የሆነ በዘፈን፣ በሙሾ፣ በእንጉርጉሮ እና በሌሎች ተመሳሳይ ዜማዊ ቅርፆች ውስጥ የሚገኝ ህዝባዊ ግጥም ነው።" በማለት ገልፀውታል።

ይህ የቃል ግጥም ብያኔ የቃል ግጥምን በደፈናው በቃል ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ ነው ከሚለው አመለካከት ባሻገር ቀረብ ብለን ብዙ ነገሮችን መመልከትና ባህሪያቱንም ማወቅ እንዳለብን የሚያመለክት ነው። የቃል ግጥም አደራረሱ እና አከዋወኑ እንዲሁም ተስተላልፎው በቃልና ብዙ ጊዜ በመዜም መሆኑ ለማጥናት የበለጠ አስቸጋሪ ያደርገዋል። ምክንያቱም ከቋንቋው ባሻገር የዜማን እውቀትም ይጠይቃልና። ከቃል ግጥሙ ዜማ ጋር ውህደት በመፍጠር ልዩ ውበት የሚሰጠው ክዋኔው ነው። ሥነ ቃል ሰበበ ድርሰት ወይም ሰበበ ክዋኔ ያስፈልገዋል። Finnegan (1970፣102-104) የቃል ግጥምን ሰበበ ድርሰት ብዙውን ጊዜ ግብር፣ ክብረ በዓላት፣ ለቅሶ እና ሌሎቹም ማህበራዊ ጉዳዮች እንደሆኑ ይገልፃሉ። በዚህ ጥናት Finnegan ከጠቀሷቸው መካከል የለቅሶ ክፍል በሆኑት በወየታና በፋከራ ግጥሞች አከዋወንና ይዘት ትንተና ላይ ይተኮራል።

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

እንደ ሌሎቹ ባህላዊ ጉዳዮች ሁሉ፣ የሃዘን መግለጫ መንገዶች እና የለቅሶ ክዋኔ ስርዓቶች ከማህበረሰቡ የአኗኗር ፈሊጥ፣ አመለካከትና ፍልስፍና የሚቀዱ ናቸው፡፡ አንድ ማህበረሰብ በሚያከናውነው የለቅሶ ሥነ ሥርዓት አማካይነት ስለህይወት፣ ስለሞት፣ ስለሟች እና በህይ ወት ስላለው ማህበረሰብ አመ ለካከት ምን እንደሆነ መ ረዳት ይቻላል፡፡

በለቅሶው ወቅት የሚቀርቡት የቃል ግጥም ዓይነቶች፣ ክዋኔዎች፣ ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችና እና የተለያዩ አካላዊ እንቅስቃሴዎች (ረገዳ፣ ደረት መደለቅ፣ ፊት መቧጠጥ ወዘተ...) ለለቅሶ ክዋኔ አይነተኛ ማሳያዎች ናቸው፡፡ በተለይም ረገዳ፣ ደረት መደለቅ፣ ፊት መቧጠጥ፣ ፀጉር መላጨትና መውደቅ መነሳት ለሥጋ ዘመድ የሚሰጥን ክብር እንዲሁም በባዕድ እና በሥጋ ዘመድ መካከል ያለን ልዩነት የሚያሳዩ ናቸው፡፡ የሟቹን ሰው ለቅሶ ኢጋጣሚ በመጠቀም የሚከወኑ የወዮታና የቁጭት ግጥሞች ያለው ማህበረሰብ በነባሩ ባህልና አስተሳሰብ ተገርቶ ይኖር ዘንድ ይመክራሉ፣ ያሳስባሉ፣ እስከ ወዲያኛው ድረስም ያፀናሉ፡፡ ይህ ጥናትም ከዚህ አኳያ በስፊው የተቃኘ ሲሆን ክዋኔውና ግጥሞቹ ደግሞ የጥናቱ ዋና ጉዳዮች በመሆናቸው ሰፊ ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡

እያንዳንዱ ማህበረሰብ የራሱ የሆነ የማንነቱ መገለጫ ማህበራዊ ወግና ልማድ አለው፡፡ በመሆኑም የደብረታቦር ከተማ ማህበረሰብ እንደሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች ሁሉ ደስታውን፣ ሀዘኑን፣ ዓውድ አመታዊ ክብረ በዓሉን የሚያከብርበትና የሚያደምቅበት እንዲሁም ማንነቱን የሚያንፀባርቅበትና የሚያጠናክርበት የራሱ የሆነ ሥነ ቃላዊ ክዋኔ አለው፡፡ ከነዚህ ውስጥ ይህ ማህበረሰብ ወዳጅ ዘመዶቹ፣ ቤተሰቦች እና ሌሎች የማህበረሰቡ አባላት በሞት ሲለዩት ሀዘኑን የሚገልፅባቸው የራሱ የሆነ የለቅሶ ስርዓት እና ክዋኔ አለው፡፡ የለቅሶ ስርዓት በማህረሰቡ ውስጥ የነበረ እና አሁንም ያለ ማህበራዊ ልማድ ነው ፡፡

ይህን የለቅሶ ኢጋጣሚ ተንተርሰው የሚከወኑ ስነቃሎች ሲተነተኑ የህብረተሰቡን፣ ሀዘን፣ ምሬት፣ ፍላጐት፣ እምነትና ቁጭት እንዲሁም ሌሎች ድብቅና ጥልቅ ስሜቶችን ያንፀባርቃሉ፡፡

የዚህ ጥናት ትኩረትም በለቅሶ ላይ የሚገጠሙ የወየታና የፋከራ ግጥሞች ክዋኔና ይዘት ትንተና ነው፡፡ የፉከራና የወየታ ግጥሞችም ህልውናቸው ክዋኔያቸው በመሆኑ ትንተናውም ክዋኔያቸውን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ይህ ጥናትም የተከተለው የአፃፃፍ ስልት ገላጭ እና ተንታኝ ሲሆን ክዋኔውን በመግለፅ እና ግጥሞቹን በመተንተን ያተኩራል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በለቅሶ ላይ የሚገጠሙ የወየታና የፋከራ ግጥሞች ክዋኔና የይዘት ትንተና በደብረታቦር ከተማ በሚል ርዕስ ጥናቱን ለማድረግ ያነሳሱኝ ሶስት ምክንያቶች ናቸው፡፡ እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. በደብረታቦር ከተማ ማህበረሰብ ውስጥ በዚህ ርዕስ ጉዳይ የተሰራ ጥናት ባለመገኘቱ፡፡
2. የለቅሶ ቃል ግጥሞችን ጠቅልሎ የሙሾ ግጥሞች ብሎ ማጥናቱ ተገቢ አለመሆኑን ለመጠቆም እና በወየታ፣ ሙሾና ፋከራ ግጥሞች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በማሳየት ማህበረሰቡ የሰጣቸውን ስያሜ ጠብቀው መጠናት እንዳለባቸው ማመኔ፡፡
3. በደብረታቦር ከተማ ማህበረሰብ የለቅሶ ክዋኔው ቆይታ እየቀነሰ መምጣቱና ከሁለት ሰዓት እስከ አራት ሰዓት ብቻ እንዲሆን በመንግስት መወሰኑ ለቃል ግጥሞቹ አለመፈጠርና መጥፋት ምክንያት ስለሚሆን አሁን ላይ ያሉትን ክዋኔዎችና ቃል ግጥሞች ሰብስቦና ተንትኖ ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው ብየ በማሰቤ፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማዎች

ይህ ጥናት በደብረታቦር ከተማ በለቅሶ ላይ የሚገጠሙ የወየታና የፋከራ ግጥሞች ክዋኔ እና የይዘት ትንተና ላይ የተመሰረተ ሲሆን፡፡ የሚከተሉት አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

### 1.3.1 አጠቃላይ ዓላማ

በደብረታቦር ከተማ በለቅሶ ላይ የሚገጠሙ የወየታና የፉከራ ግጥሞችን በመሰብሰብ ክዋኔያቸውና ይዘታቸው ምን እንደሚመስል መተንተን ነው፡፡

### 1.3.2 ዝርዝር አላማዎች

- በሙሾ፣ በወየታና በፉከራ ግጥሞች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ለይቶ ማሳየት፡፡
- የወየታና የፉከራ ግጥሞችን ክዋኔ በመግለፅ እና የግጥሞቹን ይዘት በመተንተን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ፋይዳችውን መጠቆም፡፡
- ማህበረሰቡ በነዚህ ግጥሞች አማካይነት ባህሉን እና ማንነቱን ለመጠበቅ እና ለመቆጣጠር የሚያደረገውን ጥረት ማሳየት፡፡
- ፉከራ የሚፎከርላቸው ሰዎች እነማን እንደሆኑና ከፆታና ከማህበራዊ ደረጃ አንፃር ማሳየት።

## 1.4 የምርምር ጥያቄዎች

ይህ ጥናት የሚከተሉትን የምርምር ጥያቄዎችን ይመልሳል ተብሎ ይታሰባል፡፡

- በደብረታቦር ከተማ የሚገኘው ማህበረሰብ በለቅሶ አጋጣሚ የሚከውናቸው የወየታና የፉከራ ግጥሞች ክዋኔ ምን ይመስላል?
- የወየታና የፉከራ ግጥሞች ይዘቶች ምን ምን ናቸው?
- ግጥሞቹ በማን ይከወናሉየሚሉ?
- ለማን ይከወናሉ?
- የግጥሞቹ መከወን ለማህበረሰቡ ያላቸው ፋይዳ ምንድን ነው? እና
- ምን ምን መልዕክቶች ያስተላልፋሉ? የሚሉ ናቸው፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

በደብረታቦር የተለያዩ አውዶችን መሰረት በማድረግ የሚከወኑ በርካታ ቃል ግጥሞች አሉ፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ትኩረት የተደረገበት ሞትን ተከትሎ በሚመጣው ለቅሶና የለቅሶ መገለጫዎች በሆኑት የለቅሶ ክዋኔ እና ቃል ግጥሞቹ ላይ ነው፡፡ አንድ ሰው ከሞተበት ሰዓት ጀምሮ እስከ ቀብሩ መጠናቀቅና ከቀብርም በኋላ ለቅሶውን ተከትለው የሚመጡ ክዋኔዎች አሉ፡፡ በቅድመ-ቀብር እና ድህረ-ቀብር ሂደት ውስጥ በርካታ የለቅሶ ስርዓቶች ይከናወናሉ፡፡ ምንም እንኳን ሁሉንም የለቅሶ ሥርዓት ማጥናቱ አስፈላጊ ቢሆንም ካለው የገንዘብ፣ የጉልበትና የጊዜ ውስንነት አኳያ በዚህ ጥናት ሁሉንም መመልከት አልተቻለም፡፡ በዚህ የተነሳ ይህ ጥናት በደብረታቦር ከተማ በወርታና በቶክሬ ግጥሞች ክዋኔ ላይ ብቻ በመመስረት የይዘት ትንተና እማድረግ ላይ ተወስኗል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ይሰጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡

1. የቃል ግጥሞች ከዘመን ዘመን የመለወጥና የመቀየር ባህርይ ስለሚታይባቸው ወደፊት የሚመጡ ተመራማሪዎች በዘመናቸው ያለውን ካለፈው ጋር እያነፃፀሩ እንዲያጠኑ እገዛ ያደርጋል፡፡

2. እነዚህን ቃል ግጥሞች የሚከውኑትን ማህበረሰብ ወግ፣ ባህል፣ ልማድ፣ እምነት፣ እንዲሁም አስተሳሰብና አመለካከት ማወቅ ለሚፈልጉ መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶችና መስሪያ ቤቶች፣ ተቋማትና ግለሰቦች አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

3. የክዋኔው ቀይታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያጠረ በመምጣቱ ምክንያት በክዋኔው ላይም ሆነ በቃል ግጥሞቹ ላይ መ ዳከምና መ ለወጥ ስለሚ ኖር ሰብስቦ በቅርስነት ማስቀመጡ አሁን ላይ ያለውን ማንነት ለወደፊት ትውልድ ለማሸጋገር ይጠቅማል፡፡

4. የሚመለከተው አካል ለዚህ የእውቀት ዘርፍ ተገቢውን ትኩረት ይሰጥ ዘንድ ይጠቅማል፡፡

## 1.7 የአጠናን ዘዴዎች

ይህ ክፍል የቀረበው የመረጃ አሰባሰብ ሂደት ምን እንደሚመስል እና አጥኚው የተጠቀመባቸውን ዋናዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተግባራዊነት ያሳያል።

### 1.7.1 የመረጃ አሰባሰብ ሂደት

አንድ የፎክሎር አጥኚ ወደ ሥራው ከመግባቱ በፊት የተሻለ መረጃ ለመሰብሰብ ቅድመ ሁኔዎችን በማስቀመጥ ጊዜን፣ጉልበትንና ገንዘብን ቆጣቢ በሆነ መልኩ መረጃን መሰብሰብ ይጠበቅበታል። እናም ወደ ጥናቱ ከመግባቴ በፊት ቅድመ ሁኔታዎችን በማመቻቸት መረጃዎችን ሰብስቢአለሁ።

ለመስክ ጥናት መረጃን የሚሰበስብ አጥኚ ወደ ዋናው መረጃ ስብሰባ ከመግባቱ በፊት መረጃውን እንዴት ማግኘት እንዳለበት ቅድመ ሁኔታዎችን መንደፍ ይጠበቅበታል። ይህ ደግሞ የተሻለ መረጃን ሊሰጡ የሚችሉ መረጃ አቀባዮችን ከማግኘት ጀምሮ ቦታን ጊዜን እና ሌሉችንም አስፈላጊ ጉዳዮች ለማመቻቸት ይጠቅማል። በዚህም መሰረት ወደ ጥናቱ ከመግባቴ በፊት መረጃ ሊሰጡ ከሚችሉ ሰዎች ጋር መተዋወቅን፣የለቅሶ መታደሚያው ቦታ የት እንደሆነ መለየትን፣ለመረጃ መሰብሰቢያ የተያዙትን መሳሪያዎች ደህንነት ማረጋገጥን በቅድመ ዝግጅት ጊዜ አጠናቅቄ ነው ወደ ስራው የገባሁት። የነዚህን ተግባራት ሂደት በዝርዝር አቀርባለሁ።

በሁሉም ቀበሌዎች ውስጥ ስለ ለቅሶና ለቅሶን በተመለከተ ግንዛቤ ያላቸውንና በማህበረሰቡ ዘንድ ታዋቂ የሆኑ እንዲሁም ከለቅሶ ጋር በተያያዘ በእድርና ሌሉችም ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ሃላፊነት ያላቸውን ሰዎች ለመረጃ ሰጭነት መለየት ተገቢ ነበር። በዚህም መሠረት ታዋቂና ፈቃደኛ መረጃ ሰጭዎችን ለማግኘት በቅድሚያ ሁለት አካላትን ማግኘት የግድ ይል ነበር። እነዚህ አካላትም የደቡብ ጎንደር አስተዳደር ዞን ባህልና ቱሪዝም እና የደብረታቦር ከተማ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሃላፊዎች ናቸው ። እነዚህ ሃላፊዎችም በሰጡኝ አድራሻ መሰረት ደብረታቦር ከተማ ውስጥ የሚገኙ የ 19 እድሮችን ሃላፊዎች መተዋወቅ ችያለሁ። በነዚህ ከተማ ውስጥ ባሉት ሰዎች አማካይነት በገጠር ቀበሌያት ያሉትን ንጣሚዎችና ፎካሪዎችን ማግኘት ተችሏል። ከዚያም ከነዚህ ሰዎች ጋር ትውውቅ ካደረግን በኋላ ለቅሶ መናር አለመኖሩን፣ ለቅሶው የት እንደሚታደም፣ ለቅሶው የዕለትና የቅጥር መሆንና የሚቹን ማህበራዊ ደረጃ ጭምር መረጃ እንደሚሰጡኝ በመግባባት

የስልክ አድራሻ በመለዋወጥ ሃያ ከሚሆኑ መረጃ ሰጭዎች ጋር ቅድመ ትውውቅ አደረግሁ፡፡ ከእነዚህ ሰዎች ውስጥ አብዛኞቹ የወየታም ሆነ የፋክራ ግጥሞችን በመደርደር የታወቁ ናቸው፡፡

ከዚህ በፊትም የማውቃቸው ሰዎች መኖራቸውና ለምፈልገው መረጃ ቅርብ በመሆናቸው መረጃውን በመሰብሰብ ሂደት ጥሩ አጋጣሚ ፈጥሮልኛል፡፡ ይህን የፈጠረልኝ ደግሞ ተወልጄ ያደግኩት ከዚያው ደብረታቦር ከተማ አስፋው ግራር ቀበሌ 01 በመሆኑ ከአብዛኛዎቹ መረጃ ሰጭዎች ጋረ በሥራ እና በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች አማካይነት የምተዋወቅ መሆኔ ነው፡፡

እነዚህ ሰዎች  ለመረጃው ቅርብ የሆኑበት ምክንያት በከተማው ወጣት አዋቂውን ሲጣላ ከማስታረቅ ጀምሮ በሃዘኑም ይሁን በደስታው ወቅት በማስተባበርና ማህበረሰቡን ወክለው በተለያዩ ቦታዎች በመገኘት የማህበረሰቡን አቋምና ፍላጐት በመግለፅና በማሳወቅ የሚሰሩ በመሆናቸው ነው፡፡ በተጨማሪ  አንዳንዶቹ የእድር ሊቀመንበር፣ አንዳንዶቹ ደግሞ በየቀበሌው  አስታራቂ ሽማግሌዎች ና  ለማህበረሰቡ  ማህበራዊና  ባህላዊ  ጉዳዮች ቅርበት ያላቸው በመሆናቸው የታላሚ  የመረጃ  አቀባዮች አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም ሊመረጡ ችለዋል፡፡

ከዝግጅቶቹ አንዱ በደብረታቦር ከተማ ውስጥ ሰው ሲሞት የት እንደሚለቀስ፣ የማልቀሻ ቦታዎች የት የት እንደሚገኙ እንዲሁም የቀብር ቦታዎች የት የት እንደሆኑ ማጣራት ነበር፡፡ በዚህም መሠረት ቀደም ሲል በተዋወቅኳቸው ሰዎች አማካይነት ቦታዎችን መለየት ጭያለሁ፡፡ በተገኘው መረጃ መሰረት ታዋቂ ሰው ሲሞትና ተራ ሰው ሲሞት የሚለቀስበት ቦታ የተለያየ ነው፡፡ ተራ ሰው ሲሞት በመኖሪያ ቤቱ አካባቢ በሚገኝ ክፍት ቦታ ማለትም የከብት ማገጃ ቦታ እና በቀበሌው አካባቢ ይለቀሳል፡፡ ታዋቂ ሰው ሲሞት ደግሞ የሚታደመው ሰው በርካታ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ "እጅባር" የሚባል ሰፊ ሜዳ ላይ ይለቀሳል፡፡ እጅባር ከከተማው አማካይ ቦታ ላይ የሚገኝ ሲሆን በዐፄ ሰይፈ አርዕድ ዘመን የነበሩ መጋቢ አበባው የተባሉ ታዋቂ ሰው ይህን ቦታ የህዝቦች መገናኛ ይሁን፣ ከብት እንዳይገባበት በመከልከል "እጅባር" ብለው እንደሰየሙት እና ምናልባትም ትርጉሙ ሰፊ ሜዳ ማለት ይመስለኛል ሲሉ ከመረጃ ሰጭዎች መካከል አቶ አለምነው አሉላ የተባሉ የ67 አመት የዕድሜ ባለፀጋ ገልፀውልኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ 12/05/2004 ዓ.ም)፡፡

አጅባር ሜዳ ከማህበራዊና ከሃይማኖታዊ ጉዳዮች ሌላ እንደ ለቅሶና እንደ ጉግስ ያሉ ባህላዊ ክዋኔዎች እንዲሁም የተለያዩ ዘመናዊ ስፖርታዊ ውድድሮች ይካሄዱበታል፡፡ ታዋቂ ሰው ሲሞትም ወደ አጅባር ሜዳ በመሄድ ለቅሶው ይከናወናል፡፡

የሥርዓተ ቀብር መፈፀሚያ ቦታን በተመለከተ ታዋቂም ይሁን ተራ ሰው ሟች በህይወት ሳለ ቤተክርስቲያን በመሳምም ይሁን በማስቀደስ ከሚያዘወትርበት እና ከዚያ በፊት አያት ቅድመ አያቶቹ ወይም የቅርብ ዘመድ የተቀበረበትን ቤተክርስቲያን ቅድሚያ በመስጠት ስርዓተ ቀብሩ እንደሚከናወን ከመረጃ አቀባዮች መረዳት ተችሏል፡፡

በዚህ መሠረትም ከሜዳው ወጣ ብለው በከተማው አካባቢ የሚገኙ እናቲቱ ማርያም፣ ቅዱስ መድሃኒያዓለም፣ ልጅቱ ማርያም፣ ወይብላ ማርያም፣ ደብረታቦር ኢየሱስ፣ ቅዱስ ኡራኤል፣ ፁጉር ኪዳነ ምህረት፣ ፀጉር ሚካኤል፣ ጎሩይ ጊዮርጊስና ባዕታማርያም የሚባሉ ቤተክርስቲያኖች እንደሚገኙና ቀብርም በነዚህ ቤተክርስትያኖች እንደሚፈፀም መረጃ አቀባዮቼ ነግረውኛል፡፡

ወደ ጥናቱ ቦታ ወደ ደብረታቦር ከተማ ለመድረስ ከአዲስ አበባ 667 ኪሎ ሜትሮችን በመኪና መጓዝ ነበረብኝ፡፡ ለጉዞው ከመነሳቴ በፊት የያዝኳቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች መንገድ ላይ ሊበላሹ፣ ሊጠፉና ችግር ሊያጋጥማቸው ይችላል የሚል ስጋት ስላደረብኝ ወደ ስራ ከመግባቴ በፊት በጥንቃቄ ይዠና ተመልክቼ ለስራ ዝግጁ መሆናቸውን በማረጋገጥ፣ በካሜራውም ሆነ በቴፕ ሪከርደሩ ባትሪ መኖር አለመኖሩን አጣርቼአለሁ፡፡ ከመሳሪያዎቹ ዝግጅት በላይ ደግሞ በጥናት ቦታው ተገኝቼ ስራው ለመጀመር የሚያስችለኝን ስነ ልቦናዊ ዝግጅት አስቀደመሜ አድርጌአለሁ፡፡

### 1.7.2 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች

ይህ ጥናት ምልከታንና ቃለ መጠይቅ በዋነኛነት የተጠቀመ ሲሆን ለተወሰኑ ጉዳዮች ደግሞ የቡድን ውይይት እጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ቀጥሎ የነዚህ ዘዴዎች መልክ በዝርዝር ቀርቧል፡፡

### 1.7.2.1 ምልከታ

ምልከታን Goldstin (1964፣77) "The term observation, as used in this context, is not limited only to visual aspcts of the situation, but also involves a full range of sensual experience including hearing, feeling, smelling, and tasting, whenever these may be appropriate". ባሉት መሰረት እኔም ከዚህ ሃሳብ መረዳት የቻልኩት በምልከታ ዘዴ መረጃን ለማግኘት የመስክ አጥኝዎች ባይናቸው መመልከት ብቻ ሳይሆን በሌሎች የስሜት ህዋሳታቸውም ጭምር ሁኔታውን መረዳት እና መገንዘብ ያለባቸው መሆኑን ነው። በዚህ ጥናት ምልከታ የተመረጠበት ምክንያት አንዱ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ በመጋራት ወይም አልቃሹ የሚያከናውነውን ትዕይንት ሁሉ እንደነሱ ሆኖ በማከናወን መረጃ ለመሰብሰብ ስለሚያስችል ነው። የለቅሶ ክዋኔ መሮጥ፣ መቀመጥ፣ መነሳት፣ መንበረከክ እና ሌሎችንም አስደንጋጭ እንቅስቃሴዎች ሥለሚጨምር እነሱን ሆኖ መከወን የግድ ይላል። ይህ በመሆኑ አጥኙውም የክዋኔው ተሳታፊ ነው ማለት ይቻላል።

ሌላው ምክንያት ደግሞ ጥናቱ ተፈጥሮአዊ አውድ (natural context)ን መሠረት ያደረገ በመሆኑ ለቅሶው በሚከወንበት ቦታ በመገኘት ሟቹ ማን እንደሆነ፣ የሟች ቤተሰቦች እነማን እንደሆኑ፣ ማህበራዊ ደረጃቸው ምን እንደሚመስል፣ የከዋኞቹን እና የታዳሚዎቹ ጥምረት ምን እንደሚመስል፣ የአልባሳቱና በለቅሶው ላይ የተያዙ ቁሳቁሶች፣ በቃል ግጥም ታጀበው የሟቹን ማንነት እንዴት እንደሚያንፀባርቁና በአጠቃላይ የለቅሶው ድባብ ምን እንደሚመስል፣ ለማወቅ ስለሚረዳ ነው። በሌላ መንገድ የመረጃ ሰጭዎችን የመረጃ ባለቤትነት ከማረጋገጡም በላይ የመረጃውን ተአማኒነት ያጎላዋል። አጥኙውንና ተጠኚውን ማህበረሰብ ቀጥታ በተመሳሳይ ሰዓትና ስፍራ በማገናኘቱም የመረጃውን ተአማኒነት ይበልጥ ያጠናክረዋል። በተጨማሪም በአጥኙው አዕምሮ ውስጥ የተለያዩ ጥያቄዎች እንዲፈጠሩ እና እንዲህ ለማለት ፈልገው ይሆን? በማለት በአንድ አቅጣጫ ብቻ ሳይሆን በተለያየ አቅጣጫ እንዲያስብ ያደርገዋል። ይህን የለቅሶ አጋጣሚ በመጠቀም ሰዎች ከተለያየ አካባቢ መጥተው ለቅሶውን ይታደማሉ። አብዛኛዎቹም ለቅሶውን ከደረሱ በኋላ ፈንጠር ፈንጠር ብለው በቡድን በቡድን የግል ጉዳያቸውን ያነሳሉ ይጥላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ግጥሞችን ከመግጠምና ከማስገጠም ጀምሮ "እውነት ነው"፣ "እንዲያበል"፣ "ምን ታደርገዋለህ" ወዘተ. በማለት የለቅሰውን ክዋኔ በማድመቅ ዋና ተዋናኝ ሆነው ይታያሉ። አንዳንዶቹ ቆም እያሉ፣ ሲሻቸው እየተንበረከኩ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ያልተጠበቀና አስደንጋጭ አካላዊ እንቅስቃሴ እያደረጉ

በለቅሶው ዋና ክዋኔ ላይ ይሳተፋሉ።የምልከታው ዘዴ ይህን ሁሉ ለማየት አስችሏል። በምልከታየ ጊዜም የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ማለትም ቪዲዮ፣ ፎቶ ካሜራና ድምፅ ሪከርደር ተጠቅሜያለሁ።

## 1.7.2.2 ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ ማድረግ በፎክሎር ጥናት በጣም የታወቀና የተለመደ የመስክ ጥናት ዘዴ ነው። የቃለ መጠይቅ መረጃ አቀባዩ በተነሳው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ያለውን አጠቃላይ እውቀት ማለትም እምነት፣ ሃሳብ፣ ስሜትና ፍላጐት ወዘተ. የመሳሰሉትን ያጠቃልላል። በመሆኑም የሰዎችን ሃሳብ ወይም ክስተቶችን ከአካባቢው አጠቃላይ የክዋኔ ድባብ ጋር በማቀናጀትና በማነፃፀር ለመጠየቅ ይረዳል። ይህ የሚወስነው ቃለ መጠይቅ በሚደረግለት ሰው ነው። የመስክ አጥኚው በሚያጠናው የባህል ጥናት ተሳታፊ በመሆን በተሳትፎ ምልከታ ወቅት በአጥኚው አዕምሮው ውስጥ ያጫሩትን ጥያቄዎች በቃለ መጠይቅ ጊዜ በማንሳት የተሻለ ማብራሪያ ማግኘት ስለሚችል አስፈላጊነቱን ከፍ እንዲል ያደርገዋል። በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ የተሻለ መረጃ ይሰጡኛል ያልኳቸውን 20 ሰዎችን በታላሚ ናሙና አመራረጥ በመምረጥ አሥሩ አምስቱን በቁልፍ መረጃ አቀባይነት አምስቱን ደግሞ በተራ መረጃ አቀባይነት መረጃ እንዲሰጡኝ አድርጌያለሁ።

እነዚህ መረጃ ሰጭዎች የተመረጡበት ምክንያት ተወልደው ያደጉት በዚሁ በደብረታቦር ከተማ በመሆን በማህበረሰቡ ውስጥ ተሰሚነትና በርዕሰ ጉዳዩ ላይ የተሻለ እውቀት ያላቸው ሰዎች መሆናቸውን በማወቁ ነው። ይህ ደግሞ የተሻለ መረጃ ከማግኘትም በተጨማሪ ጊዜ፣ጉልበትና ገንዘብን በመቆጠብ ጠቀሜታው የጎላ ሆኖ አግኝቼዋለሁ ። ቃለ መጠይቁ በሁለት አይነት መንገድ የተከናወነ ነበር። እነሱም የመክፈቻ ቃለ መጠይቅ /Pre interview/ እና ጥልቀት ያለው ቃለ መጠይቅ /In-depth interview/ ናቸው። የመክፈቻ ቃለ መጠይቅ ከመረጃ ሰጭዎች ጋር መተዋወቅያና ወደ ዋናዎቹ ጥያቄዎች መንደርደሪያ ሲሆን ጥልቀት ያለው ቃለ መጠይቅ ደግሞ ስለጉዳዩ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት የሚያስችሉ በርከት ያሉና ትልልቅ ጥያቄዎች የሚጠየቁበት ነው።

ለቃለ መጠይቅ የተዘጋጁትን ጥያቄዎች አስቀድሞ በመግለፅ ከወዲሁ እንዲዘጋጁበት በማድረግ ተራ በተራ ቃለ መጠይቅ ተደርጓል። ቃለ መጠይቁም የተደረገው አልፎ አልፎ በመሆን የማሰቢያ ጊዜ እንዲኖራቸው ረድቷል። ሁሉም መረጃ ሰጭዎች ያለገደብ መረጃ

እንዲሰጡ፣ አንዳንዴም መሪ ጥያቄዎችን በማንሳት ወደ ሚፈለገው ነጥብ እንዲመጡ፣ በምልከታ ወቅት የተፈጠሩት ብዥታዎች ምላሽ እንዲያገኙ በማድረግ መረጃው ተሰብስቧል። በተለይም በጥናቱ ዋና ጉዳይ በሆነው በሙሾ፣በወየታ እና በፉከራ ግጥሞች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በተመለከተ፣ እና ግጥሞቹ ከዖታና ከማህበራዊ ደረጃ አኳያ ለማን ለማን እንደሚገጠሙ የሚያስረዱ መረጃዎችን በቃለ መጠይቁ መሰብሰብ ተችሏል።

### 1.7.2.3 የቡድን ውይይት

ለዚህ የቡድን ውይይት የተመረጡት መረጃ ሰጭዎች በቃለ መጠይቅ ጊዜ መረጃ የሰጡ ሰዎች ናቸው። ይህ የሆነበት ምክንያትም ለቃለ መጠይቅ መረጃ ከሰጡት ሰዎች ውስጥ በደብረታቦር ከተማ ውስጥ ተካተው ከሚገኙ የገጠር ቀበሌዎችም ጭምር የመጡ በመሆናቸውና ለቡድን ውይይቱ ተጨማሪ ጊዜና ጉልበት ማባከኑ አስፈላጊ መስሎ ስላልታየኝ በተመሳሳይ ጊዜ ለማካሄድ ተገድጃለሁ። ለቃለ መጠይቅም ይሁን ለቡድን ውይይት 20 ሰዎች የተመረጡበት ምክንያት ባጋጣሚ ነው። በመረጃ ሰጭነት ሴቶች አልተመረጡም። ሴቶች ያለመካተታቸው ምክንያት ስለ ርዕሰ ጉዳዩ በይበልጥ የሚያውቁት ወንዶቹ መሆናቸው በተሰጠኝ ጥቆማ መሰረት ነው። በቃለ መጠይቅ ስዓት 15ቱ ሰዎች ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ሲሆኑ 5ቱ ደግሞ ተራ መረጃ አቀባዮች ናቸው። በቡድን ውይይት ጊዜ ግን ሁሉም በስፍራው ቢኖሩም መረጃ የሰጡት ግን 10ሩ ሰዎች ናቸው። ውይይቱም የተካሄደው በ25/05/2004 ሲሆን ከአንድ ሰዓት ተኩል እስከ ሁለት ሰዓት ቆይታ አድርገናል።

በዚህም መሠረት በተለይ በወየታና በሙሾ ግጥሞች መካከል ስለአለው ልዩነት፣ ለቅሶ በደብረታቦር ማህበረሰብ ዘንድ ለምን ትልቅ ስፍራ እንደተሰጠው፣ጉዳዩም በሰፊው እንዲጠና ለማድረግ የነሱ ሚና ምን መሆን እንዳለበት ውይይት ተደርጓል። እንዲሁም ወየታ፣ ሙሾ እና ፉከራ የሚባሉት ጉዳዮች ምን ማለት እንደሆኑ፣በአንዳንድ የቦታ ስሞች ስያሜ እና ሌሎች ትርጓሜዎችን በሚፈልጉ ጉዳዮች ላይ ውይይት ተካሂዷል።

## 1.8 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

መረጃውን በሚሰበሰብበት እና ጥናት በሚካሄድበት ወቅት የተለያዩ ችግሮች አጋጥመዋል። ያጋጠሙ ችግሮችን በመፍታት አስፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ ተችሏል። በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርበዋል።

### 1.8.1 የገንዘብ እጥረት

ለመስክ ስራ በግንባር ቀደምነት አስፈላጊ ከሆኑት ጉዳዮች ውስጥ ገንዘብ ትልቁን ቦታ ይይዛል። በተለይም ለባህል ጥናት አጥኝዎች ደግሞ ሌሎች የአጥኙው ጥንካሬዎች እንዳሉ ሆነው ገንዘብ ትልቁን ሚና ይጫወታል። ከመረጃ ሰጭዎች ጋር በየጊዜው በመገናኘት እነሱን ለመጋበዝም ይሁን የኪስ ገንዘብ ለመስጠት የተመደበው ገንዘብ በቂ ባለመሆኑ እና ካለው የኑሮ ውድነት አኳያ ለጥናት የተመደበው ገንዘብ አነስተኛ በመሆኑ በአንድ ወር የመስክ ቆይታ ከፍ የጊዜ ያለ ችግር ፈጥሯል።

ይህን ችግር ለማቃለል በእድሜ ከእኔ እኩያ ለሆኑትና በተለይም ለዋናው መረጃ ጥቆማ በመስጠት ለተባበሩኝ፣ ለቅሶ የት እንዳለ፣ማን እንደሞተ፣የሟች ማህበራዊ ደረጃ ምን እንደሚመስል እገዛ ላደረጉ 5 ሰዎች ለእያንዳንዳቸው የ100 ብር ሞባይል ካርድ ሰጥቻለሁ። በእድሜ ትልቅ ለሆኑትና ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ደግሞ ለእያንዳንዳቸው ብር መስጠት ከዚህ በፊት ከነበረን ማህበራዊ ግንኙነት አኳያ ደስ ላይላቸው ይችላል በማለት ከተገናኘንባቸው 5 ቀናት ውስጥ በሁለቱ ቀናት ቢጋራ ሆነው እንዲጫወቱ 500 ብር ድምር 1000 ብር በመስጠት ግንኙነታችን በጥሩ አኳኋን ላይ መመስረት በመቻሉ ችግሩን ለመፍታት ተችሏል።

### 1.8.2 የክዋኔው ጊዜ ማጠር

በአንድ ቀን የተለያዩ የለቅሶ ክዋኔዎች መኖራቸው፣ ካሁን በፊት ከጧት ጀምሮ እስከ ዘጠኝ እና አስር ሰዓት ይውል የነበረ ለቅሶ በአሁኑ ጊዜ ግን እስከ አራት ሰዓት ብቻ እንዲቆይ በመደረጉ በርካታ የወየታና የቁከራ ቃል ግጥሞች ሳይከወኑ ገጣሚዎች እኔ እገጥም እኔ እገጥም እንዳሉ መቅረታቸው በአጥኙው አረዳድ እንደ ችግር ታይቷል። ይህ የሆነበትን ምክንያትም መረጃ ሰጭዎች ሲያብራሩ በመንግስት ዘንድ ሥራ ላይ መዋል

የሚገባው ጊዜና ትልበት ያላግባብ እየባከነ ነው የሚል እምነት በመኖሩ ምክንያት እስከ አራት ሰዓት ብቻ እንዲቆይ ተወስኗል፡፡ ከዚህ ካለፈ ግን ለሟች ፍታት እንደማይደረግለትና በንስሃ አባቶች ውግዘ እንደተደረገ መረጃ አቀባዮቹ ገልፀውልኛል፡፡

በዚህ ረገድ የተከሰተውን ችግር አብዛኛዎቹ ለቅሶዎች ተመሳሳይ በመሆናቸው በተለየ መልኩ ግጥም የሚያረደርላቸው ጀግና ሰዎች የሞቱበትን ለቅሶ በመለየትና አስፈላጊ ነው የተባለውን መረጃ በፍጥነት በመሰብሰብና ቀረፃ በማካሄድ ለመፍታት ተችሏል፡፡

### 1.8.3 የመረጃ ባለቤቶች ፈቃደኛ አለመሆን

የመረጃ ባለቤቶች የተባሉት የሟች ቤተሰቦች፣ስለ ለቅሶ በቂ ማብራሪያ ሊሰጡ የሚችሉ ሰዎችንና ገጣሚዎችን ነው፡፡ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ለቅሶዎች መቅረፀ ድምጽ፣ ቪዲዮና ፎቶ ካሜራ ለመጠቀም በተወሰነ መልኩ አስቸጋሪ ነበር፡፡ የሟች ቤተሰቦች እነሱ ያላወቁት ሰው ለቅሶውን ሲቀርፅ ሲመለከቱ ጠይቀዋል፡፡ በገጣሚዎች በኩል ሁለት ነገር መመልከት ተችሏል፡፡ አንዳንዶቹ እንዲያውም እራሳቸው ለመቀረፅ ካላቸው ፍላጎት የተነሳ ሲፎክሩም ይሁን ወየታ ሲያረድሩ ወደ ካሜራው እየቀረቡ ነበር፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ካሜራውን ሲያዩ እጃቸውን ከፍ በማድረግ ፊታቸውን በመከለል ፍቃደኛ አለመሆናቸውን አመልክተዋል፡፡

የተፈጠረውን ችግር ለማቃለል በጊዜው እንዲህ ነው ብሎ ለማስረዳት መሞከር የለቅሶውን ድባብ ከመረበሽ ባለፈ የአንድ አጥኝ ስነ ምግባርም ባለመሆኑ በጊዜው ፈቃደኛ የሆኑትን ሰዎች ብቻ በመለየት ቀረፃ ተካሂዷል፡፡ ከሌሎቹ ጋርም ስለ ጥናቱ አስፈላጊነት በማስረዳት ችግሩን መፍታት  ተችሏል፡፡ በተለይም ከነዚህ ሁለት ለቅሶዎች በኋላ ከሟች ቤተሰቦች ጋርም ይሁን ከገጣሚዎች ጋር ቅድሚያ በመነጋገርና ፈቃደኛ እንዲሆኑ በማድረግ የሚፈለገው መረጃ በተገቢው መንገድ ተሰብስቧል፡፡ ሌላው የገጠመ ችግር አንዱ ገጣሚ ስለ ሌላው ገጣሚ ያለው አመለካከት ነው፡፡ ይህውም አንዳቸውን ስለሌላው መረጃ እንዲሰጡ ሲጠየቁ እገሌ 'ቡዳ' ነው እንዳይበላህ ከሱ ቤት አትሂድ በማለት የስነ-አዕምሮ ጫና ለማሳደር ሞክረዋል፡፡ ነገር ግን ቡዳ ነው ወደ ተባለው መረጃ ሰጭ ቤት ድረስ በመሄድና ጥሩ ትውውቅ  በመፍጠር እሱም በዚያ አካባቢ የታወቀና አለ የተባለ ፎካሪ በመሆኑ በየቀኑ ከተለያየ ቦታ የለቅሶ ጥሪ ስለሚደረግለት ከሱ ጋር በመሄድ የምፈልገውን መረጃ ያለገደብ መሰብሰብ ችያለሁ፡፡

### 1.8.4 የመብራት መጥፋት

በመረጃ መሰብሰብ ሂደት ከገጠሙ ችግሮች ውስጥ አንዱና ዋነኛው የመብራት መጥፋት ነው። ለአንድ ሳምንትና ከዚያ በላይ መብራት በመጥፋቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መግሪያዎችን በተፈለገው ጊዜና ሰዓት ለመጠቀም አስቸጋሪ ነበር። ወረታና ባህር ዳር ለሚመላለሱ የታክሲ ሹፌሮች በመላክ ባትሪ በማስሞላትና አንዳንድ ጀኔሬተር ካላቸው መስሪያ ቤቶች ትብብር በመጠየቅ ችግሩን በተወሰነ ደረጃ ለመፍታት ተችሏል።

## 1.9 የመስክ ቆይታ ውጤት

ይህ ክፍል በመስክ ቆይታ ስንት ክዋኔዎች ተገኙ? ምን ዓይነት መረጃ ተሰበሰበ? እንዴት ተሰበሰበው? ከማን ተሰበሰበ? መረጃ ሰጭዎች? ምን ያክል መረጃ ተሰበሰበ? የሚሉትን የመስክ ስራ ውጤቶች የሚገልፅ ነው።

### 1.9.1 ክዋኔዎች

መረጃውን ለመሰብሰብ በተደረገው የአንድ ወር ቆይታ የአራት ወንዶችና የሁለት ሴቶችን በድምሩ የስድስት ሰዎችን የለቅሶ ክዋኔዎች በአካል በመገኘት መከታተል ተችሏል። ሟቾችም አቶ እውነቱ ዘለቀ ቀበሌ ፀጉር ኪዳነምህረት በ16/05/2004፣ አቶ እሱያውቃል በሌጠ ቀበሌ ደብረታቦር ኢየሱስ በ21/05/2004፣ አቶ ንጋት ዘለቀ ቀበሌ አባረጋይ በ30/05/2004፣ ወ/ሮ እቴነሽ አበበ ቀበሌ 04 በ 02/06/2004፣ አቶ ወረደ መኮንን ከበሌ 02 በ 05/06/2004 እና ወ/ሮ አበሩ ንጉሴ ቀበሌ 02 በ15/06/2004 ናቸው። ሆኖም ለዚህ ጥናት በማሳያነት የቀረቡት ሁለት የለቅሶ ክዋኔዎችና ግጥሞች ናቸው።የሁለቱን ሴቶች የለቅሶ ክዋኔ ስንመለከት ሁለቱም የሰባተኛውን ቀን አድቬንቲስት ሃይማኖት ተከታይ በመሆናቸው ምንም ዓይነት የወየታም ሆነ የቆከራ ግጥሞች አልተደረደሩም። በግጥሞቹ ፋንታ መዝሙር በመዘመር ክዋኔው ተካሄዷል። በሌሎቹ ሁለት ወንዶች ለቅሶ ክዋኔ ላይም መጠነኛ የወየታ ግጥሞች የተደረደሩ ሲሆን ለቅሶው ከታዳሚው ማነስ ጀምሮ ክዋኔውም ሳቢ አልነበረም።

በመጨረሻም ለዚህ ጥናት በማሳያነት የተመረጡት የአቶ እውነቱ ዘለቀ እና የአቶ ወረደ መኮንን የለቅሶ ክዋኔዎች ናቸው። ብዙ ታዳሚዎች እና ከዋኞች የተገኙባቸው ናቸው። በነዚህ ላይ የታዳሚዎቹ ግጥም የማውረድ ቶክክር፣ እየወደቀ እየተነሳ የሚያለቅሰው አልቃሽ ሁኔታ፣ ይታይ ነበር። ለፎካሪዎቹ የቀረቡት የተሸለሙ በቅሎዎች ብዙ ነበሩ። የሟች

ቤተሰቦች ሽጉጥና ዝናር ታጥቀዋል። ጓደኞቹ የያዙት ጦርና ጎራዴ ይዘዋል። በዙሪያው ብዙ ባንዲራ ይውለበለባል። ማህበርተኞች በመሀረብ የተጠቀለለ ዋንጫ ይዘዋል። ለገጣሚዎቹ ወረፋ ባለመድረሱ ምክንያት ለቅሶው በሁለትና በሦስት ተከፍሎ ፉከራዎች ይፎከራሉ። ሲደበላለቅ፣ የሴት ወገን እና የወንድ ወገን ጎራ ለይቶ በፉከራ ግጥም ሲወዳደስና ሲወቃቀስ ይታያል። ማዶ ለማዶ በቅሎ ላይ ሆኖ እንደማመጥ እንጅ በማለት የሰውን ብዛት የለቅሶውን መድመቅና ይህን ተከትሎ በቀላሉ መደማመጥ አስቸጋሪ የነበረበት ክዋኔዎች ነበሩ፡

## 1.9.2 ከዋኞች

ከሟች ቤት ጀምሮ አደባባይ ሲለቀስ ውሎ ቀብሩ እስከሚፈፀም ድረስ በርካታ ከዋኞች ይሳተፋሉ። አንዳንድ ጊዜ ከዋኞችንና ታዳሚዎችን ለመለየት ያስቸግራል። ታዳሚ የነበረው ከዋኝ ሲሆን ከዋኝ የነበረው ደግሞ ታዳሚ የሚሆንበት አጋጣሚ በርካታ ነው። ምክንያቱም መሬት ላይ ሆኖም የሚያስገጥም በቅሎ ላይ ሆኖም የሚገጥም እንዲሁም የሚፎክረውና የሚያስፎክረው በርካታ ነው። በመስክ ቆይታዩ ከተመለከትኳቸው ትዕይንቶች መካከል አንዳንዶቹ በቅሎ ላይ የመውጣት እድል ይነፈጋቸውና መሬት ላይ ሆነው ይፎክራሉ። አንዱ ካንዱ ላይ እየነጠቀ ይፎክራል። አንዳንዱ በመሃከል በቅሎ ላይ ያለው "እንደማመጥ እንጅ" በማለት የለቅሶውን ድባብ ጋብ በማድረግ መሬት ያሉትን ዝም እንዲሉ አልቃሹ ተዕዕኖ እንዲያደርግባቸው ጥረት ያደርጋል። በዚህ ሁኔታ በአንድ ለቅሶ ቢያንስ ከ10-20 የሚደርሱ ከዋኞች ወይም ግጥም ደርዳሪዎች ሲኖሩ የገጣሚዎች ብዛትም እንደ ሟቹ ማህበራዊ ደረጃ ይወሰናል።

## 1.9.3 ታዳሚዎች

አጥኚው በተሳተፍባቸው ስድስት የለቅሶ ክዋኔዎች በሁሉም እኩል መጠን ያለው ታዳሚ አልነበረም። በተለይም በሁለቱ ሴቶች ለቅሶ ላይ የተገኘው ሰው ብዛት በግምት ከ300 እስከ 500 የማይበልጥ ነው። በሌሎቹ ሁለት ወንዶች ለቅሶዎች ደግሞ በግምት ከ700 እስከ 1000 ይሆናል። በመጨረሻ ደግሞ ለዚህ ጥናት በማሳያነት በቀረቡት ሁለት ለቅሶዎች ክዋኔ ላይ ደግሞ በግምት ከ2000 እስከ 2500 ይደርሳል። በመሆኑም ይህ መረጃ የተሰበሰበው በነዚህ ሁለት ለቅሶዎች ክዋኔ ከ70 እስከ 80 ከሚደርሱ ገጣሚዎች ነው።

### 1.9.4 መረጃው እና መረጃ ሰጭዎች

የፎክሎር ጥናት መረጃ ሲሰበሰብ ትኩረት የሚደረገውና የመረጃው ቁልፍ ማዕከል ክዋኔው ላይ ያለውን ትዕይንት በሚገባ መግለፅ መቻል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ግጥሞቹ የተሰበሰቡት ከዚያው ክዋኔው ላይ ነው፡፡ ከአንዳንድ መረጃ ሰጭዎች ጋር ቃለ መጠይቅ የተደረገበት ምክንያትም በምልከታ ወቅት በአጥኝው አዕምሮ የተፈጠሩትን ጥያቄዎች ለመመለስና ማህበረሰቡ ለቅሶን እንዴት እንደሚገልፀው፣ ከዋኞች ግጥሞችን እንዴት እንደሚገጥሟቸውና የፈጠራ ችሎታው በምን ላይ የተመሠረተ እንደሆነ፣ ማህበራዊ ግንኙነቶች ምን እንደሚመስሉና በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸው ቦታ ምን ያክል እንደሆነ በምልከታ ወቅት ለተሰበሰበው መረጃ ማጠናከሪያ እንዲሆን በማሰብ ነው፡፡

በዚህ መሰረት የተሰበሰቡት የወየታና የቆከራ ግጥሞች ብዛት 500 ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥም 200 የሚሆኑት ግጥሞች በቀጥታ ክዋኔው ላይ በመቅረጸ ድምፅ የተሰበሰቡ ሲሆን ሌሎቱ 300 ግጥሞች ደግሞ ከፎካሪዎች በጽሑፍ የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ 16 የወየታና 34 የቆከራ በድምሩ 50 ግጥሞች ለትንተና የተመረጡ እነዚህም የተመረጡት በቀጥታ ከዋኔው ላይ ከተሰበሰቡት ግጥሞች ውስጥ ነው፡፡ እነዚህ ግጥሞች የተመረጡበት ምክንያት ርዕሰ ጉዳዩን በተፈለገው መልኩ ያስረዳሉ ብዮ በማሰቤና ለምደባም አመች ሆነው ስለአገኘሁዋቸ ነው፡፡

# 2. ክለሳ ድርሳን

ይህ ክፍል ከ ርዕስ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቀደምት ጥናቶችንና የቲዎሪ አቋም የሚቃኝበት ነው። ቅኝቱም ርዕስ ጉዳዩ በተጠናበት አካባቢ የተጠኑ ቀደምት ሥራዎችንና ሌሎች መጻሕፍትን ዳሷል። በተጨማሪ የቲዎሪ አቋሞች የተዳሰሱበት ክፍል ነው። የተቃኙት ጥናቶች በለቅሶ ላይ ብቻ ያተኩሩት ናቸው።

## 2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ የጥናት ክፍል በለቅሶ ሥነ ሥርዓትና በሙሾ ግጥሞች ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ የተለያዩ ጽሑፎች ተቃኝተዋል። በመጀመሪያም የምንመለከተው ርዕስ ጉዳዮቹን አንስተው የተጻፉ የመመረቂያ ጽሑፎችን ነው። ከዚያም ከተለያዩ መፃሕፍት ጥናቶች ይቃኛሉ። የዚህ ቅኝት ዋና አላማም የጥናቶቹ የትኩረት አቅጣጫ ምን እንደሚመስል እና ከዚህ የጥናት ጽሑፍ ጋር ያላቸው ተመሳስሎ እና ልዩነት ምን እንደሆነ ማመልከት ነው። በተለይ የትኩረት አቅጣጫቸው ምን ላይ ያተኩር እንደነበር፣ ክፍተቱን በመለየት አቅጣጫ ለመጠቆም ነው።

ታደሰ መንግስቱ በ(1963) "የጎጃም የለቅሶ ግጥሞች" በሚል ርዕስ የባችለር ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ አቅርቧል። የታደሰ ጥናት ትኩረቱ ምን ላይ እንደሆነ ለማወቅ ያስቸግራል። ምክንያቱም በጥናታዊ ጽሑፉ ውስጥ ዓላማ፣ ጠቀሜታና ወሰን አልተገለፁም። ጥናቱ ግጥሞችን ሰብስቦ ማቅረብ ላይ ብቻ የተወሰነ ነው። የቀረቡት ግጥሞችም አባት ሲሞት፣ እናት ስትሞት፣ ወንድም ሲሞት፣ እህት ስትሞት፣ ልጅ ሲሞት... በማለት የቤተሰብን የዝምድና አይነቶችን በመዘርዘር እንዲሁም የሟቹን የሞት አጋጣሚ ማለትም ሰው ለገደለው፣ ውሃ ለወሰደው፣ አውሬ ለበላው... በማለት አጋጣሚዎቹን በማንሳት በሃያ አራት ክፍል ከፍሎ ከማስቀመጥ ውጭ በአንድም ግጥም ላይ የደበትም ይሁን የቅርጽ ትንተና አላደረገም። መረጃውን የሰበሰበው በክረምትና በእረፍት ጊዜው ወደ አካባቢው በመሄድ መሆኑን ገልጿል። የሰበሰበውም የሙሾ ግጥሞችን ነው። የግጥሞቹን ክዋኔ አላሳየም።

ወርቁ ማንደፍሮ በ (1987) ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበውን ጥናት "በሊቦ ከምከም ወረዳ የለቅሶ ሥነ - ሥርዓትና የሙሾ ግጥሞች" የተሰኘ ነው። የዚህ የጥናት ትኩረት በሊቦ ከምከም ወረዳ አንድ ሰው ነፍሱ ከስጋው ከተለየችበት ጊዜ ጀምሮ እስኪቀበር

ድረስ ያለውን የለቅሶ ሥነ-ሥርዓት ነው። በተጨማሪም የሙሾ ግጥሞችን ከባህላዊና ኃይማኖታዊ ክዋኔዎች እንዳገር ለመመልከት ሞክሯል። ይሁን እንጅ አበይት ትኩረቱ የለቅሶ ሥነ-ሥርዓት ክዋኔ ነው። በዕለተ ሞትና ድኅረ ሞት የሚከወኑ የለቅሶ ሥርዓቶች እንደየ ሟቹ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሃየማኖታዊ ሁኔታና ደረጃ መሰረት በማድረግ እንደሚለያዩ ገልጿል። ከጥናቱ ዓላማዎች ውስጥም ህብረተሰቡ በግጥሞች አማካይነት የራሱን ማህበራዊ እሴቶችና አሻራዎች እንዴት ይገልፃል? ማሳየት ነው። የሚል ይገኝበታል። አጥኚው ክዋኔውንና ግጥሞቹን በመመልከት የይዘት ትንተና አካሂዷል። ነገር ግን የህብረተሰቡ ማህበራዊ እሴትና አሻራ ይህንን ይመስላል እያለ ዘረዘር ያለ ማብራሪያ አላቀረበም።

በመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ረገድ ጥንካሬም አለው። ከነዚህ ጥንካሬዎች ውሥጥም መረጃውን ሲሰበስብ የተሳትፎ ምልከታና ቃለ መጠይቅ በማድረግ፣በምሥልና በድምፅ በማስደገፍ መሰብሰቡ ነው። ከነዚህ ጥንካሬዎች ሌላ ደግሞ ድክመቶች አሉት። ዋነኛወ ድክመቱ በአብዛኛው ራሱን አብይ የመረጃ ምንጭ አድርጎ መውሰዱ ነው። ይህም የጥናቱን ተአማኒነትና ሚዛናዊነት እንዲቀንስ አድርጎታል። ሌላው 38 ግጥሞችን የተነተነ ሲሆን በምን መስፈርት እንደመረጣቸው በጥናቱ ውስጥ አልገለፀም። የጥናቱን ወሰን ባለመወሰኑና ባለመገለፁም ብዙ ክፍሎችን በመዘርዝር መልኩ እንዲነካካ አስገድዶታል።

"ክዋኔ በጎንደር ከተማ ለቅሶ ሥነ ሥርዓት" በሚል ርዕስ ጌጡ ታደሰ በ1989 የባችለር ዲግሪ ማሟያ ጥናት አቅርቧል። የጥናቱ ትኩረት የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ላይ ሲሆን ወደ ለቅሶው ከመግባቱ በፊት የከተማዋ ወግ፣ ልማድና ባህል ምን እንደሚመስል ሰፊ ማብራሪያ ሰጥቷል። በተጨማሪ ለቅሶ በጎንደር በሦስት አይነት እንደሚከፈሉና እነሱም የዕለት ለቅሶ፣ የቅጥር ለቅሶና የደመር ለቅሶ በማለት በየደረጃው ያብራራ ሲሆን የለቅሶ ባህሪያትን ገልጿል። ጌጡ ለተነሳበት ርዕስ ጉዳይ መንደርደሪያ የሚሆን ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት ያደረገ ሲሆን በዋናኛነትም የጠቀሰው የ Malinoweskie እና የ Bauman ን ስራዎች ነው።

የመረጃ አሰባሰብ ዘዴን በተመለከተ አጥኚው ምልከታንና ቃለ መጠይቅን የተጠቀመ ሲሆን ከሌሎች እንዳገር ስመለከተው መረጃን በመሰብሰብና መረጃውን መነሻ አድርጎ ትንተና በመስጠት የተሻለ ሆኖ አግኝቸዋለሁ።

ወርቅነሽ ደምሰው 1992 "ጀግና ወንዶችና ሴቶች ሲሞቱ የሚደረደሩ የለቅሶ ግጥሞች /በአቸፈር ዙሪያ ወረዳ/" በሚል ርዕስ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ አቅርባለች፡፡ ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ትኩረት ያደረገው በለቅሶ ወቅት በሚገጠሙ ግጥሞች ላይ ሲሆን እነሱንም በሙሾ፣ በቀረርቶ እና በፉከራ መልክ የሚቀርቡ በሚል አጥኝዋ በሦስት ዘርፎች ከፋፍላ ተመልክታቸዋለች፡፡ አጥኚዋ ወደ ጥናቱ ዝርዝር ጉዳይ ከመግባቷ በፊት ስለ ባህል፣ ስለ ክዋኔ፣ ስለ ለቅሶና ስለ ስነ ቃል ቅድመ ማብራሪያ ሰጥታለች፡፡ በዋናው ጥናቷ ውስጥ ግን በቀረርቶና በፉከራ እንዲሁም በሙሾ ላይ በሰጠችው ማብራሪያ ረስታ ከለቅሶ ውጭ ሊከወኑ በሚችሉ የቀረርቶና ፉከራ ግጥሞች ላይ ሰፊ ማብራሪያ ትሰጣለች፡፡ በተጨማሪም የለቅሶ ስርዓትን በሰፊው ያብራራች ሲሆን በመነሻዋ ላይ ስለ ግጥሞቹም ቢሆን የይዘትም ይሁን የቅርፅ ትንተና እንደምታደረግ አትገልፅም፡፡ ይህ ደግሞ መነሻዋን ወስና ባለመጀመሯ መድረሻዋ ምን ሊሆን እንደሚችል በተገቢው ሁኔታ አይጠቁምም፡፡

አጥኚዋ መረጃ የሰበሰበችው በዋነኛነት በቃለ መጠይቅ ብቻ ነው፡፡ በጥናቱ ውስጥ ሰፊውን ቦታ የሚይዘው ስለ ለቅሶው ስርዓት ምንነት የተደረገው ገለፃ ነው፡፡ አንድን የባህል ክዋኔ ደግሞ በቃለ መጠይቅ ላይ ብቻ ተመስርቶ ማጥናት አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

ካሳው ደሳለው በ1997 ያቀረበው የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ "የደብረሲና ወረዳ የለቅሶ ስርዓትና የሙሾ ግጥሞች ይዘት ትንተና" የሚል ነው፡፡ አጥኚው በዋነኛነት በለቅሶ ስርዓት ላይ ትኩረት በማድረግ ‹‹ቅድሙ ቀብር››ና ‹‹ድህረ-ቀብር›› በሚል በተለይም የሙስሊምና የክርስትና እምነት ተከታዮችን የለቅሶ ሥርዓት አብራርቷል፡፡ ነገር ግን በሙስሊምና በክርስትና እምነት ተከታዮች መካከል ያለውን የለቅሶ ሥርዓት በማነፃፀር አያሳይም፡፡ ምን አልባት ይህ እራሱን የቻለ ርዕስ ጉዳይ ሊሆን ስለሚችል መጀመሪያ ወስና ባለመነሳቱ የትኛው ላይ ትኩረት እንዳደረገ ለመረዳት አያስችልም፡፡

የመረጃ አሰባሰብ ዘዴውን ስንመለከት ካገው መቅረፀ ድምፅ በመጠቀም በለቅሶው ላይም ተገኝቶ ቀረፃ በማድረግም ግጥሞችን ለመሰብሰብ ሞክሯል፡፡ በዚህ መሠረትም ሁለት መቶ ሃምሳ ግጥሞችን በመሰብሰብ ሃምሳ አንድ ግጥሞች ተንትኗል፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ የመረጃ አሰባሰብ ሂደቱን የተሻለ አድርጎታል፡፡

ሽመልስ አክሊሉ በ 1997 "የቋሪት ወረዳ የለቅሶ ሥነ ሥርዓትና የለቅሶ ግጥሞች ይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ አቅርቧል፡፡ ሽመልስ በጥናቱ

ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ ይገልፃል። በዋነኛነትም በለቅሶው ሥርዓት ላይና በለቅሶው ግጥሞች ላይ ነው። በዚህ ላይም በተወሰነም መልኩ ቢሆን የለቅሶውን ስርዓት ገልጿል።

አጥኚው መረጃ ሲሰበስብ የተጠቀመው ዘዴ ቃለ መጠይቅ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ በተለይ የለቅሶውን ስርዓት በሚገባ ለማሳየት አያስችልም። ከዚህ አንፃር ሽመልስ ከመነሻው ርዕሱ ላይ ግልፅ የሆነ ነገር ይዞ ቢነሳ፣ በመረጃ አሰባሰብ ዘዴው ላይ ምልከታን ጨምሮ ቢጠቀም የተሻለ ጥናት ይሆንለት ነበር።

ፈለገ ህይወት ዘገዬ በ1997 "በባንጃ ሽኩዳድ ወረዳ የቀብር ስነ ስርዓት" በሚል ርዕስ አቅርቧል። የለቅሶ ግጥሞች ስብስብ ይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ የጥናት ጽሁፉን አቅርቧል። ፈለገ ህይወት በዚህ ጥናቱ ላይ ስለ ባንጃ ሽኩዳድ ወረዳ አጭር ታሪካዊ ዳራ ጽፏል። በመቀጠልም የባንጃ ሽኩዳድ ወረዳ የቀብር ስነ ስርዓት አፈፃፀም ከቀብር በፊት እና ከቀብር በኋላ ያለው ስነ ስርዓት ምን እንደሚመስል አሳይቷል። በለቅሶው ስነ ስርዓት ጊዜ የእድሮች እና የማህበራት ሚና ለሟች የሚደረጉ ሃይማኖታዊ ስርዓቶች "ቁርባን"፣ የ "አርባ" እና "የተዝካር"፣የመረዶ ለቅሶ የሚባሉትን ስነ ስርዓቶች እየዘረዘረ አሳይቷል። ይህንን ስራ ከሌሎቹ ለየት የሚያደርገው አጥኚው በለቅሶ ስነ ስርዓት ወቅት የእድሮችንና የማህበራትን ሚና በመመልከቱ ነው። ይህ ጉዳይ በተለይ ከማህበራዊ የህይወት ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ነጥቦችን ሊጠቁም ይችላል። ጥናቷድኩት ምልከታ ይህንን ጉዳይ የተመለከተ ሌላ ጥናት እስከ አሁን ድረስ አላጋጠመኝም። ከዚህ አንፃር የተሻለ ሊያስብለው ይቻላል።

አጥኚው ስለ ክዋኔ ምንነት አንድ ብያኔ ብቻ በመጥቀስና ስለ ስነ ቃልም የተወሰነ ነገር ብቻ በማለት አልፎታል። ጥናቱ የሚያተኩረው በግጥሞቹ የይዘት ትንተና ላይ በመሆኑ ስለ ይዘት ትንተና ምንነት መግለፅ ነበረበት።

የመረጃ አሰባሰብ ዘዴን ስንመለከት ምልከታ ቃለ መጠይቅ የቡድን ውይይት እና የጽሑፍ ምርመራ እንደተጠቀመ በመግለፅ "እንደ ይዘታቸው ተቀራራቢነት እና ልዩነት በመመደብ እና በመከፋፈል" የተወሰኑትን ግጥሞች መረጦ እንደተነተነው አስቀምጧል። ይሁን እንጅ ግጥሞቹ የተመረጡት በይዘት ሳይሆን በዕታ ምድብ ነው። በዚህም የወጥነት ችግር ይታያል።

የጌጡ ታደሰ "ክዋኔ በጎንደር ከተማ የለቅሶ ስነ ስርዓት" 1989 እና ፈለገህወት ዘገየ 1997 "በባንጃ ሽኩዳድ ወረዳ የቀብር ስነ ስርዓት" የሚሉት ጥናታዊ ጽሑፎች የትኩረት አትጣጫቸው የለቅሶ ስርዓት ይሁን እንጅ ዋናው ጉዳይ ሞት እና ሞት የፈጠረውን የለቅሶ አጋጣሚ ነው፡፡ በትንታኔው ውስጥም ሰፊውን ቦታ ይዞ የተገኘው የለቅሶውን ሥርዓት መግለፅ ነው፡፡ የእኔም ርዕስ ጉዳይ ለቅሶ በመሆኑ ከኔ ጋር ያላቸው ተመሳሳይነት ጉልህ ነው፡፡ ሌላው የለቅሶው ስርዓትም ሆነ ግጥሞቹም ሲነሱ ክዋኔው ይነሳል፡፡ ስነ ስርዓቱም ሆነ ግጥሞቹ ተዋህደው የአንድን ማህበረሰብ ባህላዊና መንፈሳዊ ማንነት የሚያንፀባርቁ በመሆናቸውና የሰውን ሞት ተከትለው የሚከወኑ በመሆናቸው ያመሳስላቸዋል፡፡

የወርቁ ማንደፍሮ "ቡሊቦ ከምከም ወረዳ የለቅሶ ስርዓትና የሙሾ ግጥሞች" 1987፣ የካሳው ደሳለው "የደብረሲና ወረዳ የለቅሶ ስርዓትና የሙሾ ግጥሞች ይዘት ትንተና" 1997፣ የሽመልስ አክሊሉ "የቋሪት ወረዳ የለቅሶ ስነ ስርዓትና የለቅሶ ግጥሞች ይዘት ትንተና" 1997 እና የፈለገ ህይወት ዘገዬ "በባንጃ ሺኩዳድ ወረዳ የቀብር ስነ ስርዓትና የለቅሶ ግጥሞች ስብስብ ይዘት ትንተና" 1997 የሚሉ ናቸው፡፡ የስነ-ስርዓቱም ይሁን የግጥሞቹ ማዕከል ለቅሶው በመሆኑ ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ ሌላው ደግሞ ቃል ግጥሞችንም እንዱ የትኩረት አትጣጫቸው በማድረጋቸው ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነታቸው የጎላ ነው፡፡

በመጨረሻም ወርቅነሽ ደምለው 1992 "ጀግና ወንዶችና ሴቶች ሲሞቱ የሚደረደሩ የለቅሶ ግጥሞች በአቸፈር ዙሪያ ወረዳ" በሚል ርዕስ ቅኝት የተደረገበት ጥናታዊ ጽሁፍ ሲሆን የጥናቱ ትኩረትም የለቅሶ ግጥሞቹን ነው፡፡ ከሌሎቹ ጥናቶች አንፃር ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳሳይነቱ የጎላ ነው፡፡ ምክንያቱም የኔ ጥናትም ትኩረቱ የወየታና የፉከራ ግጥሞችን ትንተና ማድረግ በመሆኑ ነው፡፡

በአጠቃላይ ቅኝት የተደረገባቸው ከእኔ ጥናታዊ ጽሑፎች ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ተመሳሳይነት ከዚህ በላይ የተገለፀ ሲሆን ልዩነታቸውን ስንመለከት አንዳንዶቹ በለቅሶ ስርዓቱ ላይ ብቻ ያተኩሩ ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ሁለቱንም ማለትም ስርዓቱንና ግጥሞችን አያይዘው የተመለከቱ ሲሆን የተወሰኑት ደግሞ በለቅሶ ግጥሞች ላይ ብቻ አተኩረዋል፡፡ አብዛኛዎቹ ከመንሻቸው ላይ ግጥሙን እንደሚመለከቱ ይገልፁና ወደ ትንተና ሲገቡ በይበልጥ ሰፊውን ቦታ የሚይዘው የለቅሶው ስርዓት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የወጥነት ችግር እንዲታይባቸው አድርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአብዛኛዎቹ መረጃ የተሰበሰበው ከሁለተኛና ሦስተኛ ወገን ነው፡፡

ይህ ጥናት በአንፃሩ ትኩረት ያደረገው የለቅሶው ክዋኔ ምን እንደሚመስልና የወየታና የፉከራ ግጥሞቹ ይዘት ምን እንደሆነ ትንተና በማድረግ ማሳየት ነው። መረጃውም የተሰበሰበው በተሳትፎ ምልከታ፣በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት ነው። እንዲሁም በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በማስደገፍ ነው። በመሆኑም ይህ ጥናት ይሞላቸዋል ተብለው የሚጠበቁ ክፍተቶች አሉ። እነሱም አንደኛ የወየታ ግጥምን አስመልክቶ ካሁን በፊት በትምህርት ክፍሉ ያልተጠና በመሆኑ ስለ ወየታ ግጥም ምንነት በተወሰነም መልኩ ቢሆን መረጃ ይሰጣል። ሁለተኛ የለቅሶ ቃል ግጥሞች የወየታ፣የሙሾና የፉከራ በሚል በሦስት ክፍሎች ተከፍለው መጠናት እንዳለባቸውና በጥቅሉ የሙሾ ግጥም በማለት ለማጥናት መሞከር ተገቢ አለመሆኑን ይጠቁማል። ሦስተኛ በደብረታቦር የለቅሶ ክዋኔው የቆይታ ጊዜው እንዲያጥር በመደረጉ ምክንያት በክዋኔው ላይም ይሁን በቃል ግጥሞቹ ላይ የመለወጥና የመጥፋት አጋጣሚ ስለሚኖር ከወዲሁ ሰብስቦ በሰነድነት ያቆያል።

## 2.2 የንድፈ ሐሳብ ቅኝት

ይህ ጥናት ሞት የሚያስከትለውን ለቅሶ እና ለቅሶው የሚገለፅበት ክዋኔና ቃል ግጥም ላይ በማተኮር የቲዎሪ አቋሞችን ይዳስሳል። ክዋኔ በአንድ አጋጣሚ ከዋኞችን (performers)፣ ታዳሚን (audience)፣ የሚጠናውን ጉዳይ (text)፣የሚተላለፈውን መልዕክት (message)፣ ቅርፅ፣ መቼት፣ እና ሌሎችንም ፎክሎራዊ ጉዳዮች አጣምሮ የሚይዝ በመሆኑ ለዚህ ጥናት የተመረጠው የቲዎሪ አይነት ክዋኔ ተኮር (performance-centered-approach) ነው። የተጠኘው ማህበረሰብ እውቀትና የአጥኚው ግለሰብ እውቀትና ግንዛቤ ሚገናኙበት ድልድይ በመሆኑ ለዚህ ጥናት ያለውን አስፈላጊነት ያጎላዋል። *ክዋኔ ንድፈ ሀሳብ በቡድን ውስጥ እና በውስን አውዶች ያለውን ጥበባዊ ገለፃ ለማጥናትና ለመፍጠር የሚያስችል ዕንለ ሃሳብ ነው በማለት Sims Martha C. እና Martine Stephens ያስረዳሉ (2005፣26-27)።*

> *"The performance approach helped to estabelish the core of the discipline as the study of artistic expression in groups and specific contexts. For folklorists, looking at performance meant the opportunity to expand the understanding of how people create, share, and relate with folklore texts".*

አንድ ቃላዊ ፎክሎር ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፍ መከወን አለበት። የክዋኔ ቲዎሪ ለፎክሎር ጥናት በማንባር ቀደምትነት የሚመረጥ እይታ መስመር ነው። ቲዎሪው ከስነ ጽሑፍና ፎክሎር ተመራማሪዎች ባሻገር ለስነ ልቦና፣ለማህበራዊ ሳይንስ እና ለስነ ልሳን ተመራማሪዎችም እንደሚያስፈልግ Bauman (1992፣43) እንዲህ በማለት ያስረዳሉ። "... other students of language, however, especially, psychologists, sociologists and linguistics anthropologists, are centrally concerned with performance". በማለት የ (performance) ቲዎሪ ለፎክሎር ጥናት ብቻም ሳይሆን ለሌሎቹም የጥናት ዘርፎች አስፈላጊነቱ የጎላ መሆኑን ያሳያሉ።

ስለዚህ የአንድን ማህበረሰብ ማንነት ለማወቅ በአዕምሮው አስቦ በቁሳዊ ሃብቱ በማስደገፍ በእንቅስቃሴው የሚያንፀባርቀውን እውቀቱን በውል ለመረዳት የዚህ ቲዎሪ ሚና ከሁሉም የተሻለ እይታን እንደሚፈጥርና የዘመኑ ተመራጭ የቲዎሪ አይነት መሆኑን ያሳያል። Finnegan (1992፣90) በበኩላቸው የ performance ንድፈ ሃሳብ ለሰው ልጆች እንቅስቃሴ፣ ባህላዊ አስተሳሰቦችና ባህላዊ ክዋኔዎች ቁልፍና ወሳኝ መሆኑን ያስረዳሉ። ለአንድ ክዋኔ መከወን ከሁሉም በፊት ቀድሞ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባው መሠረታዊ ጉዳይ አውድ (context) ነው። Sims Martha C. እና Martine Stephens (2005፣137-138) Dan Ben-Amos ጠቅሰው ሲያስረዱ ሁለት ዓይነት አውዶች አሉ። እነዚህም ሁኔታዊ አውድ (context of situation) እና ባህላዊ አውድ (context of culture) ናቸው። በአንድ በተወሰነ አጋጣሚ ያለውን ክዋኔ የምንመለከትበት ሁኔታዊ አውድ ሲባል ባህላዊ አውድ ደግሞ ሰፊ እና በውስጡም ከማህበራዊ ባህላዊ አስተሳሰቦች አንስቶ እስከ እምነት ድረስ ያለውን ክዋኔ ያጠቃልላል። ከዚህም የምንረዳው ሁኔታዊ አውድና ባህላዊ አውድ ለክዋኔ (performance) መሰረታዊ መሆናቸውን ነው።

Hufford (1995፣529) ደግሞ የአንድ ማህበረሰብ የጋራ እውቀት፣ የአናናር ዘዬ፣የቋንቋና የእምነት የግንዛቤ ደረጃ፣ስለታሪካዊ እውቀታቸውና ሥነ ምግባራዊ ደንብ ያላቸው ግንዛቤና እውቀት በባህላዊ አውድ (context of culture) ይታያሉ። ፎክሎራዊ እውቀት ወይም ጥበብ የሚገለፀው በክዋኔ ነው ከመገለጫዎቹ አንዱ ቃል ግጥሞች ናቸው።ከዋኞች ሥሜታቸውንና ፍላጎታቸውን ከመግለፅ ባሻገር አካባቢያቸውን እንዲያውቁ ያስችላቸዋል በማት ይገልጻሉ ። በሌላ በኩል ደግሞ Hufford ሁኔታዊ አውድን "context of situation)ን ሲያብራሩ context of situation as the narrowest, most direct context for speaking

folklore"(1995፣529)። ሁኔታዊ አውድን በተመለከተ ከባህላዊ አውድ አንፃር ሲታይ ጠባብ ነው ይላሉ። ምክንያቱም ሁኔታዊ አውድ ብዙ ጊዜ በግለሰቦች መካከል ባልተጠበቀ ጊዜና ስፍራ የሚፈጠር ድንገቴ ክዋኔ ነው። በዚህ ክዋኔ የተሳታፊው ቁጥርም አነስተኛ ከመሆኑም በተጨማሪ የጎላ ተሳትፎ አያደርግም።

ባህላዊ አውድን መሰረት ያደረጉት አብዛኛዎቹ ክዋኔዎች ግን ማህበረሰቡ ቀድሞ አውቋቸው የመከወኛ ጊዜና ስፍራቸው ተለይቶ የሚከወኑ ሲሆን የታዳሚው ተሳትፎም ከፍተኛ ነው። ለምሳሌ-ለቅሶን ስንመለከት ሟች ነፍሱ የሚወጣበት ቅፅበት ድንገቴ (situational) ሲሆን ከዚህ በኋላ ግን ለቅሶ የሚለው ቃል ሲነሳ በማንኛውም ሰው አዕምሮ ውስጥ ቀድሞ የሚመጣው አሳዛኝነቱ እና የአከዋወን ሂደቱ ነው። በመሆኑም ስለ ለቅሶ ምንነት ማንኛውም ሰው በቀላሉ ይረዳል። ነገር ግን የአንዱ ለቅሶ ከሌላው ለቅሶ የሚለየው በክዋኔው ሲሆን ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ በሰዎች መካከል በሚፈጠር የማህበራዊ ደረጃ ልዩነት ነው።

## 2.3 ክዋኔ

*"ክዋኔ የሚለው ቃል በአጠቃላይ ሥነ ቃሉ የሚነገርበትን አውድ ወይም አካባቢ ከድርጊት ጋር አያይዞ የሚያመለክት ነው"* Okpewho *(1992፣16)* በማለት አንድ ሥነ ቃል ከመከወኑ በፊት የሚከወንበት አውድና የሚያስተላልፈው መልዕክት እና ሌሎችም ለክዋኔው አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ሁሉ ለክዋኔው ውጤታማነት ሚዛን እንደሚደፉ ያሳያሉ። በአንድ ክዋኔ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ እና አስፈላጊ የሆኑ ነጥቦች አሉ። ከነዚህ መሃከልም ዓውድ (ከዋኝ፣ ታዳሚ፣ መቼት፣ ቅርፅ፣ መልዕክት እና አስተያየቶች) ዋነኞች ናቸው።

ክዋኔ በከዋኙ የግል ችሎታ፣ በሥነቃሉ መክሰቻ እና በባህሉ ውስጥ ባለው ተቀባይነት ላይ የተመሰረተ ነው። ይህን አስመልክቶ *Bauman (1988፣3) የቃል ክዋኔ ልክ እንደማንኛውም የሰው ልጅ ችሎታ ሁሉ የክወናው ዓይነት፣ ትርጉምና አገልግሎት በባህሉ ከተደነገገው ሥርዓትና ክስተት ቅደም ተከተል ጋጠመኝ ተመርኩዞ ለድርጊቱ፣ለትንተናውና ለምዘናው በተሰጠው አውዳዊ ትርጓሜ መሰረት የተካተተ ነው ይላሉ።*

ከዋኝ የክዋኔ አብይ አላባውያን ከሚባሉት መሃከል አንደኛው ነው። ከዋኙ የበቀለበት እና ያደገበት ማህበረሰብ ማንነት፣ ማህበራዊ ደረጃው፣ ዕድሜው፣ የአነጋገር ወይም የአገላለፅ እና የአከዋወን ብቃቱ፣ የመድረክ እና የታዳሚ አያያዝ ችሎታው፣ የፈጠራ እና የአቀራረብ

ክህሎቱ ሁሉ በክዋኔው ላይ ለሚመጣ አስተያየት፣ አድናቆት፣ ስምረት እና ውድቀት የማይናቅ ድርሻ አለው። ከዚህም ሌላ ከዚህ በፊት የነበረው ልምድ እና ችሎታ፣ የመሪነትና የከዋኝነት ኃላፊነቱን የመወጣት አቅሙ፣ ከዚህ በፊት በዘርፉ ያለው ተቀባይነት እና ዝና፣ ፆታው፣ የማህበራዊ ህይወቱ ሁኔታ ሁሉ በክዋኔው ላይ ጉልህ ሚና ይኖረዋል። Finnegan (1992፣90) ይህንን የከዋኝ ባህሪይ እንደሚከተለው ይገልፁታል፦

> *"How performers carry out their roles relying mainly on words and gestures, or also plotting music or dance or; purporting to deliver works by others human or super natural creative or other wise in the sense of composing during or before performance".*

በክዋኔ ወቅት የከዋኝ እና ታዳሚ ሚና እንደ ክዋኔው እና እንደክበራው ዓይነት የተለያየ ይሆናል። Finnegan ይህንን መሠረት በማድረግ ስድስት ዓይነት የከዋኝና የታዳሚ ሚናዎችን የሚወስኑ የክበራ ነጥቦችን ይዘረዝራሉ። የመጀመሪያው በከዋኝና ታዳሚ መሃከል ግልፅ የሆነ የሚና ልዩነትን የሚፈጥር የክዋኔ አይነት ነው። ሁለተኛው ከዋኝ እና ታዳሚ በመጠኑ የሚለያዩበትን ሚና የሚፈጥር ነው። ለዚህ ማሳያ የሚሆነን አንድ ተረት በሚከወንበት ወቅት ተራች የራሱ ሚና አለው። አድማጭም እንዲሁ። ይሁን እንጅ አድማጭ አልፎ አልፎ መልሶችን ይሰጣል። በለቅሶ ላይም አንድ ፎካሪ በቅሉ ላይ ወጥቶ እየፎከረ ታዳሚው እውነት እያለ ካልተቀበለውና ምስክርነቱን ካልሰጠው ፎካሪው ፋከራውን አይቀጥልም። በተለይም ይህ ሁኔታ የሚከሰተው ገጣሚዎቹ ሟች ከሚኖርበት አካባቢና ማህበረሰብ ራቅ ብለው የመጡ እና የማህበረሰቡን ማንነት በውል የማያውቁ ከሆኑ፣ ይህም በፎካሪዎቹ ከተገለፀ ተቀባይ አለመኖር ብቻ አይደለም፣ ሊቃወሙም ይችላሉ።

መሳቅ፣ ማዘን፣ መደመም፣ ማልቀስ... በዚህ የተነሳም የከዋኝ አንዳንድ ድርጊቶች ሊሻሻሉ እና ሊስተካከሉ ይችላሉ። ይህን የከዋኝ የፈጠራ ችሎታ መጠየቁ የማይዘነጋ ነው። ይህ ደግሞ የሚታየው በክዋኔው ላይ የታዳሚን ስሜት በመግዛትና ታዳሚው በሚሰጠው ምላሽ ነው። የታዳሚው ንቁ ተሳታፊነት እና ኢ-ንቁ ተሳታፊነት የሚገለፀው ወይም የገጣሚዎች ችሎታ የሚታየው በዚህ የክዋኔ አጋጣሚ ነው። ሌላኛው የሚና ልዩነት ደግሞ በሆነ ሁኔታ የተለያዩ ነገር ግን በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ሁለቱም ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉበት ነው።

አራተኛው ነጥብ በአንዳንድ ቦታዎች እና አጋጣሚዎች ላይ የታዳሚን ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቁ ሁኔታዎችን ይመለከታል። ያለ ታዳሚ ንቁ ተሳትፎ ክዋኔው ሊቀጥል የማይችልበትን አጋጣሚ አለ። ለምሳሌ ተራች "ተረት ተረት" ሲል ታዳሚ "የላምበረት" በማለት እና ፈቃደኝነቱን ካላረጋገጠ ክዋኔው ሊቀጥል አይችልም። ቀጣዩ የሚና ልዩነት የለም ሊባል በሚያስችል ሁኔታ በጣም ውስን ልዩነት የሚያመጣ ነው። ለዚህ ማሳያ የሚሆነው የህብረ ዝማሬ መዝሙር ነው። በብዛት ሁሉም በአንድነት የሚለው ቢሆንም አንዳንዱ የሚቀባበል ነገር አይጠፋውም። የመጨረሻው ነጥብ ደግሞ በሁለቱ መሃከል ምንም ልዩነት የማያመጣ እና ሁለቱንም አንድ የሚያደርግ የሚና ክፍፍል የሌለበት ነው። ለዚህ ማሳያ የስራ ላይ ዘፈን ነው። ሁሉም በጋራ እየዘፈነ ስራውን ያሳልጣል። በለቅሶ ክዋኔ ላይም ከዋኙ የምንለው ግጥም ደርዳሪውን ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ግጥም ደርዳሪው በወኔና በሞራል ይገጥም ዘንድ ለሱ ሀይልና ሞራል የሚሆነውና ለፋከራ የሚያነሳሳው የአልቃሹ የሃዘን ደረጃ ከፍተኛ መሆንና ዝምበሉ እየተባለ ስሜቱን መቋቋም ተስኖት የሚያደርገው መውደቅ መነሳት አጋዥነቱን፣ፈቃደኛነቱን በማሳየቱ ለፎካሪው ጉልበት ይሆነዋል። ለዚህ ደግሞ በዋንኛነት የሚነሳው የሟች ማህበራዊ ደረጃ የአልቃሹንም ሆነ የፎካሪውን የስሜት ሚዛን እንዲያጋድልና ልዩነት እንዲኖር ያደርገዋል። ይሁን እንጅ በክዋኔው ላይ የሁሉም ሚና ተመሳሳይ መሆኑን ያሳየናል።

አንድ ክዋኔ በውስጡ በቃልም ሆነ በድርጊት የሚተላለፍ በርካታ መልዕክቶችን ሊይዝ ይችላል። ይህ እንዲህ እንዲሆን ሁለት ዓበይት ፍሬ ነገሮች ይነሳሉ። እነዚህም የሚተላለፈው መልዕክት ቅርፅ እና የሚተላለፍበት ቅጥ ናቸው። የቃላዊ ክዋኔ ቅርፅ በዝርው ሊሆን ይችላል። በግጥም መልክ ሊሆን ይችላል፣ ከዜማ ተዋህዶ በግጥም ሊቀርብ ይችላል። በቃል ሲባልም ከላይ እንደተጠቀሰው በዜማ፣ በድምፅ ከፍታና ዝቅታ ተቀናብሮ ሊቀርብ ይችላል።

በሌላ በኩል ደግሞ በተግባር በልዩ ልዩ እንቅስቃሴ፣ የፊት ገፅታ በመቀያየር፣ አለባበስን እና አጊያጊያጥን በመቀያየርና በቁሳቁሶች በመታጀብ ማስተላለፍ ይቻላል። በቅሎ ላይ ሆኖ የሚፎክር ፎካሪ በስሜት በቅሎው ላይ እርካብ ረግጦ ይቆማል። ወዲያና ወዲህ መንቆራጠጥና አንገትን ማወዛወዝ፣ ወደ ኋላና ወደ ላይ መንጠራራት ግጥሞቹ ከሚያስተላልፉት መልዕክት በተጨማሪ በአካላዊ እንቅስቃሴ የሚገለፀው ስሜት ከፍተኛ በመሆኑ የፎካሪውን ክዋኔያዊነት ጠቀሜታ አጉልቶ ያሳያል። ከዚህም በመነሳት አጥኚው

አጠቃላይ የማህበረሰቡን ስሜት፣ አስተሳሰብና ፍላጐት እንዲሁም ማንነቱንና እውቀቱን መረዳት ይቻለዋል።

ከዋኙ ቃል ግጥምን ወይም ሥነ ቃልን ለመድረስ ወይም ለመፍጠር ምቹ ነው። ምክንያቱም ከዋኙ ከዚህ ቀደም የሚያውቀውን እየከወነ እያለ እዚያው ክዋኔው ላይ ያየውን ወይም ከሁኔታው ጋር አብሮ ሊሄድ የሚችለውን፣ ከአውዱ ጋር የሚሥማማው እና ለታዳሚው የሚስብ ቃል ግጥም ይደርሳል። የቃል ግጥሙ ከዋኝ ሥሜትም በማህበረሰቡ ስሜት እና ፍላጎት እንዲሁም በአጠቃላይ ለአውዱ ሥርአት የተገዛ ነው። ማንኛውም ሰው በወቅቱ የሚከወኑት ቃል ግጥሞች በሚያሳድሩበት የመነሳሳትና ሥሜትን በድፍረት የመግለጽ ሁኔታ እንኳን ቢፈጠር ከአጠቃላዩ አውዳዊ ሥርዓት አይወጣም። ይህን ደግሞ አውዱ የበቀለበት ማህበረሰብ ማንነት ይወስነዋል። ያ አውዳዊ ማንነት ነው የተለያዩ አጋጣሚዎችን መሰረት በማድረግ በቃል ግጥም አማካይነት እየወጣ ለተደራሲያን ጆሮ በመድረስ ተደራሲያን ደግሞ ለአዕምሮአቸው እና ለሥሜታቸው እንደተረዳቸው ወይም እንደተገነዘቡት ነው ምላሽ የሚሰጡት።

ስለዚህ አንድን የሥነ ቃል አይነት ጭብጡን በሚገባ ተረድቶ በሚገባ ትንታኔ ለመስጠትም ሆነ ይዘቱን ለመረዳት የክዋኔ አስፈላጊነት ከፍተኛ ነው። ክዋኔ ሲባልም ከዋኙ በቃል የሚያደረገው ዜማዊ ክዋኔ ብቻ ሳይሆን የከዋኙ አካላዊ እንቅስቃሴ፣ የታዳሚው አቀባበል፣ ክዋኔው የሚከወንበት ወቅትና የአካባቢው ድባብ ሁሉ የአንድ ክዋኔ አብይ ጉዳዮች ናቸው። በለቅሶ ላይም የሚታዩት የወየታና የቆዘራ ግጥሞች ሲደረደሩ ታዳሚው እውነት ነው፣ እንዲያበል እያለ በድምፅ ከሚያደርገው ተሳትፎ በተጨማሪ ቁጭ ብድግ እያለና ከወዲያ ወዲህ እየተንቆራጠጠ የሚያደርገው እንቅስቃሴ የዚሁ መገለጫዎች ናቸ ው።

## 2.4 ለቅሶ

ሞት ከሚያስከትላቸው ጠንካራ ስሜቶች መሃከል ዋነኛው ሃዘን ነው። አብዛኛውን ጊዜ የሃዘን መግለጫ ተደርጎ የሚወሰደው ደግሞ ለቅሶ ነው። የለቅሶን ትርጉም ስንመለከት ኪዳን ወልድ ክፍሌ (1948፣269) በመዝገበ ቃላታቸው ውስጥ "በክይ፣ ዩት፣ (በለየ፣ ይበኪ፡1 ዕብ በካ፡ ስር ብካ። ዐረ በበ)፣ ማልቀስ፣ እንባ ማፍሰስ፣ ዋይ ማለት መጮህ፣ መንሰቅሰቅ" በሚል ይተረጉሙታል።

ቀጥለውም ማልቀስን ከማዘን፣ ከመጨነቅ እና እንባ ከማፈሰስ ጋር አያይዘው ይገልፁታል። ይህውም ማልቀስን እና ለቅሶን ከስሜት መለወጥ ጋር ተያይዞ የሚመጣ እንደሆነ ያሳያል። "we all believe we know that death is because it is a familiar event and one that arouses in tense emotion" (Hertz፣ 1960፣27) በማለት ሞት አብሮን የኖረ እና የተለመደ ቢሆንም ሁሉም ከፍተኛ የሆነ የሃዘን ስሜትን እንደሚያጭር ይገልፃሉ። በሃገራችን እና በሌሎችም የዓለም ክፍሎች ባህል ውስጥ እንደምንመለከተው ሞት ብዙውን ጊዜ ሀዘንን ያስከትላል። ሀዘንም እንደዚሁ ለቅሶን ያመጣል። ለቅሶ ደግሞ በተለያየ መልኩ ይገለፃል። የለቅሶ መገለጫው ደግሞ በቃል ግጥሙ፣ በክዋኔውና በልዩ ልዩ ስርዓቶች መታጀቡ ነው። በዋነኛነት የለቅሰው ጎልቶ መታያ እና የሟች ግብረ መገለጫ እንዲሁም የማህበረሰቡ እሴት እና ማንነት ማሳያ ሆኖ የሚቀረበው የሰው ልጆችን ሁለተናዊ እውቀትን አካቶ በያዘው ፎክሎር፣ የዚህ ሰፊ የጥናት ዘርፍ አንዱ ክፍል በሆነው ሥነ-ቃል፣በዚህ ሥር በሚገኘው ቃል ግጥም፣ ማለትም በሙሾ፣በወየታ እና በቆዘራ ግጥሞች አማካይነት ይገለፃል። ለቅሶ ሞትን ተከትሎ የሚመጣ እራሱን የቻለ እውድ ሲሆን ሥርዓቱን ጨምሮ እነዚህ ሙሾ፣ወየታ እና ቆዘራ የዚህ ለቅሶ ማሳያዎች ናቸው። በዚህ ጥናት ይበልጥ ትኩረት የተደረገባቸውም ለቅሶን አጋጣሚ በማድረግ የሚደረደሩት ቃል ግጥሞች ላይ ነው።

## 2.5 ቃል ግጥም

ቃል ግጥም በሰው ልጅ ህይወት የዕለት ተዕለት የኑሮ ውጣ ውረድ ውስጥ የሰው ልጆችን ስሜት የሚገልፅ የስነ ቃል አይነት ነው። የአንድን ማህበረሰብ ማንነት ሊያሳይ ይችላል። በቃል እየተደረሰ፣ በቃል እየተባለ እና በቃል እየተከወነ የዘመን አሻራን ከትውልድ ትውልድ ከዘመን ዘመን ሲያሸጋግር ቆይቷል። በዚህም የተነሳ ቃል ግጥም ማህበረሰቡ የወደደውን፣ የጠላውን፣ ያገኘውን፣ ያጣውን፣የሚያደርገውን፣ እንዲደረግለት የሚፈልገውን፣ ያጠቃልላል። ቃል ግጥም የትላንቱን፣ የዛሬውን እና የነገውን እንዲሁም በአጠቃላይ የትውልድን የማንነት ሽግግር የሚያሳይ በመሆኑ የሰው ልጆች ሁለንተናዊ ሀብት ነው ማለት ይቻላል።

የቃል ግጥም ዋና መለያ የሆነው ቃላዊነቱ እና በቃል መከወኑ ብቻ ሳይሆን ይልቁንም በዜማ ተውቦ ለስሜት አዝናኝና መሳጭ በሆነ መልኩ ለታዳሚ ጆሮ የሚደርስ መሆኑ ነው። እንዲሁም በትብብሉሽ የሚከወንና ቡድናዊ በመሆኑም የህዝብ ሃብት ነው።

ቃል ግጥም የቃል የሚያስብለውም ሲደርስ በቃል ከተደረሰም በኋላ ለተደራሲያኑ በቀጥታ የሚደርሰውም በቃል ነው። ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ የሚሰራጨውም በቃል በመሆኑ ቃል ግጥምን ቃል ግጥም የሚያስብለው አንድ ቃል ግጥም ይበልጥ የቃል የሚያሰኘው አደራረሱ፣ የመተላለፊያ መንገዱ፣ከመተላለፊያ ዘዴው ጋር ተያይዞ የሚመጣው ከዋኔው መሠረት በማድረጉ ነው።

ቃል ግጥሞች ምንነት ሲነሳ የአፈጣጠራቸው (composition) ጉዳይ ይነሳል። ይህውም ማን እንደሚፈጥራቸውና እንዴት እንደሚፈጠሩ ማወቅ ተገቢ ነው። ይህን አስመልክቶ *Dorson (1972፣88) ሲያስረዱ "ቃል ግጥም ወይም ህዝባዊ ግጥም (folk poetry) በታወቁና የተለየ ችሎታ ባላቸው ሰዎች የሚፈጠር እና ለተደራሲያን የሚተላለፍ ነው" ይላሉ።*

ይህም የሚያሳየው ቃል ግጥም የሁሉም ወይም የህዝብ ሃብት ቢሆንም ሁሉም ሰዎች ደግሞ ቃል ግጥምን መፍጠር የማይቻላቸው መሆኑን ነው። ከማህበረሰቡ ውስጥ ቃል ግጥምን መፍጠር ወይም መከወን የሚችሉት ልዩ ችሎታ ያላቸው ሰዎች መሆናቸውን ያሳያል። ነገር ግን ሁሉም ቃል ግጥምን መፍጠር ባለመቻሉ የቃል ግጥሙ ባለቤት አይሆንም ማለት አይደለም። ሁሉም ቃል ግጥሞች ሃብትነታቸው የህዝብ ነው። ሁሉም ሰው መፍጠር ላይጠበቅበት ይችላል። በከዋኔያቸው ላይ ንቁ ተሳታፊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በፈለገው ሰዓትና ስፍራ ስሜቱንና ፍላጎቱን ስለሚገልፅባቸው እንዲሁም እንደ ችሎታውና እንደ አውዱ ሁኔታ ስለ ሚያሻሽላቸው ሃብትነታቸው የህዝብ እንጅ የግለሰብ አይሆንም።

በዚህ ጥናት ውስጥም የወዮታና የቆከራ ግጥሞችን ስንመለከት የሚገጥሟቸው ግለሰቦች ከአብዛኛው ማህበረሰብ የተለዩና በዚህ ችሎታቸውም ገንዘብ እየተከፈላቸው ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ከአውዱ ጋር እያስማሙ ግጥሞችን መግጠም የሚችሉ ናቸው። አብዛኛው አልቃሽ ደግሞ እውነት ነው፣እንዲያበል፣ በማለት ተሳታፊ ይሆናል። ምን አልባት በአንድ ከዋኔ ላይ ግጥም ደርዳሪው ግጥሞችን እየደረደረ ተቀባይ ባይኖረው ወይም ሁሉም ዝም ቢል ከዋኔው ላይቀጥል ይችላል። ምክንያቱም በአንድ የፎክሎር ክዋኔ ላይ የታዳሚ ተሳትፎ ጉልህ ድርሻ ያለው በመሆኑ፣ ሁሉም አልቃሽ ግን ግጥም ገጣሚ አይደለም። ግጥሞቹ በሚያሳድሩበት ተፅዕኖ ምክንያት እንደፈለገ ሊምህና አስደንጋጭ አካላዊ እንቅስቃሴም ሊያደርግ ይችላል። እነዚህን ጉዳዮች መሠረት አድርጉ ቃል ግጥም ከጽሑፋዊ ግጥም የተለየ ስሜትን የመፍጠር ኃይል አለው።

ይህን አስመልክቶ Finnegan በሥነ ቃል እና በሥነ ጽሑፍ መካከል ግልፅ የሆነ ድንበር እንደሌለው ይገልፃሉ። (1997፣2) ቃል ግጥም በግለሰቦች ተደርሶና በወረቀት ላይ ሰፍሮ ከሚገኘው ግጥም የተለየ መሆኑን እና ከሥነ ቃል ዓይነቶች አንዱ መሆኑን ጭምር ሲያስረዱ፡-

*"... ቃል ግጥምን ከጽሑፋዊ ግጥም ለመለየትና ድንበር ለማበጀት "ቃል" የሚለው ስያሜ ብቻ በቂ ነው። በመሆኑም ቃል ግጥም ከጽሑፋዊ ግጥም ጋር ሲነፃፀር አደራረሱ፣ አስረጫጨቱ እና ክዋኔው በጽሑፍ ላይ ካለው ጥገኛ ሳይሆን በአንደበት ወይም በንግግር ላይ የተመሰረተ ነው። በዚህ የተነሳም ቃል ግጥም ከስነ ቃል ዓይነቶች አንዱ ነው (1997፣16)" ይላሉ።*

በመሆኑም ቃል ግጥም በተወሰነ የመከወኛ ቦታ እና ወቅት በከዋኙ አማካይነት ተደርሶ ከዚያው የሚከወን እንዲሁም ክዋኔውን ለማጀብ፣ ለማድመቅ ወይም በክዋኔው ለመሳተፍ ለሚመጡ ተደራሲያን የሚቀርብ ነው። በዚያውም እግረ መንገዱን በከወናው ወቅት ለተደራሲው ሲደርስ ስርጭቱም በታዳሚዎች አማካይነት ይሆናል።

ስለዚህ ቃል ግጥም ከጽሑፋዊ ግጥም በአደራረሱ፣ በአካዋወኑ፣ በተስተላልፎውና በስርጭቱ የተለያየ ነው። ስለሆነም ቃል ግጥም በባህሪውም ከጽሑፋዊ ግጥም ይልቅ ከስነ ቃል ጋር አንድ አይነት የሆነ የጋራ ባህርይ እንዳላቸው መረዳት አያዳግትም። ምክንያቱም ቃል ግጥም ሲነሳ ሰፋ ወዳለው ስነ ቃል እና በርከት ነገሮችን አካቶ ወደያዘው ፎክሎር ማምራቱ አይቀርም። ይህ ደግሞ የፎክሎርን ዘርፈ ብዙነትን ያሳያል። ይህ የፎክሎር ዘርፈ ብዙነት የሚገለፀው በክዋኔው እና በእያንዳንዱ ዘርፍ በሚታየው ተግባር እና በሚሰጠው ጠቀሜታ ነው። ይህን አስመልክቶ Finnegan (1977፣125) የሚከተለውን አስፍረዋል፡-

*There are also conventions about the appropriate occasions for oral poetry. These vary according to local cultural conventions, but common ones include social occasions when people are relaxing and free of work (perhaps the most common setting for length and specialized verse); work contexts in which poetry (often music) accompanies such tasks as holing, paddling, grinding, or rocking a baby, religious rituals; and the celebration of recognized*

*ceremonial points such as harvest enthronement, intiation, marriage, or death.*

በማለት የቃል ግጥምን በተመለከተ የጋራ የሆነ ስምምነት ቢኖርም ከቦታቦታ፣ ከባህል ባህል፣ እንደየማህበረሰቡ የማንነት ሁኔታ የሚለያዩበት አጋጣሚ አለ፡፡ በተጨማሪ የቃል ግጥሞችን አስፈላጊነት እና ይህን ሚናቸውን ተከትሎ የሚከወኑበትን አውድ (context) ይጠቁማሉ፡፡ ለምሳሌ ሰዎች ቃል ግጥምን በህብረት በሚሰሩበት ጊዜ ለስራ ማሳለጫ፣ በርሻ ቦታ፣ ሴቶች እህል በሚፈጩበት ጊዜ፣ በሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት፣ በሰርግ፣ በለቅሶ፣ በልጅ ማጫወት እና በሌሎችም ክዋኔዎች ጊዜ የሰው ልጆች በግልም ይሁን በቡድን በሚያደርጉት ማህበራዊ መስተጋብር ላይ ድካምን ወይም ድብርትን በማስወገድ የደስታ ስሜትን በመፍጠርና በማዝናናት የተጀመረን ክዋኔ በጥሩ ሞራልና መነሳሳት መፈፀም ማስቻል ነው፡፡ ይህ ደግሞ እንደየ አውዳዊ ክዋኔው የራሱ የሆነ ጠቀሜታ አለው፡፡

ይህ የ Finneganን ሃሳብ ከዚህ ጥናት የትኩረት አቅጣጫ አንፃር ሲታይ በለቅሶ ወቅት የሚገጠሙ የወኖታና የቆዘራ ግጥሞችም አውዱን ወይም የዕለቱን ክዋኔ መሰረት ያደረጉ ተግባራት አሏቸው፡፡ በስራ ወቅት ድካምን በማስወገድ የስራ ተነሳሽነትን እንደሚፈጥሩ ሁሉ በለቅሶ ወቅትም የወኖታና የቆዘራ ግጥሞችን በመሃል እያፈራረቁ በመከወን አልቃሽ ከገባበት ድካም ወጣ ብሎ ትንፋሽ እንዲወስድ እና እንዲያርፍ በማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡ በተለይም የቆዘራ ግጥሞች ሲገጠሙ በሁሉም አልቃሽ ዘንድ የሚፈጠር የጀግንነት ወኔ እና ተነሳሽነት ከፍተኛ ነው፡፡ ይህን የለቅሶን አጋጣሚ መነሻ በማድረግ የሚገጠሙ ቃል ግጥሞችን፣ እነዚህን ቃል ግጥሞች መሠረት አድርጎ የሚፈጠረው ስሜት እና አጠቃላይ ስርዓቱ ተጨምሮ የሚታየው መስተጋብር የዚያን ማህበረሰብ ፎክሎራዊ እውቀት ወይም ጥበብ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፡፡

ፎክሎር ከሚያጠቃልላቸው ጉዳዮች ውስጥ ስነ ቃል ሲሆን ስነ ቃል በስሩ አካቶ ከሚይዛቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ደግሞ ቃል ግጥም ነው፡፡ በአጠቃላይ ቃል ግጥም ሲነሳ የደራሲው አለመታወቅ፣ ሲከወን ሌሎችንም ተሳታፊዎች መጨመሩ፣ ስርጭቱ በቃል አማካይነት መሆኑ፣ ቃል ግጥም የሥነ ቃል አንዱ አካል መሆኑንና የጋራ ባህሪይ ያላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም በ "ሥነ ቃል ላይ የሚታየው ክዋኔያዊነት ተለዋዋጭነት እና ድግግሞሽ ባህሪያት በቃል ግጥም ላይም እንደሚከሰት" (ዘሪሁን አስፋው፣ 1998፣22) ያስረዳሉ፡፡

## 2.6 ሙሾ

ሙሾ የሰውን ልጅ ሞት ተከትለው ከሚመጡት የለቅሶ መገለጫዎች አንዱ ነው፡፡ የሟች ወገን ዘመድ ፊቱን ነጭቶ፣ፀጉሩን ተላጭቶ፣ደረቱን ደልቆ ወድቆ ተነስቶና አይሆኑ ሆኖ ሃዘኑን የሚገለፅበት ነው። ደስታ ተክለወልድ ሙሾን ሲገልፁት፡-

*ሙሾ፣ "(ስቆቃው)፣ የለቅሶ፣ ቅንቀና፣ ዥመራ፣ ግጥም ፣ዜማ፣ቁዘማ፣እንጉርጉሮ፣ ረገዳ ፣ጭብጨባ ያለበት" (1962፣1016)፡፡*

በማለት መዝገበ ቃላዊ ፍችውን ያስቀምጣሉ። ከዚህም የምንረዳው የሟች ቤተዘመድም ይሁን አልቃሽ የሃዘን ስሜቱን የሚገልፅበት መንገድ መሆኑን እና የሃዘኑን መራርነት የሚያሳዩ ሰቆቃው መሆኑን ነው። ከዚህ ተጨማሪ የሙሾን ምንነት በሚመለከት ከመረጃ ሰጭዎች ውስጥ (አቶ ታከለ ንጋቱ) የሚከተለውን ነግረውኛል፡-



ምስል 1፡ አየኘው ከፎካሬ ታከለ ንጋቱ ጋር ሙሾን አስመልክቶ ቃለ መጠይቅ ሲያካሂድ

*ሙሾ፡[1] ሙሾ የሚደረገው አብዛኛውን ሰው ተሳታፊ ለማድረግና ሃዘንተኛውን ለማፅናናት ነው። በዚህ ጊዜ ወንዶች ብቻ በአራት ማዕዘን ተሰልፈው ይቆማሉ፡፡ ሦስት ሰዎች መሀከል ይገቡና እጅ ለእጅ ተያይዘው አንድ ጊዜ ወደዚህ አንድ*

---

[1] አቶ ተሾመ ጨሰቴ፣ አቶ አስምላው አሰፋ፣ አቶ በሪሁን መንግስቱ ተሻገር፣ አቶ ሀብታሙ ሙጨ፣ አቶ አርቅይሁን ወሂደ፣ አቶ ባለው መለስ፣ አቶ እንዳ ወሰለም፣ አቶ አብርሃም ዘለቀ እና አቶ መንፍንት ጫኔው 20/05/2004 በተደረገው ቃለ መጠይቅ ሙሾን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ሰጥተውኛል።

*ጊዜ ወደዚያ በመዞር በጋራ ሙሾ ያወርዳሉ፡፡ ሙሾ ለሟች ብቻ አይደለም የሚወርደው ለመላው የሰው ልጅ ነው፡፡ የሙሾ ክፋቱ ፈጣሪን ይነካል፣ ያማርራል፡፡ ለምሳሌ፡- "እበባ ብንሆን ብንመስል ጨረቃ አወይ የሰው ነገር ተመልሶ ጭቃ" በማለት የሟች ስም ሳይጠራ ይደረደራል፡፡ ሙሾ በአንድ ለቅሶ ክዋኔ ሦስት ጊዜ የሚደረግ ሲሆን መጀመሪያ ከማልቀሻው ቦታ እንደተደረሰ፣ቀጥሎ መሀከል ላይ ሃዘንተኛውን ለማሳረፍ በመጨረሻም ወደ ቀብር ሊሄድ ሲል "ዋይ፣ዋይ፣ተሲያየን ወይ" በማለት የመሰነባበቻ ሙሾ ይደረጋል፣ (20/05/2004) ዓ.ም፡፡*

ከዚህም የምንረዳው ሙሾ ለማንኛውም የሰው ልጆች ሁሉ የሚደረደርና የፆታም ይሁን የዕድሜ ልዩነት እንደማይደረግበት ነው፡፡ በዚህ የሙሾ ዜማ አማካይነት የሚፈጠረው ሥሜት በአብዛኛው በዕለቱ ከሞተው ግለሰብ ሃዘን የተለየና ከፍ ያለ ነው፡፡ ምክንያቱም በዚያ ሰዓት የሟቹ ስም አይጠራም ነገር ግን በአጠቃላይ ሰው ሆኖ የመፈጠር እና የሰውን ልጅ ከንቱነት ማንኛውም ሰው በዕዝነ ልቦናው እንዲያስበው እና እንዲያዝን የማድረግ ስሜት ያለው ነው፡፡

ይህ መሪር ሃዘን ደግሞ የሚያሳየው ሰው ሆይ  እንዲህ በቀላሉ አፈር መሆን ስላለ በምድር ላይ ስንኖር ክፉ ሥራን አናድርግ፣ እንተዛዘን፣እንረዳዳ በማለት ለምድራዊ ኑሯችን ከምንገነባ ለላይኛው ቤታችን እንትጋ፣ ፈጣሪያችን እናስብ፣የሚልና ሞት የሚባለው ነገር በድንገት የሚመጣ በመሆኑ ተዘጋጅተን እንጠብቅ የሚል ይዘት አለው፡፡ የዚህ ሙሾ ግጥም መደርደርና የሰው ልጅን ከንቱነት ማሳየቱ ለማህበረሰቡ ያለው ጠቀሜታ ሞትን፣ ከንቱነትን እና ሳያስበው አንድ ቀን ሊለይ እንደሚችል በማሳየት እንዳይረበሽ፣ እንዳይጨነቅ የሞትን ከሰው ልጆች መፈጠር ጋር በማያያዝ ህይወትና ሞት አብረው ጎንለጎን መኖራቸውን በተነፃፃሪነት በማሳየት ከሞት በኋላ ያለው ህይወት ሚዛን እንደሚደፋ ያሳያል፡፡

ነገር ግን አጥኚው በተከታተላቸው የለቅሶ ክዋኔዎች ውስጥ ሙሾ ሲደረግ አልተመለከትኩም፡፡ ለዚህ እንደምክንያት የተቀመጠው በቃለ መጠይቅ ወቅት በተገኘው መረጃ መሰረት ቶከራ በሚደረግባቸው ታላላቅ ለቅሶዎች የጊዜ እጥረት ስለሚኖር ሙሾ አይኖርም በማለት ያስረዳሉ፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜም እየቀነሰ መምጣቱን ጭምር ይገልፃሉ፡፡

## 2.7 ወየታ

በደስታ ተክለወልድ አገላለፅ ወየታ፣ ማለት ዋይታ፡ ለቅሶ" ሲሆን "ወይ ማለት ደግሞ፡ ዐዘነ፡ ተከዘ፡ ቆዘመ፡ ተወዛወዘ፡ አለቀሰ፡ አነባ" ማለት ነው:: በሌላኛው ላይ ደግሞ (ወይ ወዩ ዋይ)፣ ሰው፡ ከሞተ፡ በኋላ፡ ወይም፡ በመርዶ፡ ጊዜ፡ መዠመሪያ፡ የሚደረግ፡ ዋይታ፣ ጩኸት፣ ቁቁታ:: (ደስታ ተክለወልድ ፤1962፤ 430-469)::

ይህ አገላለፅ የሰው ልጅ የገጠመውን መሪር ሃዘን የሚገልፅበት መንገድ መሆኑን ያሳያል። ወየታ በለቅሶ ወቅት ሲገለፅ ዘርፈ ብዙ ነው:: ምክንያቱም በለቅሶ ሰዓት አንገት ላንገት ተናንቆ የሟችን ስም እያነሳ ወይኔ፣ወይኔ እያል ከሚያለቅሰው ለቀስተኛ በተጨማሪ የለቅሶውን ድባብ ቡድናዊ ለማድረግ እና ለቀስተኛው ሁሉ በተመሳሳይ ሥሜት እንዲከታተል ለማድረግ ወየታ ይደረደራል። ይህን አስመልክቶ (አቶ መኮንን ክፍሌ) ሲገልፁ፡-



ምስል ፰፡ አዋጊው አበበ ፕሮዲዩሰር የሆነ አስተዳደር ባለሙያ ቴሬዥም ጋሻዬ ከአቶ መኮንን ክፍሌ ጋር ወየታን አስመልክቶ ቃለ መጠይቅ ሲያካሂድ

*ወየታ፡፡[2] የወየታ ግጥም አንድ ግለሰብ መሬት ላይ ሆኖ ወዬ በማለት ግጥሙን ሲደረድር ይቆይና ሲጨርስ በዙሪያው ያለው አልቃሽ ተንጫጭቶ ያለቅሳል፡፡ ወዬ ባዩ ወየታ ሲደረድር አልቃሹ ዝም ብሎ ያዳምጥና ወየታውን ጨርሶ ሲደፋ ሰው ሁሉ ያለቅሳል፡፡ እንደገናም ሌላ ወዬ ባይ ዋንጫና ሌሎች መስሪያዎችን ይዞ ያለቅሳል፡፡ የወየታ ግጥም በአብዛኛው በሟች ቤት በራፍ አካባቢ እና በዋናው ማልቀሻ ቦታ ከቀብሩ ጋር እየተፈራረቀ የሚቀርብ ነው የወየታ ግጥም ከሃይማኖት ሰዎች ውጭ የፆታም ይሁን የዕድሜ ልዩነት ሳይደረግ ለሁሉም ይደረደራል ይላሉ (20/05/2004 ዓ.ም)፡፡*

ከዚህ እንደምንረዳው ወየታ ሟች ከሞተበት ሰዓት ጀምሮ ቀብሩ እስከሚጠናቀቅ ድረስ እንደሚለቀስ እና ከሃይማኖት አባቶች ውጭ የፆታም ይሁን የእድሜ ልዩነት ሳይደረግ ማንኛውም ሰው ሲሞት እንደሚደረደር ነው፡፡ በአንድ ሰው ግጥም ደርዳሪነት በአብዛኛው አልቃሽ ተቀባይነት የሚከወን የሃዘን መግለጫ ቃል ግጥም መሆኑን ነው፡፡ "ዋንጫ" ለምን እንደሚያዝ መረጃ ሰጭዎች ምላሽ ሲሰጡ ሟች በህይወት ዘመኑ እያለ የበላበትና የጠጣበት መሆኑን እና ያ የተበላውና የተጠጣው እህል ውሃ እንባ ሆኖ በመፍሰስ ስለ ሟች ማንነት እንገዳ ተቀባይነት፣ ጀግንነት፣ ደግነት እና በአጠቃላይ የስራ ውጤትን ለመመስከር ነው፡፡

የወየታ ግጥም ከሙሾ ግጥም የሚለየውም በሚያስተላልፈው መልዕክት ይዘት እና በሚኖረው ማህበራዊ ፋይዳ ተጨባጭነት ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ በሚፈጠሩት ማህበራዊ መስተጋብሮች የግለሰቦች ሚና ምን እንደሚመስልና ምን መሆን እንዳለበት ስለሚጠቁም የዕርስ በዕርስ ግንኙነትን በማጠናከር ረገድ ከሙሾ ግጥሞች ይልቅ የወየታ ግጥሞች ጉልህ ድርሻ አላቸው፡፡ ነገር ግን ይህ ጥናት ሁለቱም የመከወኛ አጋጣሚያቸው አንድ ይሁን እንጅ የአከዋወን ሂደታቸውና የሚያስተላልፉት መልዕክት እንዲሁም በታዳሚ ላይ የሚፈጥሩት ስሜት የተለያዩ መሆናቸውን ያሳያል፡፡

---

[1] አቶ ለገሰ አምሩ፣ አቶ ሞገስ ደጋው፣ አቶ አለምነው አሰፋ፣ አቶ በሪሁን መንግስቱ ተሻገር፣ አቶ ሀብታሙ መጫ፣ አቶ አርቅይሁን ወሰኔ፣ አቶ ሳህሉ መሰለ፣ አቶ ኑጋ ዘለለም፣ አቶ አብርሃም ዘለቀ እና አቶ መንፍጉት ጫኔው 20/05/2004 በተደረገው ቃለ መጠይቅ ወየታን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

## 2.8 ቶከራ

*ቶከራ፣ መፎከር፣ መደንፋት፣ ዞናን፣ አንበሳ፣ ጠላት፣ ገዳይ ማለት። እነዚህ መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ናቸው። (ደስታ ተክለወልድ፣ 1962፣975-976)።*

ከዚህም የምንረዳው ቶከራ ማለት ከሌሎች ከዋኔዎች አንፃር ሲታይ ከቃል ግጥሞቹ ይዘት ብቻም ሳይሆን የአከዋወን ሂደታቸውን ጨምሮ በተደራሲያኑ አዕምሮ ውስጥ የሚፈጥሩት ሥሜት ለየት ያለ እና በአብዛኛው የአርበኝነት እና የጀግንነት ሥሜትን የሚፈጥሩ ናቸው። ምክንያቱም ከመዝገበ ቃላዊ ፍቻቸው እንደምንረዳው መደንፋት፣ ዝሆን፣ አንበሳ፣ ጠላት ገዳይ የሚሉትን ሃሳቦች ስንመለከት ምን አልባት ዝሆን መግደል ብቻ ላይሆን ይችላል። ነገር ግን አንድ ሰው ጀግና የሚባለው በሚኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ በሚለይበት ማህበረሰባዊ መመዘኛ መሰረት ነው። ከዚህ መዝገበ ቃላዊ ፊቻቸው በተጨማሪ (አቶ ታከለ ንጋቱ ቶከራን) 3 እንዲህ ይገልፁታል፦



ምስል ፰፡ አጥኚው ከፎካሪ ታከለ ንጋቱ ጋር ስለ ቶከራ ምንነት ቃለ መጠይቅ ሲያካሄድ

ቶከራ[3] ለጀግና ወንዶች የሚፎከር ሲሆን ለአርበኞች፣ ለወታደሮች፣ ለአራሽ ገበሬዎች እና ለጀግና ነጋዴዎች እንደየ ጀግንነታቸው ልክና ደረጃ በቅሉ ላይ ተሁኖ ይፎከራል። ቶከራ የሚፎከረው ለጀግና ወንዶች ሲሆን ፎካሪው ሲፎክር አልቃሹ "እውነት ነው"፣ "እንዲያ በል" እያለ የምስክርነት ቃሉን ይሰጣል። ቶከራ በዚህ በደብረታቦር አካባቢ በጣም ይደምቃል። አንዳንዴም ጀግና ፎካሪዎች ገንዘብ እየተከፈላቸው መጥተው ይፎክራሉ። በዚህ ሥዓትም የወየታ ግጥምም በሙሃል እኩሉ ወየ ይልና ሲደፋ ሌላኛው ፎካሪ ይነጥቀዋል በዚህ ጊዜ አልቃሹ እረፍት ይወስዳል እንደገና ደግሞ ፎካሪው ምራቁን እንዲውጥ ወየታው ይቀጥላል ይህ የወየታና የቶከራ ግጥም እየተፈራረቀ መምጣት 'ኳርት ቅየራ' ይባላል። 20/05/2004 ዓ.ም

የቶከራ ግጥም ይበልጥ የሚኝ ጀግንነት እና አርበኝነት ጎልቶ የሚነገርበት እንደሆነ ያሳያል። ይህ የቶከራ ግጥም ደግሞ ለጀግና ወንዶች ብቻ የሚከወን መሆኑ ከወየታና ከሙሾ ግጥሞች ለየት ያደርገዋል። በለቅሶም ይሁን በሌሎቹ አውዶች ውስጥ የቶከራ ግጥም ሲነሳ ቀድሞ የሚመጣው ጀግንነት ነው። ይህ ጀግና የሚለው ጉዳይ ደግሞ በቀላሉ የሚባል ብቻም ሳይሆን የሚገኝም አይደለም። ምክንያቱም በዚያ ማህበረሰብ ውስጥ በርካታ ውጣ ውረዶችን ማየት ወይም ፈተናዎችን ማለፍ ይጠበቅበታል። ማህበረሰቡ የመሰከረለት የባህል ጀግና ደግሞ ትልቅ ክብር አለው።

በመሆኑም ይህ ጀግና በሞት ሲለይ በህይወት ዘመኑ የፈፀማቸውን ሥራዎች በማነሳሳት ተነሰቅስቆ ከማልቀስ ይልቅ በአዕምሮው ውስጥ ያን ጀግንነት እያሰበ ጀግና መሆንን ይሻል፤ከዚያው ማህበረሰብ ውስጥም ሌላ ጀግና፣ ሌላ አርበኛ ያጫል። ይህን ተተኪ ጀግና ለማግኘት የሚኝ ጀግንነት ተደጋግሞ ይተረካል። የጀግንነት ዓይነት እና ደረጃው ቢለያይም ትልቁ ዳኛ ደግሞ ራሱ ጀግናው የበቀለበት ማህበረሰብ ነው። በዚያ ማህበረሰብ

[3] አቶ ለገሰ አምሩ፣ አቶ ምስጋ ደጋው፣ አቶ አስምገው አሉላ፣ አቶ በሪሁን መንግስቱ ተሻገር፣ አቶ ሀብታሙ ሙሉ፣ አቶ አርቅይሁን በላይ፣ አቶ ባህሩ መለሰ፣ አቶ ኑጋ ዘለለም፣ አቶ አብርሃም ዘለቀ እና አቶ መኳንንት ጫኔው 20/05/2004 በተደረገው ቃለ መጠይቅ ቶከራን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ሰጥተውኛል።

እሳቤ መሰረት የሀገሩን ዳር ድንበር ከወራሪ ጠላት ተዋግቶ ያቆየ፣ ፀሐይ ዝናቡ፣ ብርድ ውችንፍሩ ሳይበግረው እርሶ ገበያውን በእህል የሚሞላ ገበሬ፣ በሃቅ ነግዶ የሚያተርፍና እህል ሰፍሮ፣ ብር ቆጥሮ የሚያበድር ነጋዴ እንዲሁም ባለው ሃብትም ይሁን ባለው ሥም ሲታሰሩ ዋስ ጠበቃ ሆኖ የሚያስፈታ መሆን አለበት።

በተለይም የሀገር ጠባቂው ጀግና ክብሩና ሞገሱ ከፍ ያለ ነው። ጀግናው ደሙን አፍስሶ፣ አጥንቱን ከስክሶ ለከፈለው የጀግንነት ተጋድሎ ማህበረሰቡ ብድር ይከፍላል። ይህ የመጨረሻው ክፍያ ደግሞ እንባ ነው።

በዚህ የቆከራ ክዋኔ ወቅት ቃል ግጥሙ ብቻ ሳይሆን የሚደጋገመው ከአንድ ዓመት እና ሁለት ዓመት በፊት የሞቱ ጀግኖችም ታሪክ ይወሳል። በለቅሶ ጊዜ ከሚከወኑት ግላዊ የሃዘን ማዕናኛ ንግግሮችና ግጥሞቹ በሃዘን የተጎዳው ቤተሰብና ማህበረሰብ ሃብቶች ናቸው። በዚህ ረገድ የሙሾ፣ የወየታ እና የቆከራ ግጥሞች ትልቁን ሥፍራ ይዘው ይገኛሉ።

# 3. ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢያዊ ገጽታ

ደብረ ታቦር ከተማ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በደቡብ ጎንደር ዞን የምትገኝ ሲሆን የዞኑም ዋና ከተማ ናት። ከአዲስ አበባ 667 ኪ.ሜ ርቃ ትገኛለች። ደብረታቦር ከተማ ረጅም እድሜ ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት እና የተለያዩ ታሪካዊ ቦታዎች አሏት። ከነዚህም መሃከል አፄ ቴዎድሮስ "ሴቫስቶፖል" መድፍን ያሰሩበት የጋፋት ኮረብታ፣ የራስ ጉግሳ አስከሬን ያረፈበት እና የጣና ሃይቅን በቅርብ ርቀት ለመመልከት በሚያስችል ተራራ ላይ የታነፀው የደብረታቦር ኢየሱስ ደብር፣ ሰመርናህ የአፄ ዮሐንስ ቤት መንግስት የነበረው፣ ጉራይ ጊዮርጊስ የተባለው ጥንታዊ ቤተክርስቲያን፣ ራስ አሊ ተወልደው ያደጉበት ማህደር ማርያምና ብቸኛው የተክሌ አቋቋም ትምህርት ቤት ጥቂቶቹ ናቸው (ፈለገህይወት አዕምሮ መጽሄት፣1991)።

## 3.1 መልክአምድራዊ ገጽታ

ደብረ ታቦር ከተማ በ$11^{0}$ 5 ኬንትሮስ በ $38^{0}$02 ከፍታ ምስራቅ ኬክሮስ እንዲሁም ከባህር ወለል በላይ 2667 ሜትር ከፍታ ላይ የምትገኝ ጥንታዊና ከተማ ናት። ደብረታቦር ከተማ ከዞኑ ዋና ከተማነትም በተጨማሪ የፋርጣ ወረዳም ዋና ከተማ በመሆን ታገለግላለች። በ 1983 ዓ.ም የስርዓት ለውጥ ከመካሄዱ በፊት የደብረታቦር አውራጃ ዋና ከተማ ነበረች።

በአዲሱ አወቃቀር ደግሞ በደቡብ ጎንደር ስር ከሚገኙ አስራ አንዱ ወረዳዎች ውስጥ የከተማ ወረዳ በመባል አንዷ ሁና ትገኛለች። ደብረታቦር ከተማን ዙሪያዋን በፋርጣ ወረዳ የተከበበች ናት። በመሆኑም ከሚያዋስኗት የፋርጣ ወረዳ ቀበሌዎች ውስጥ በስተሰሜን መደብ ጉብዳ፣ በስተምዕራብ አሪንጎ አቦ፣ በስተምስራቅ ውዶ ገብርኤል፣ በስተ ደቡብ ማህደረ ማሪያም ቀበሌዎች ያዋስኗታል። የከተማው ምዕራብ አቅጣጫ በአብዛኛው ወጣ ገባ የበዛበት ሲሆን አለምሳጋ እየተባለ የሚጠራ ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ይገኛል። በስተሰሜን አቅጣጫ ደግሞ ሜዳማ ሲሆን በደቡብ አቅጣጫ ተራራማ ነው። በስተምስራቅ አቅጣጫ ደግሞ ጉና ተራራን ጨምሮ ሌሎች ተራሮች ይገኛሉ። ይህ ጉና ተራራ በኢትዮጵያ ከራስ ዳሸን ተራራ ቀጥሎ በ 4230 ሜትር ከፍታ በሁለተኛ ደረጃ የሚጠቀስ ሲሆን ከደብረታቦር ከተማም 25 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። ጉና ተራራ ክረምት ተበጋ በበረዶ የተሸፈነ ሲሆን ለወታደራዊ ማዘዣ ጣቢያነት ምቹ ከመሆኑም ጋር ተያያዞ በርካታ አውደ ውጊያዎች ተካሂደውበታል። (ከደብረታቦር ከተማ ወረዳ ባህል እና ቱሪዝም ጽ/ቤት የተገኘው መረጃ፣ 2002፣23-27)።

## 3.2 የከተማዋ አመሰራረትና ስያሜ

የደብረታቦር ከተማ በአፄ ሠይፈ አርዕድ (ከ1327-1361 ዓ.ም) እንደተመሠረተች ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የተገኘው መረጃ ይገልፃል። ደብረታቦር ከተማ ስያሜዋን ያገኘችውም በከተማዋ ራስጌ ከሚገኘው የደብረታቦር እየሱስ ደብር የተተከለበት ተራራ አቀማመጡና ቅርጹ ክርስቶስ በእየሩሳሌም ለመላዕክት የተገለፀበትን ተራራ ስለሚመስል ከዚያ እንደመጣ ሲገለፅ ከዚያ በፊት ግን ደብረታቦር ከተማ "ጁራ" እየተባለች ትጠራ ነበር። (ፈለገ ህይወት አዕምሮ መጽሄት፣ 1991፤12 )።

ከዚህም በተጨማሪ አቶ አለምነው አሉላ፣ አቶ በሪሁን መንግስቱ ተሻገር እና አቶ ሳህሉ መለሰ የተባሉት መረጃ ሰጭዎች በተመሳሳይ መልኩ ሲገልፁ ከተማዋን የቆረቆሯት አጼ ሰይፈ አርዕድ እንደሆኑና ስያሜዋንም እሳቸው እንደሰጧት ነግረውኛል። ( ቃለ መጠይቅ፣25/05/2004)።

ራስ ጉግሳ ወሌ፣ ራስ አሊ፣ አፄ ቴዎድሮስ፣ አፄ ዮሐንስ አራተኛ እንደመናገሻና የጦር ማከማቻ አድረገው እንደተጠቀሙባት የታሪክ ተመራማሪዎች ይገልፃሉ (ባህሩ ዘውዴ፣1999፤11)።

## 3.3 ኢኮኖሚያዊ ገጽታ

የአካባቢው የአየር ፀባይ በአብዛኛው ደጋ እና ወይናደጋ ስለሆነ ለእርሻ ስራ ተስማሚ በመሆኑ አብዛኛው የአካባቢው ነዋሪዎች የሚተዳደሩት በእርሻ ነው። በዋናነት ጤፍ፣ ገብስ፣ በቆሎ፣ አተር፣ ባቄላ፣ ድንችና የመሳሰሉት ይመረትበታል። የከተማው ነዋሪዎች በመንግስት ስራ ላይ ተቀጥረው እና በንግድ ሙያ ተሰማርተው ይገኛሉ። አልፎ አልፎ በሽመና ስራ የሚተዳደሩ ሙስሊሞች አሉ።

## 3.4 ባህላዊ፣ ማህበራዊ እና የክብረ በዓላት ክዋኔ

የደብረታቦር ከተማ ማህበረሰብ ማህበራዊ ግንኙነቱ እጅግ በጣም የጠበቀ ነው። የስጋ ዝምድና ኖረም አልኖረም ከጉረቤት ጀምሮ አብዛኛው የከተማው ማህበረሰብ እርስ በርሱ ይተዋወቃል። ማህበረሰቡ በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች የሚገናኝ ሲሆን በማህበር፣ በዝክር፣ በእቁብ በመሳሰሉት የሚገናኙበት አጋጣሚዎች በርካታ ናቸው። እንኳንስ የከተማው ነዋሪ

ቀርቶ በከተማው ዙሪያ ካለው የገጠሩ ማህበረሰብ ጋርም በተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ እና እምነታዊ ጉዳዮች ግንኙነቱ የጠበቀ ነው። በተለይም ሰርግ፣ ክርስትና፣ ለቅሶ፣ ተስካር ጥምቀት እና ሌሎችም ክዋኔዎች ለማህበረሰቡ የጥብቅ ግንኙነቶቹ መፍጠሪያ አጋጣሚዎች ናቸው።

ይህ ማህበረሰብ በክፉውም በበጎውም አብሮ የሚላወስ እና እንብላ እንጠጣ ባይ ማህበረሰብ ነው። ያለውን ተካፍሎ በመብላትና የቸገረውን በመደገፍ ይታወቃል። ከዚህም የተነሳ ማህበራዊ ግንኙነቱ ከሌሎች ጉዳዮች በላይ የጠበቀ ነው። የከተማው ማህበረሰብ ከገጠሩ ማህበረሰብ ጋር በጋብቻና በክርስትና እጅግ የተሳሰረ ነው። ከዚህም ባሻገር በተለያዩ አመታዊ ክብረ በዓላት የመገናኛ መንገዶች ይሁኑ እንጅ ለገበያ፣ለፍርድ ጉዳይ፣ለስብሰባ እና ለሌሎች ጉዳዮች ገጠሬው ከተማ ሲመጣ ለወዳጅ ዘመዱ እሸት ጭኖ፣ግልገል ስቦ ብቅ ማለት የተለመደ ነው።

ጋብቻ በአካባቢው ማህበረሰብ ክብር የሚሰጠው ጉዳይ ነው። ከመረጃ አቀባዮቹ መካከል አቶ አለምነው አሉላ እንደነገሩኝ የአፈፃፀም ሁኔታውም የእያንዳንዱን ሰው ዘር እና ማህበራዊ ደረጃ መሰረት ያደረገ ነው። ለምሳሌ፡ ባላባትነት፣ አርበኝነትና ባለፀጋነት ትልቅ ክብር የሚሰጣቸው ጉዳዮች ሲሆኑ ባንፃሩ ደግሞ ቀጥቃጭ፣ ፋቂና ሸማኔ የመሳሰሉት ዝቅተኛ ግምት የሚሰጣቸው ናቸው በማለት በ 25/05/2004 በተካሄደው ቃለ መጠይቅ ገልፀውልኛል ።

የተወሰነ ለውጥ ቢኖርም በአብዛኛው ግን ዛሬም መታየቱ የዚያን ማህበረሰብ ቀደምት ማንነት ያንፀባርቃል።

ሌላው በዚህ ማህበረሰብ ሃይማኖታዊ የክበራ በዓላት ትልቅ ስፍራ አላቸው። ጥምቀት በደብረታቦር ውስጥ ሁሉም በየአመቱ በሞቀና በደመቀ ሁኔታ ይከበራል። "እጅባር ሜዳ" የለትለ ማርገጃ ብቻም ሳይሆን የተለያዩ አመታዊ ክብረ በዓላት መከወኛ ስፍራም ነው። የጥምቀት እለት ከ17 በላይ ታቦታቱ እጅባር ሜዳ ያድራሉ። ህፃን አዋቂውም ታቦታቱን አጅቦ ከመታደሙ በተጨማሪ ታቦታቱ ከወረዱበት ማደሪያው አብሮ በማደርና ትዕዛዛቱን በመፈፀም ልዩ በረከት እንዳገኝ ይቆጥራል።

ሌላው ደግሞ ጥር 25 ቀን የመርቆሪዎስ ንግስ በዓል ከሌሎቹ ሁሉ የተለየና በፈረስ ጉግስ የታጀበ፣ የከተማና የገጠሩ ሰው በየአመቱ በጉጉት የሚጠበቀው አዝናኝ የክበራ በዓል

ነው፡፡ ቁሱ ወረቡን፣ ወጣቱ የመተጫጫ እስክስታና ዘፈኑን፣ እናት አባቶች በወትግባ በወት እያሉ ሲያጨበጭቡና እናቶች የእንኳን ስለቱ ሰመረ እስክስታውን ሲከውኑ፣ የፈረስ ጉግስኛው ከተቃራኒ ቡድን ፈረስኛ ገዳም ውስጥ ገብቶ ፈረሰኛውን ሲወጋው፣ በአጠቃላይ ፈረው ሲወቀስ ጉበዙ ሲወደስ ለበዓሉ ልዩ ድምቀት ሰጥቶት ይውላል፡፡

አጆባር ሜዳ ላይ ከሚውለው የእለቱ ክብረ በዓል በተጨማሪ ማታ የሩቅ ዘመዱ፣ የቅርብ ጉረቤቱና ዘመድ አዝማዱ ተጠራርቶ ሲበላ ሲጠጣና ሲዘፍን ያድራል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ የሚያሳየው የደብረ ታቦር እና አካባቢው ማህበረሰብ ለማህበራዊ ግንኙነቱ፣ ለእምነትና ለሃይማኖቱ ያለው ክብር ከፍተኛ መሆኑን ነው፡፡

ሌላው በየአመቱ የሚከበረው መስከረም 17 ቀን የሚውለው የመስቀል በዓል ሲሆን ይህ በዓል በከተማው እምብይ ቦታ "ቴዎድሮስ አደባባይ" ላይ ትልቅ ደመራ ተደምሮ ህፃናት፣ ወጣትና ሽማግሌዎች ነጭ የሀገር ባህል ልብስ በመልበስ ሁሉም አምሮ እና ተውቦ አደባባይ ወጥቶ ሲያከብር በዙሪያው ያለው የገጠሩ ማህበረሰብ ፈረሱን ጋልቦ፣ የተለያዩ የጦር መሳሪያዎችንና የተለያዩ አልባሳትን በመያዝ ደመራውን በመዞር ያጅባሉ፡፡ ቀሳውስቱና ከተለያዩ ቤተክርስቲያን የመጡ የሰንበት ተማሪዎች በመዝሙርና በሽብሸባ ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ በዓሉን ያከብራሉ፡፡ በመጨረሻም ለግማሽ ቀን ያክል ከዚያው ላይ ቅዳሴ ተደርጐ በሃይማኖት አባቶች ፀሎት ተደርጎ፣ ተባርኮ ደመራው ይለኮሳል፡፡ ሰው የደመራውን ተሸካሚ ምሰሶ ወዴት እንደሚወድቅ በጉጉት ይጠብቃል፡፡ በኋላም ወደወደቀበት አቅጣጫ ሃይማኖታዊ ፍች/ትርጓሜ በመስጠት የደመራውን አመድ እየተቀባ ለሚቀጥለው አመት ቀጠሮ በመያዝ ወደ ቤቱ ይመለሳል፡፡

ከዚሁ ቴዎድሮስ አደባባይ ላይ ሙስሊሙ ማህበረሰብ የአረፋና የመውሊድ ክብረ በዓላትን በተመሳሳይ መልኩ በፀሎትና በስግደት እንዲሁም በተለያዩ ሃይማኖታዊ አከባበር ስርዓት ያከብራል፡፡ በዚህ ወቅትም ይሁን በመስቀል በዓላት ላይ የሌሎች እምነት ተከታይ ወጣቶች ይገኛሉ፡፡ በዓሉን አስመልክቶ የተዘጋጀውን ምግብም አብረው በልተው ጠጥተው ይለያያሉ፡፡ የሚበሉት የሚጠጡት የምግብ አይነት ግን እንደ ለስላሳና ዳቦ የመሳሰሉትንነው፡፡ በእህ ጉዳይ ላይ የሚሳተፉትም ህፃናትና ወጣቶች እንጅ አዋቂዎችን አይጨምርም፡፡ ይህ ሁኔታ በሌሎችም ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ይበልጥ እንዲቀራረቡና ጥብቅ ግንኙነት እንዲኖራቸው ያደረጋል፡፡ ከዚህም ውስጥ አንዱ ለቅሶ ነው፡፡

የለቅሶ ክዋኔ በደብረታቦር ልዩ ቦታ ይሰጠዋል። በሰርግ፣ በጥምቀት፣ በማህበርና በክርስትና ሰው ተጠርቶ ሊቀር ይችላል ያን ያክል ከባድ አይደለም፤ በለቅሶ ጊዜ መቅረት ትልቅ የማህበራዊ ህይወት መናጋትን ይፈጥራል። ማንኛውም ሰው ለቅሶ ሰምቶ አይቀርም። የገጠሩም ተሸኝቶ ውሉ አድሮ ቢሆን ይመጣል። በተለይም ከገጠር የሚመጡት እንጀራ፣ ድፍድፍ፣ስጋ፣ ሌሎችንም በእህያ ጭነው ይመጣሉ። በለቅሶ ክዋኔ ስዓት ሟች ነፍሱ ከውጣበት ዕለት ጀምሮ እስከ ለቅሶው መጠናቀቅ ድረስ የማስተባበር ሃላፊነቱን የሚወስደው ማህበረሰቡ እንጅ ቤተሰብ አይደለም።

በክዋኔው ላይም የወየታም ሆነ የቆከራ ግጥም በመደርደር የሚታወቁት ከከተማው ነዋሪዎች ይልቅ የገጠሩ ነዋሪዎች ናቸው። በአጠቃላይ የለቅሶውን የክዋኔ ድባብ ተቆጣጥረውት ይውላሉ። በለቅሶ ጊዜ የገጠር ዘመድ የሌለው ሰው ለቅሶው አይደምቅለትም። ይህም ራሱን ችሎ ሊጠና የሚችል ጉዳይ ይመስለኛል። ምክንያቱም በከተማና በገጠሩ ማህበረሰብ መካከል ይበልጥ ለፎክሎር ዘሮች መፈጠር፣መከወንና መተላለፍ አስተዋፅኦ የሚያደርገው ማነው? የሚለውን ለማወቅ ስለሚረዳ።

በአጠቃላይ በደብረታቦር ከተማ 19 እድሮች ይገኛሉ። እድሮች የሃይማኖት ልዩነት ሳይኖር ሁሉም በፍላጎቱ አባል ይሆናሉ። የእድሩ አባላት ለቅሶን ያክል ከባድ ነገር በጋራ እንጅ በሃዘን የተጎዳው ቤተሰብ ብቻውን ሊወጣው አይችልም በማለት  እስከ ሳልስቱ ድረስ የሟችን ቤተሰብ ያፅናናሉ። በወቅቱ የሚፈለገውን ይሸፍናሉ፣ የገንዘብ ችግር ላለበት ገንዘብ ይሰጣሉ፣ ልጆቹንና ቤተሰቡን በመንከባከብ አይዞህ እና አለንልህ በማለት እገዛ ያደርጋሉ። ይህ ሁሉ የተደረገለት ግለሰብ ደግሞ በተራው በሌላ የለቅሶ አጋጣሚ ላይ ቀዳሚ በመሆን የመረዳዳትና የመደጋገፉን ተግባር ያከናውናል። ከዚህ በተጨማሪ የወጣቶች እድር እየተመሰረተ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሃዘን ወቅት የመረዳዳትና የመደጋገፉ ጉዳይ በተተኪው ትውልድም በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ትልቁን ድርሻ ይዞ ይገኛል።

## 4. ትንተና

የቃል ግጥም ጉዳይ ሲነሳ ሁሉም ቃል ግጥሞች የሚከወኑበት አውድ (context) እንደሚለያይ ሁሉ ይዘታቸውም ይለያያል። ቃል ግጥሞች ሲከወኑ የመከወኛ አውዳቸው የተለያየ መሆኑ አንዱ ልዩነት ሲሆን በተመሳሳይ አውድ ውስጥም የተለያየ ይዘት ያላቸው ቃል ግጥሞች መኖራቸው ደግሞ በትንተና ጊዜ ምደባ ማድረግን ይጠይቃል።

በዚህ መሰረት ከዚህ ቀጥሎ የወዮታና የፉከራ ግጥሞችን የይዘት ትንተና ለማድረግ ምደባ ተደርጓል። በመስክ ስራ ጊዜ የተሰበሰቡት የለቅሶ ቃል ግጥሞች የወዮታና የፉከራ ግጥሞች በማለት በሁለት አበይት ክፍሎች ተከፍለዋል። ምደባው የአከዋወን ሂደታቸውን (performance) እና ተግባራቸው (function) መሰረት ያደረገ ነው። ወዮታ ለማንኛውም ሰው ይደረደራል። ዓላማውም ሌሎቹ ማህበራዊ ፋይዳዎች እንዳሉ ሆነው በለቅሶው ዕለት ስለ ሟች መልካምና አሳዛኝ ታሪክ በመተረክ አልቃሽ ከልቡ ተንሰቅስቆ እንዲያለቅስና ብሶቱና ሃዘኑ እንዲወጣለት ማድረግ ነው።

በዚህ መሰረት የወዮታ ግጥሞች ማብላት ማጠጣትን የሚገልፁ ግጥሞች እና ቁጨትን የሚገልፁ ግጥሞች ተብለው በሁለት ተከፍለዋል። በሁለት ተከፈሉበት የተከፈሉበት ምክንያት ግጥሞቹን በአካል በአውዱ ተገኝቼ መረጃ በሰበሰብኩበት ጊዜ የተለያዩ ገጣሚዎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን ሲያነሱ ከላይ በተከፈሉት ሃሳቦች ላይ የሚያጠነጥኑ ሆነው በማግኘቴ ነው።

የፉከራ ግጥሞችን ስንመለከት ደግሞ ፆታና ማህበራዊ ደረጃን መሰረት በማድረግ ለጀግና ወንዶች ብቻ የሚገጠሙ ናቸው። በአብዛኛው አልቃሽ ወይም ሃዘንተኛ ከእንጀቱ ተንሰፍስፎ እንዲያለቅስ ከማድረግ ይልቅ ሟች በህይወት ዘመኑ የፈፀማቸውን የጀግንነት አይነቶችን በመጥቀስ በማህበረሰቡ ስሜት ውስጥ ሌላ ጀግና በሟች እግር እንዲተካ በማሳሰብ፣ የአርበኝነት ስሜትን በመፍጠርና በማጀገን ላይ ያተኩሩ ናቸው። ትልቁ ጉዳይም ጀግናውን ማወደስና በውዳሴ መሸኘት ሲሆን ሌላ ጀግናም ቦታውን እንዲረከብ ጥሪ ማድረግ ነው። በፉከራ ግጥሞች ከዋኜ ጊዜ እንደ ወዮታ ግጥሞች አልቃሽ ተንሰቅስቆ ከማልቀስ ይልቅ እፊቱ ላይ የሚታየው የቁጨት ስሜት ነው። ከማስለቀስ ይልቅ የማፅናናት እና ቀሪውን ማህበረሰብ ሟች የጀግንነት ታሪክ ሰርቶ አልፏል ይልቅስ አንተም እንደሱ ጀግና ሁን የሚል እንደምታ አለው። በፉከራ ግጥም ውስጥ በዋነኛነት የጀግንነትና የአርበኝነት ስሜት ጉልቶ

የሚንፀባርቅ በመሆኑ አውዱን መሠረት በማድረግ የጦር ሜዳ ጀግንነትን የሚገልፁ ግጥሞች እና የስራ ጀግንነትን የሚገልፁ ግጥሞች በሚል በሁለት አበይት ክፍሎች ተከፍለዋል። የለቅሶ ክዋኔዎቹም ሆኑ የተሰበሰቡት ግጥሞች ይዘት የሚያንፀባረቀው የእነዚህን ዓይነት ጀግኖች ታሪክ በመሆኑ እነዚህ በሁለት መከፈላቸው የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል።

የጦር ሜዳ ጀግንነትን የሚገልፁ በሚለው ስር ሁለት ንዑሳን ክፍሎች አሉ። እነሱም ሟች ያደገበትንና ጀብድ የፈፀመበትን ቦታ እና ማህበረሰብ የሚገልፁ ግጥሞች እና የሟችን ተግባር ወይም ስብዕና በቀጥታ የሚገልፁ ግጥሞች የሚሉ ናቸው።

ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የስራ ጀግንነትን የሚገልፁ ግጥሞች የሚል ነው። በዚህ ስር ሦስት ንዑሳን ክፍሎች ይገኛሉ። እነሱም፦ አንደኛ የስራ ታታሪነትን የሚገልፁ ግጥሞች፣ ሁለተኛው የስራ ውጤትን የሚገልፁ ግጥሞችና ሦስተኛው እንግዳ ተቀባይነትን የሚገልፁ ግጥሞች ናቸው።

የቀከራ ግጥሞች ከላይ በሁለት አበይት ክፍሎች የተከፈሉበት ምክንያት በዚያ ማህበረሰብ ውስጥ እነዚህ ሁለት ጉዳዮች ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጣቸው መሆኑና ይህን ደግሞ ከዚያው የመረጃው ባለቤት ከሆነው ማህበረሰብ መገንዘብ በመቻሉ ነው። በተጨማሪም ግጥሞቹ ሲደመጡ የሚፈጥሩት ስሜትና በተለያዩ ገጣሚዎች ሲገጠሙ መደጋገማቸው እንዲሁም በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ማድረጋቸው በዚህ አይነት እንዲመደቡ አደርጎቸዋል።

በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ጀግንነት ሲነሳ ከተቀናቃኝ ጠላት የሚጠብቅና መከታ የሆነ ሰው ይፈለጋል። ተኩሶ ሊገድል፣ ሞግቶ ሊረታ፣ተናግሮ ሊደመጥ የሚችልና የማህበረሰቡ እና የባህሉ ጠባቂ ጀግና ያስፈልገዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ሃብታሙ አትንቶ፣ድሃው ሸምቶ ይገባ ዘንድ ገበያው መጥገብ አለበት። ይህ ይሆን ዘንድ ደግሞ አምራች ገበሬ ያስፈልጋል። ሌሎች የጀግንነት መገለጫዎች ቢኖሩም ለእነዚህ ሁለቱ የጀግንነት መገለጫዎች ማህበረሰቡ ልዩ ክብር አለው። ጀግና የሚላቸው ግለሰቦች በነዚህ በሁለቱ ጉዳዮች ውስጥ በአንዱ ወይም በሁለቱም ግለፍ ሲችሉ መሆኑን ጭምር ግምት ውስጥ ያስገባል። ለዚህ ጥናት ማሳያ ይሆናሉ የተባሉ የሁለት ግለሰቦች የለቅሶ ክዋኔ ላይ የተሰበሰቡት የወየታና የቀከራ ግጥሞች አውዳቸውን መሠረት በማድረግ ይተነተናሉ።

ሁለቱ ታዋቂ ግለሰቦችም አቶ ወረደ መኮንን በጦር ሜዳ ጀግንነት፣ አቶ እውነቱ ዘለቀ በስራ ጀግንነት የታወቁ ነበሩ፡፡ መረጃ በምሰበስብበት ወቅት ከተመለከትኳቸው ስድስት የለቅሶ ክዋኔዎች እና ከተሰበሰቡት ግጥሞች አንፃር የእነዚህ ሁለት ግለሰቦች የለቅሶ ክዋኔ የተለየ እና ለጥናቱ በማሳያነት ቢቀርቡ ጥሩ ነው ብየ በማመኔ ነው፡፡

በመስክ ስራ ላይ ከተሰበሰቡት 500 (አምስት መቶ) ግጥሞች ውስጥ 16 (አስራ ስድስት) የወየታ ግጥሞችንና 34 (ሰላሳ አራት) የፉከራ ግጥሞችን በድምሩ 50 (ሃምሳ) ግጥሞችን አውዳቸውን በመመርኮዝ ተተንትነዋል፡፡ ከተሰበሰቡት ግጥሞች ውስጥ እነዚህ ብቻ ለትንተና የተመረጡበት ምክንያት ጉዳዩን ለማሳየት በቂ ናቸው ተብሎ ስለታመነ እና የጥናት ወረቀቱ ገጽ ብዛት ከተፈቀደው በላይ እንዳይሆን ጥንቃቄ ለማድረግ ሲባል ነው፡፡

## 4.1 የወየታ ግጥሞች ይዘት ትንተና

የወየታ ግጥሞች ፆታና ማህበራዊ ደረጃን ሳይለዩ ለሁሉም ይደረደራሉ፡፡ ከመረጃ ሰጭዎች መካከል አቶ ሳህሉ መለሰ የወየታ ግጥሞች ለወንዶች፣ ለሴቶች፣ ለአዋቂዎች፣ ለወጣቶችና ለህፃናት ሳይባል ለሁሉም የሚደረደሩ መሆናቸውንና የአከዋወን ደረጃቸው ግን ማህበራዊ ደረጃን መሰረት እንደሚያደርጉ ገልፀውልኛል (ቃለ መጠይቅ፡25/05/2004)፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ በክዋኔ ወቅት የተሰበሰቡት የወየታ ግጥሞች ግብዓት ግጠማትን የሚገልፁ እና ቁጩትን የሚገልፁ በማለት የተከፈሉ ሲሆን ይህም ምደባ የሚሰራው ለነዚህ ግጥሞች ብቻ እንጅ ለሁሉም የወየታ ግጥሞች አይደለም፡፡ ቀጥሎ የሁለቱ ትንተና ቀርቧል፡፡

### 4.1.1 ግብዓት ግጠማትን የሚገልፁ ግጥሞች



ምስል 4፡ የአቶ እውነቱ ዘለቀ ማህበርተኞች ሀዘናቸውን ሲገልፁ

ሀ. ስጡኝ ያንን ዋንጫ በእንባ እሞላዋለሁ

በሞቴ እየተባለኩ ጠጥቸበታለሁ፡፡

ለ. ላይለቀስ ነው ወይ ወትሮስ ላበላ ሰው

ላይለቀስ ነው ወይ ወትሮስ ላጠጣ ሰው

እጁ ወንፊት ሆኖ ሰጥቶ ለጨረሰው፡፡

ሐ. እንኳን አበላሀው እንኳን አጠጣሀው አልከው ግባግባ

መፈታቱ አይቀረም ቤትና ገበያ፡፡

(አቶ ነጋ ዘላለም፣16/05/2004 ዓ.ም)፡፡

በዚህ ግጥም ውስጥ የምንረዳው ሟች በህይወት ዘመኑ እያለ ምን ያክል ለጋስ ሰው እንደነበር ነው፡፡ ይህንን የማድረግ የሃብት አቅም ያለውና ለዚህ ማንነቱ ደግሞ ሊለቀስለት ይገባል የሚል ይዘት አለው፡፡ በተለይም በግጥም "ሀ" የምንረዳው ማንም ሰው ሊያበላ ሊያጠጣ ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህን ሟች የተለየ የሚያደርገው በዋንጫ ማጠጣት መቻሉ ነው፡፡ በዋንጫ ማጠታት ደግሞ ክብር አለው፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ በአንድ አውድ ውስጥ ለምሳሌ በማህበር፣ በሰርግ፣ በክርስትና እና በመሳሰሉት በተመሳሳይ ጊዜና ስፍራ በሚታደሙ ሰዎች መካከል የደረጃ ልዩነት በመኖሩ ምክንያት የመጠጫው እና የመመገቢያው እቃ ይለያያል፡፡ ከፍ ያለ ደረጃ ያላቸው ደግሞ በዋንጫ ይጠጣሉ፡፡ ዝቅ ያሉት ደግሞ በቆርቆሮ አለያም በቅል ሊጠጡ ይችላሉ፡፡ ይህ ዋንጫ ደግሞ በማንኛውም ሰው ቤት ሳይሆን በሞላላቸው ሃብታሞች ቤት ነው፡፡

እንደዚህ አይነት ሰዎች በሞት ሲለዩ በለቅሶው ዕለት ወየባይ ወይም ፍካሪ ዋንጫ ይዞ የሚያለቅሰው ሟቹ በህይወት በነበረበት ጊዜ የበላው የጠጣው እንባ መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ አስለቃሽ ይህን እውነታ በመግለፅ ወየ ሲል አልቃሽም ተንሰቅስቆ ያለቅሳል፡፡ በተለይ ማህበርተኞችም ዙሪያውን ዋንጫ ይዘው ማልቀሳቸው ዋንጫው በዚህ አውድ ውስጥ የተበላበትና የተጠጣበት መሆኑን እንዲሁም ገጣሚው ያለው ነገር ትክክል መሆኑን ለማመልከት ነው፡፡

በግጥም "ለ" የምንመለከተው መለቀስ ካለበት ለእንደዚህ አይነቱ ሟች ነው፡፡ ያለውን አብልቶ አጠጥቶ ለቸገረው ሰጥቶ ያለፈ ሰው በመሆኑ ማልቀስ ክብር ነው፤ የበላ፣ የጠጣ እንጀት ለዚህ ምስክርንት መስጠት አለበት የሚል እንድምታ አለው፡፡ በዚህ

ግጥም ውስጥ ወንፊት የተገለፀበት አገባብ ሟች ያለውን ገንዘብ ከሌላው ጋር ተካፍሎ የበላና ሰው ተቸግሮ ማየት የማይፈልግ ለነገ የማይል ደግ ሰው መሆኑን ለመግለፅነው፡፡

በከርከርና በድርድር ደምቆ የዋለ ገበያም መፈቻ ሰዓቱ ሲደርስ ጭር እንደሚል ሁሉ፣ የተበላበት የተጠጣበት ቤትም ጌታው ሲሞት ይዘጋል፡፡ ግጥም "ሐ" ም በንጽጽር በሟች ቤት ውስጥ የነበረውን የመስተንግዶ ድምቀት የሚገልፅነው፡፡ ስለዚህ አንተ አይቆጭህም ደግ ሰው ነህ፡፡ በህይወት በነበርክበት ጊዜ ማንንም እየጠራህ አብልተህዋል፣ አጠጥተህዋል የሚል ሲሆን ሌላውም ይህን የሞትን አይቀሬነት አውቆ ለቸገረው ቢሰጥ፣ ለራበው ቢያበላ መልካም ነው የሚል መልዕክት አለው፡፡

ሟች ከሞተ በኋላ ይህ ግጥም መደርደሩ ለሟች ምንም ጠቀሜታ የለውም፡፡ ነገር ግን ለሟቹ ምስክርነትን ከመስጠት ባሻገር ማብላት ማጠጣቱ በማህበረሰቡ እንዲለመድና እንዲቀጥል ጭምር ያሳስባል፡፡ ማሳሰብም ብቻ ሳይሆን ዛሬም አብሮ መብላትና መጠጣት የተለመደ በመሆኑ ማህበረሰቡ ዘንድ ልዩ ትርጉም አለው፡፡ ከነ እገሌ ቤት ድሮ ተበልቷል፣ ተጠጥቷል፣ በማለት ታሪክ እንዲነገርለት የመፈለግም ነገር አንዱ ነው፡፡



ምስል ፮፡ አቶ ዋንታየው የሟች በአቶ ወረደ መቀነትን ለትስ ላይ ወኖ ሲል

### 4.1.2 ቁጨትን የሚገልፁ ግጥሞች

ሀ. "ስጋህም ለምኔ ጠጅህም ለምኔ  
ወንድም አለኝ ማለት በቂ ነበር ለኔ፡፡

ለ. ምነው ቀርቶ ቢሆን ሰው ሆኖ መፈጠር  
ተመልሶ ጭቃ አፈር መሆን ላይቀር፡፡

ሐ. እንባን ጠለል አርጎ፣ አይንን ቅርዝዝ አርጎ  
ቢነግሩት ለወንድም አይጨክንም ነበር  
በውድም በግድም፡፡

መ. አደባባይ ወጪ የሚቀሰኝ ባጣ  
ምድር ምድር እየሁ ቆፍሬ ላወጣ፡፡

ሠ. ሞትማ ሙት እንጅ ከማን ትበልጣለህ  
እንዲያው አጟጒትህ ታሳዝነኛለህ፡፡

ረ. እንኳን ወጪ ማለት አላውቅም መናገር  
እንጀቴን በልቶኝ ነው የወገኔ ነገር፡፡"

ሰ. ኧረ ከፋኝ ከፋኝ ለማን ልንገረው፣  
ባድና ጨለማ ሁለቱ አንድ ነው፡፡  
(አቶ ባንታየሁ የማታ፣ 05/06/2004 ዓ.ም)፡፡



ምስል ፬፡ የአቶ እውነቱ ዘለቀ ቤተሰቦች ሲያለቅሱ

ይህ የወየታ ግጥም የሚደረደረውም ሟች ህይወቱ እንዳለፈ በቤቱ አካባቢ፣ ጧት ግርገጃው ወጥቶ የሩቅ ዘመድ ለቀብር እስከ ሚደርስ ድረስ ነው፡፡ ዋናው ማልቀሻ ቦታ ሲደረስ በቶከራ መሃከል አልቃሹን ለማሳረፍ ወየታ ይደረደራል፡፡ በተለይም ቤቱ ደጃፍ ላይ ህፃን ልጆቹ በሰው ጩኸትና ትርምስ ተደናግጠው ምን እንደተፈጠረ ለማወቅ ተቸግረው፣ ጣታቸውን አፋቸው ውስጥ ከተው ጥፍራቸውን እየነከሱ፣ ድምፃቸው ሳይሰማ እምባቸው ብቻ እየፈሰሰ አልቃሽ አልቃሹን እየተመለከቱ አንዳንድ አወዛጋቢ ጥያቄ ሲጠይቁ በመመልከት የሚደረደሩ የወየታ ግጥሞች ዘመድ ባዱን ስቅስቅ አድረጎ በማስለቀስ "ወቶም ዛቶም አለቀሰለት" ያስብላል፡፡

እነዚህ ግጥሞች ለቅሶውን እንዲጠነክር የሚያደርጉና አልቃሽ በሟች ሃዘን ስቅስቅ ብሎ እንዲያለቅስ የሚያደርጉ እና መሪር ሃዘኑ በእንባ እንዲወጣለት የሚያደርጉ ናቸው፡፡ በዚህ ሰዓት ደረትን መደለቅ፣ ፊትን መንጨት፣ መውደቅ መነሳት የሟች ትዝታዎች ድቅን የሚሉበት ሁኔታን የሚፈጥሩ ናቸው፡፡

ሟች በሞቱ ምክንያት የሚያደርሰው ጉዳት በቤትዘመድና በወገን ላይ ከመብላት መጠጣትም በላይ በአደባባይ አንሶ መገኘትንና ከሰው በታች መሆንን ሁሉ ያመጣል፡፡ በተለይም ግጥም "ሀ፣ "ሐ"፣ "ረ" እና "መ"ን ስንመለከት ሞት በቤተሰብ ላይ የሚያደርሰው ጉዳት  በቤት ውስጥ ከሚሸፈን ገመና ያለፈና በአደባባይ ዋስ ማጣትን፣ ከጉን አደዞሀ ባይ መ ከታ ማጣትን ብቸኝነት እና ባዛናነትን የሚያመጣ ነው፡፡ በማህበረሰቡ አንድ ሰው በአደባባይ አሸንፎ፣ ተከብሮና፣ የበላይ ሆኖ ካልታየ ከፍተኛ ስነ ልቦናዊ እና ማህበራዊ ቀውስን እንደሚያስከትል ያሳያል፡፡ በእኩዮቹ ዘንድም አንሶ መገኘትን ያመጣል፡፡ ማንም ሲያልፍ ሲያገድም ለጠብ ይመኘዋል፡፡

ጉዳዩ ከማብላት ማጠጣት ያለፈ እና የማንነት ጉዳይም ነው፡፡ ከወንድም ጋር ቢጣሉትም በጥቃት ጊዜ ግን ደራሽ መሆኑን የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ በአንድ ማህፀን መፈጠር በራሱ የተለየ ዋጋ እንዳለው ይጠቁማል፡፡ ምክንያቱም የዝምድና ጉዳይ ክብር የሚሰጠው በሥጋ ለተወለደ ብቻም ሳይሆን ጋብቻ፣ ክርስትና፣ እንዲሁም ሌሎችም እንደማህበርና እቁብ የመሳሰሉት ደረጃቸው ይለያይ እንጅ ለማህበራዊ ግንኙነቶች መጥበቅ ጉልህ ድርሻ ያላቸው መሆናቸውን ጭምር ያሳያል፡፡ ወንድሙ የተገደለበት ሰው እጥፍ ድርብ ገድሎ ይገባል የወንድም መኖር በአደባባይ ተከብሮ እንዲውል ያደርጋል፡፡

ከሃይማኖት አንፃር ተጠቅቶ ወይም የበታች ሆኖ መገኘት ማህበራዊም ሆነ ሥነ-ልቦናዊ ቀውስን ያመጣል፡፡ ይህን ማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ቀውስን ለመከላከል ሲባል ሃይማኖቱ ውግዝ ያደረገውን ድንበር በማፍረስ ባህሉ የሚያሳድርበትን ጫና ከመቋቋሙም ባለፈ በማህበረሰቡ ጀግና መባልን ያመጣለታል ሲሉ ከመረጃ ሰጭዎች ውስጥ አቶ መኮንንን ክፍሌ ገልፀውልኛል 20/05/2004፡፡

ግጥሙ ሰዎች በጆሮአቸው ከሚሰሙት ይልቅ በአይናቸው ለሚያዩትና በማህበራዊ ህይወታቸው ለሚያጣጥሙት ነገር ትድሚያ የሚሰጡ መሆናቸውን ያሳል፡፡ በሚገጥም የህይወት ውጣ ውረድ እና ማህበረሰቡ በሚሰጠው ማህበራዊ ደረጃ ዝቅተኛ ግምት መሰጠት ተሸንፎ መግባት፣ ቀስ ጠበቃ ማጣትና ባይተዋርነት ትልቅ የህሊና ቁስል ይፈጥራሉ፡፡ ይህ ደግሞ መሪር ሃዘንን ያመጣል፡፡ ከዚህ ቀን ጀምሮ ሰው አልባነትና ብቸኝነት ውሪያውን እንዲከቡት ያደርገዋል፡፡ በዚህ ሰዓት ከውስጡ ያመዋል፣ ያዝናል፣ ያለቅሳል፣ እንጉጉሩ፣ እረግመዱ፣ እስተያየቱ ሁሉ ይለወጣል፡፡ ከፍተኛ የተስፋ ቆራጭነት ስሜት በውስጡ ይነግሳል፡፡ በለቅሶ የወጣለት እየመሰለው የሟችን ስም እየደጋገመ በመጥራት ስራዎቹን በመጥቀስ ተንሰቅስቆ ያለቅሳል፡፡

ግጥም "ለ"፣ እና "ሠ"ን ስንመለከት ከመጀመሪያውም ሰው ሆኖ መፈጠር በራሱ ስህተት ነው፣ ምነው ባልተፈጠርን በማለት ተፈጥሮን ያማርራል፡፡ ይህ ግጥም የሰውን ልጅ ከንቱነት እና አቅመ ቢስነት አጉልቶ ያሳያል፡፡ ይህን ካነሳ በኋላ በግጥም "ሠ" ላይ ደግሞ መሞትማ ሙት ነገር ግን የአሟሟትህ ሁኔታ ነው እኔን እንዳለቅስ፣ እንዳዝንና እንደተከዝ ያደረገኝ ይላል፡፡ ሟች የሞተበትን አኳኋን አሰቃቂ፣ አሳዛኝና ድንገተኛ መሆኑን በማንሳት አልቃሽ አቁን ከፍቶ እንዲያለቅስ ያደርጋል፡፡ ሀዘኑን የከፋ የሚያደርገው ያሟሟቱ ሁኔታ እንደሆነ በማሳየት ከተፈጥሮ ጋር ወይም ከፈጣሪው ጋር ያለውን ግግረር አስረስቶ ሞት የተከሰተበትን ሁኔታ (situation) ማለትም በሰው ተገድሎም ከሆነ የገደለውን ሰው፣ በመኪና ተገጭቶ ከሆነ የሞተበትን አጋጣሚ በመውቀስ ከተፈጥሮ ጋር ያለውን ጥላቻ ያቀላል፡፡ ታዳሚውም በምን ሞተ? እንዴት ሞተ? ማን ገደለው? በእግዚአብሔር ነው ወይስ በሰው እጅ? የሚለውን እንዲያውት ያደርጋል፡፡ በአብዛኛው ማህበረሰብ ዘንድ በህመም ታሞ መሞት ፀጋ ነው፣ በሰው እጅ መሞት ግን የሃዘን ሁሉ መሪር ሃዘን ነው የሚል ሃሳብ ያንፀባርቃል፡፡

በአጠቃላይ የወየታ ግጥሞች ሟች በህይወት ዘመኑ የፈፀማቸውን ብቻ ሳይሆን የቤተሰቡንና የማህበረሰቡን ስሜት፣ ፍላጐትና አስተያየት የያዙ በመሆናቸው ቤተዘመድ ብቻ ሳይሆን የለቅሶው ታዳሚ ሁሉ "ዋይ" ብሎ እንዲያለቅስ ያደርጋሉ፡፡ ሚስቱን፣ ልጆቹን፣ ቤተሰቡን በማንሳት ወደፊት ችግርና ፈተና ሊገጥማቸው የሚችል መሆኑን በመጥቀስ የሟች ቤተሰብ ችግር የማህበረሰቡም ቁምር መሆኑን በመጠቆም "ነግ ለኔን" በመፍራት የየራሱን ቤተሰቦችና ልጆች በማስታወስ ለራሱ ያክል ያለቅሳል፡፡

የወየታ ግጥሞች አላማ ከማፅናናት ይልቅ ቤተዘመድ ከውስጡ ያለውን ብሶትና ሃዘን ዋይ ብሎ በማልቀስ እንዲወጣለት ማድረግ ነው፡፡ በለቅሶው ላይ እንባውን አፍስሶ በሚያለቅስ እና በማያለቅስ ሰው መካከል በሟች ቤተ ዘመድ ዘንድ የተለያየ ስሜትን ይፈጥራል፤ ይህ ደግሞ በማህበራዊ ግንኙነት ላይ ተፅዕኖ አለው። ቤተዘመድ በአደባባይ እንባውን አፍስሶ፣ ደረቱን ደልቆና ወድቆ ተነስቶ በማልቀስ ሃዘኑ የሚወጣለት የወየታ ግጥሞች በሚደረደሩበት ሰዓት ነው፡፡ ለዚህ ምክንያቱ አንድ ወየ ባይ የወየታ ግጥም ከደረደረ በኋላ ሌላኛው ወየ ባይ ከመቀበሉ በፊት ገጣሚው የመጨረሻውን ሥንኝ እንደደፋ የገጠሙ የመድፊያ ሥንኝ የቋጠረቸውን አሳዛኝ መልዕክት ምክንያት በማድረግ ሁሉም አሊቃሽ ተንጫጭቶ የሚያለቅስበት አጋጣሚ በመኖሩ ነው፡፡

## 4.2 የቶኪራ ግጥሞች ይዘት ትንተና

የቶኪራ ግጥሞች ዕድሜንና ማህበራዊ ደረጃን ልዩነት መሰረት በማድረግ ለጀግና ወንዶች ብቻ የሚገጠሙ ሲሆን የጀግንነት መገለጫዎቹ ግን የተለያዩ መሆናችውን ከመረጃ ሰጭዎች መካከል አቶ ተሾመ ውበቱ በቀን 25/05/2004 በተደረገው ቃለ መጠይቅ ነግረውኛል፡፡አቶ ተሾመ ድሮ ከጣሊያን ጋር ለተዋጉ ሴት ጀግኖቻችን ይፎከር ነበር፡፡ ዛሬ ግን ይህ ሁሉ የለም በጥሩ ጠማቂነታቸው፣ እንግዳ ተቀባይነታቸውና በጥሩ ሴትነታቸው የወየታ ግጥሞች ይደረደርላቸዋል እንጅ አይፎከርላቸውም በማለት ገልፀውልኛል፡፡ የተሰበሰቡት ግጥሞች የጦርሜዳ ጀግንነትን የሚገልፁና የሥራ ጀግንነትን የሚገልፁ ግጥሞች ተብለው በመከፈል ተተንትነዋል፡፡

### 4.2.1 የጦር ሜዳ ጀግንነትን የሚገልፁ ግጥሞች

በዚህ ክፍል ውስጥ ትንተና የተደረገባቸው ግጥሞች አገርን፣ አካባቢንና ወገንን ከጥቃት መከላከልን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ጀግናው ያደገበትን አካባቢና ማህበረሰብ

በማንሳት መሰረቱ ያደገበት ማህበረሰብና ባህሉ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ ግጥሞቹ ስለሚቼ በትርበት ለማያውቁ ለቀስተኞች (መቼቱን) ቦታውንና ሰዓቱን በመግለፅ መረጃ ይሰጣሉ፡፡ በዚህ ጥናት ሟች ያደገበትን ማህበረሰብና የጀግንነቱን ሰብዕና በቀጥታ በመግለፅ የተገጠሙ በሚል ተተንትነዋል፡፡

### 4.2.1.1 ሟች ያደገበትን፣ ጀብድ የፈፀመበትን ቦታና ማህበረሰብ የሚገልፁ ግጥሞች

ሀ. የተከዜው በሬ የበለሳው በሬ

አምበሳ ነበረ ተሸነፈ ዛሬ፡፡

ለ. እረ አገሬ መልዛ ሲቆጣ አምበሳ ነው

እረ አገሬ ጋይንት ሲቆጣ አምበሳ ነው

ዝም ብሎ እኮ አይደለም ግፍ ተቀብሎ ነው፡፡

ሐ. እረ አገሬ መልዛ ወጣቱ አልተነጻ ሴቱ አልተደፈረ

ያ የኛ ወረዳ ያ የኛ ምክትል ወረደ ነበር፡፡

መ. ጣሊያን መጥቶ ነበር ለአምስት አመት

ሃይማኖት ለውጦ ሰው እየረሸነ ሲያቃጥል ታቦት

መልዛ መቀጠዋ ቀይ አፈር ገጠመው በሰባት ብረት

አባነብሮ ወርዱ ፈታውራሪ ያለው በስምንት ሰዓት

ካምፕህን አስርክብ ብለው ጠየቁት

ዘራፍ ብለው ሂደው ቁልቁል በሮ ገጠሙት

ያሻቸውን ገድለው ሊላውን ማረኩት

በዚያው በሮ ቀረ ኢትዮጵያን ሳያያት፡፡

ሠ. ወርዱ የመልዛው ጥጃ

አንዱን በጥፊ አንዱን በርግጫ፡፡

ረ. እንንገራችሁ የመልዛን ሙያ

የወንዶቹን ሙያ

ቆራቁረው ነበር የጦር ገበያ፡፡

(አቶ ሞገስ ፀጋው፣ 05/06/2004 ዓ.ም)፡፡



ምስል 7፡ አቶ ሞገስ ደጋው እና አቶ ወንድወሰን አበባው ከአቶ ወረደ መኮንን ለቅሶ ላይ ሲፎክሩ

ያደገባቸውን አካባቢዎች እና ያደገበትን ማህበረሰብ እንዲሁም የሰራቸውን ጀብዶች በመጥቀስ የተገጠሙ ሲሆን ሟቹን ከዚህ በፊት ለማያውቀው ለቀስተኛ እና ታዳሚ መረጃ ይሰጣሉ፡፡ ጊዜና ቦታውን በመጥቀስ የሟችን ታሪክ ይዘረዝራሉ፡፡

ከዚህ በላይ የቀረቡት የቆከራ ግጥሞች የሚገልፁት ሟች ወረደ መኮንን ተወልዶ ያደገው በደቡብ ጎንደር ዞን እብናት ወረዳ መልዛ ተብሎ በሚጠራ ንዑስ ወረዳ ውስጥ መሆኑን ነው፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆነው ግጥም 'ሁ'ን ስንመለከት 'ወርዴ የመልዛው ተጃ አንዱን በጥፊ አንዱን በርግጫ' በማለት ልጅነቱን ያሳለፈውና ተወልዶ ያደገው መልዛ ተብሎ ከሚጠራ አካባቢ መሆኑን ይጠቁማል፡፡

ጀግና ለመሆን ሰው ሆኖ መወለድ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ይልቁንስ ያሳደገው ቤተሰብ እና ኮትኩቶ ያሳደገው ማህበረሰብ ትልቁን ድርሻ ይወስዳል፡፡ ይህ ሟች ጀግና ሊባል ያቢቃውም በዚያ ማህበረሰብ እይታ አንፃር ነው፡፡

የአምበሳነት ክብር ለሟቹ ብቻ የተሰጠ አይደለም፡፡ ጀግንነትን የሚቋደሰው ከማህበረሰቡ እንደመሆኑ መጠን ያ ማህበረሰብ የአምበሳነትን ክብር ቀድሞ ተጋርቷል፡፡ ግጥም 'ለ'ን ስንመለከት መልዛና ጋይንት ማዶ ለማዶ ናቸው፡፡ የዚህ አካባቢ ህዝብም በምክንያት ላይ ተመስርቶ ሲቆጣ አስፈሪ ነው የሚል እንድምታ አለው፡፡ አምበሳ ለነገር ወይም ለትንኮሳ አይቸኩልም፡፡ ታግሶ ታግሶ ሲነሳበት ግን አይጣል ነው፡፡ ማህበረሰብም የአምበሳን ባህርይ ይጋራል፡፡

ሟች አብዛኛውን የስራ ጊዜውንም በዚሁ አካባቢ የወረዳ ምክትል አዛዥ ሆኖ በደርግ ዘመነ መንግስት እንደሰራ ግጥሞቹ ይፀቁማሉ፡፡ ግጥም "ሐ"ን ስንመለከት ሟች ወረደ መኮንን በመልዛ አካባቢ የወረዳ ምክትል ሆኖ ሲሰራ ምንም እንኳ በወቅቱ የነበረው ስርዓት አስቸጋሪና ወጣቶች ለብሔራዊ ውትድርና የሚታፈሱበት፣ ሴቶች በመንግስት ወታደሮች ተገደው የሚደፈሩበት ወቅት ቢሆንም ሟቹ በወቅቱ ወጣቶችም እንዳይታፈሱ፣ ሴቶችም እንዳይደፈሩ ያደርግ ስለነበር በማህበረሰቡ አዕምሮ ውስጥ ሊጠፋ የማይችል ውለታን እንደዋለላቸው ያሳያል፡፡

በምልከታ ወቅት መገንዘብ እንደተቻለው ግጥሙን ከሚገጥመው ገጣሚ በላይ ታዳሚው "እውነት ነው"፣ "እንዲያ በል"፣ "አዎ ማንም አልነካንም" ነበር በማለት ለመደግመጥ በሚያስቸግር ሁኔታ ስሜቱን ይገልፅ ነበር፡፡ ይህ ማህበረሰቡ ከዚህ በፊትም በርካታ ፈተናዎችን የተቋቋመ እና ከእብራኩ በወጡት ጀግኖች ልጆቹ ተከብሮ እንደሚኖር በማሳየት የአሁኑ ትውልድ የቀደሙት አይነት ጀግኖችን ባህርይ በመያዝ ሃላፊነቱን መውሰድ አለበት የሚል ማሳሰቢያ አለው፡፡

በግጥም 'መ' ውስጥ የቀረበውን ሃሳብ ስንመለከት የሟች ወረደ መኮንንን ጀግንነት ለማጉላት ሲባል እሱ ባልነበረበት ዘመን ከተፈፀሙ ድርጊቶች ወይም በዘመን የማይገናኙትን ተረኮች ለግለሰቡ ሲሰጡት ይስተዋላል፡፡

እነዚህ ቃል ግጥሞች በዚህ መልክ መገጠማቸው የታሪኩን ተአማኒነት ከማጉላታቸው ባሻገር በማህበረሰቡ ስነ ልቦና ውስጥ የሚፈጥሩት የአርበኝነትና የጀግንነት መንፈስ እጅግ ከፍ እንዲል ያደርጋል፡፡ ጀግንነት ጠላትን ተኩሶ መምታት ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ ተስማምቶና ተመሳሳይ ፍላጎትን አክብሮ መኖር ነው፡፡



ምስል ፱፡ አቶ ሞገስ ይገዙ በስተቀኝ እና አቶ ለገሰ እምሩ በስተግራ ሲፎክሩ

### 4.2.1.2 የጧችን ሰብዕና የሚገልፁ ግጥሞች

ሀ. እንቺ ምሳሌ የእውነት እውሪ
የታውቀ ነው የወርዶ ስራ፡፡

ለ. ማገባቱንግ ሙላው ያገባል
ወርዶ ነበረ የወንዶቹ ባል፡፡

ሐ. ወረዶ ባለማተብ ነው
የነንደሬው ልጅ ማንም የሚያውቀው
ሃይማኖተኛ ሰው እክባሪ ነው፡፡

መ. ወርዶ ሁለት እጁ ቀኝ እንደ ሸማኔ
ወዲህ ወታደር ወዲህ ገበሬ

ሠ. የየቫለም ባል አገሪ ገኸው የፈረደው
ወረዳ እውራጃ ይገባኝ የለው፡፡

(አቶ ለገሰ እምሩ፡ 05/06/2004 ዓ.ም)

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ግጥሞች በእመዛኙ የጧችን ምግባር እና የማህበራዊ ደረጃውን ያሳያሉ፡፡ የግጥሞቹ ይዘት የጧችን ጉብዝና የሚገልፁ ሲሆን ጉብዝናው ወይም ጀግንነቱ ግን በአንድ በተወሰነ ጉዳይ ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን በተለያየ መልኩ መሆኑን ያሳያል፡፡ ገጣሚው ስለዚ ሀ ጧች ሲገጥም እሱ ብቻ ስ ለጧች ማንነት እን ዲናገር አልፈለገም፡፡ የጧች ስራ ወይም ጀግንነቱን አገር ያወቀው ፀሃይ የሞቀው ነው በማለት የግጥሞቹን እውናዊነት ያስረግጣል፡፡ በተለይም በግጥም "ለ" የተገለፀውን ሃሳብ ስንመለከት የጧች የጀግንነት ደረጃውን በጣም ከፍ ያደርገዋል፡፡ በዚህ ግጥም ውስጥ የሚገለፀው አብይ ጉዳይ የጋብቻ ጉዳይ ሳይሆን በአስፈሪነቱ፣ በጀግንነቱ እና በዚያ ማህበረሰብ ውስጥ በሚሰጠው ክብር ከሌሎች በአካባቢው ካሉት ወንዶች የተለየ እና ታዋቂ መሆኑን ነው፡፡ ምን አልባት ይህ አስፈሪነቱ በወቅቱ በዚያ ማህበረሰብ ዘንድ ያሳደረው አሉታዊ ተፅዕኖም እንዳለ ሊያመለክት ይችላል፡፡

ሌላው የጀግንነቱ መገለጫ ሆኖ የቀረበው ሰብዕናው ነው፡፡ ግጥም "ሐ"ን ስንመለከት ሟቹ ሰው አክባሪና ሃይማኖተኛ መሆኑን ይገልፃል፡፡ በሃይማኖቱ የፀና ሰው እንደነበርና በጎንደር ሙሉ የታውቀና የተከበረ ሰው እንደነበር ግጥሙ ያመላክታል፡፡

ግጥም 'መ' የሟችን ጀግንነትን በተለያየ መንገድ ይገልፃል፡፡ ማህበረሰቡ "ግራ" እና 'ቀኝ' ለሚሉት ፅንሰ ሃሳቦች እራሱን የቻለ አረዳድ አለው፡፡ ከዚህ በመነሳት ሟች በህይወት ዘመኑ በጦር ሜዳ ውሎው እና በግብርና ውሎው ስኬታማ እንደነበር እና ከአንዱ የስራ መስክ ቆይቶ ወደ ሌላው ሲገባ ቶሎ የመላመድና በሁሉም ዘርፍ ውጤታማነቱን ማሳየት እንደቻለ ያስረዳል፡፡ ሸማኔ መወርወሪያ ሲወረውር በሁለቱም እጁ እኩል ነው፡፡ እየወረወረም እዕምሮው ያሰበውን ያለምንም ችግር መፈፀም ይችላል፡፡ በሁለቱ እጆቹ መካከል ምንም ልዩነት የለም ልክ እንደዚሁ፡፡ ሟች በአንድ ወቅት ሲተኩስበት በነበረው እጁ ሌላ ጊዜ ያርስበት፣ ያመርትበት እንደነበረ ያሳያል፡፡ ይህም በሁሉም ዘርፍ ጎበዝ እንደነበር ያመለክታል፡፡

በግጥም 'ሠ' የተገለፀውን ስንመለከት ደግሞ ሟች ገዥ በነበረበት ወቅት የሚሰጣቸው ውሳኔዎችና አስተዳደራዊ ስራዎች ህግ እና መመሪያን የተከተሉ እንደነበርና ይህ በመሆኑ ጉዳዩን ሌላ ቦታም ይግባኝ ወይም ቅሬታ አመልካች ይዞ ቢሄድ ያው የሱ ሃሳብ የሚፀና መሆኑን በመግለፅ ህግ አክባሪነቱን ያመለክታል፡፡ በግጥሙ ውስጥ ሚስቱም እንደምትሞካሽ ተገልጿል፡፡ ልጆቹም ይወደሱበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሟችን ጀግንነት አጉልተው የሚያሳዩ ሌሎች ግጥሞችን እንመልከት፡፡



ምስል ፱፡ አቶ ያሬጋል ተመስገን በስተግራ እና አቶ ወንድወሰን አበበ በስተቀኝ ከአቶ ወረደ መኮንን ለቅሶ ላይ ሲፎክሩ

ሀ. ወርዷ መኮንን የአምበሳው ግልገል
በተዋከበት የማታጋድል
አምላክ አይተልህም ድል ታደርጋለህ
እንደነ ሚካኤል እንደነ ገብርኤል፡፡

ለ. ወረደ መኮንን ጦርሜዳ ወስደው ቢያታግሉት
ተጋማግቸው አንገት ላንገት
እንዲህ ነው እንጂ ጀግና ማለት
ከሞቱም አይቀር በስም መሞት
ጉንፋን ይገዳል ቀን ከደረሰ ከተኙበት፡፡

ሐ. የወዲያኛው ጦር ወዲህ ሲተኩስ
የወዲህኛው ጦር ወዲያ ሲተኩስ
ወርዷ ያዚያገለት ሳት ሳት ይለዋል
እንደሸለቆ የሰው ደም ሲፈስ፡፡

መ. ወረደ መኮንን ይበሉኝ ብሎ
ከመሃል ገባ ሳንጃውን ስሎ፡፡

ሠ. የምንጃሩ ቄስ የአልቢኑ ዳኛ
በየተራራው ነጭ የሚያስተኛ፡፡
(አቶ፡ ወንድወሰን አበበ 05/06/2004 ዓ.ም)፡፡

ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ግጥሞች ውስጥ የሟች ጀግንነት እና አርበኝነት ጎልቶ ይታያል፡፡ ሟች በተሰለፈባቸው አውደ ውጊያዎች ድል ያገኛል፡፡ የድል አድራጊነት ደረጃውም ከነ ሚካኤልና ገብርኤል ጋር ተመሳስሎ ቀርቧል፡፡ በፈጣሪ ተራዳኢነት ምንጊዜም ድል ያደርጋል፡፡ የሚካኤልና የገብርኤል ድል አድራጊነት ከእግዚአብሄር እንደተሰጠ ሁሉ ይህ ግለሰብም የልዕለ ሀይል ተፈጥሮ ዕርዳታን እንደተጋራ ያሳያል፡፡

በግጥም 'ለ' እና 'መ' የተገለፀውን ስንመለከት የስም ጉዳይ፣ የክብር ጉዳይ፣ የማንነት ጉዳይ ከፍተኛ ቦታ ይዞ ይገኛል፡፡ ሞት የሰው ልጆች ተፈጥሮአዊ ግዴታ

ነው፡፡ ነገር ግን ዝም ብሎ ተወልዶ መሞት የሞት አስቀያሚ ነው፡፡ የሰው ልጅ ከሞተም አይቀር በስሙ ሊወሳ እና ሊዘከር የሚችል የጀግንነት ታሪክ ሰርቶ መሞት አለበት የሚል ይዘት አለው፡፡ ከሞቱም አይቀር በስም እና በዝና መሞት ይመረጣል፡፡ ይህ ደግሞ እንዲሁ በቀላሉ የሚገኝ አይደለም፡፡ በግል ህይወት፣ በማህበረሰቡም ይሁን በአገር ጉዳይ ላይ በሚያጋጥም ችግር ወይም ፈተና ወቅት አንገት ላንገት ተናንቆ፣ በሳንጃ ተመሻልቆ እና ድል አድርጎ መሞት ትልቅ ክብር አለው፡፡

ይህ በመሆኑ በማህበረሰቡ ላይም ይሁን በአገር ደረጃ የነበረውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ማንነት ተጠብቆ ባለበት እና በነበረበት እንዲቀጥል ማስቻል በዚያ ማህበረሰብ ዘንድ ትልቅ አፎይታን ይፈጥራል፡፡ ለሟችም ትውልድ የማይረሳው የጀግንነት ታሪክን ማፃፍ ነው የሚል ሲሆን በጉንፋንና በሌሎች አልባሌ በሽታዎች የሞተ ግን ቦታም እንደሌለው ያሳያል፡፡ ማህበረሰቡም በዚህ ግጥም አማካኝነት ከስጋቱ ነፃ የሚያደርገው ለባህሉና ለዳር ድንበሩ ጠባቂ ጀግና እንዲኖረው ይፈልጋል፡፡ ከዚያ አኳያ የዚህን ሟች የለቅሶ አጋጣሚ በመጠቀም ዛሬ ላይ ያለውን ትውልድ አንተም እንደ እገሌ ሁን፣ አንተም ጥቅማችንና ሃይማኖታችን አስጠብቅልን የሚል ማሳሰቢያም አለው፡፡ ታዳሚም ዙሪያውን ሆኖ "እውነት" በማለት በቃል ከሚገለፀው በላይ በቃል ያልገለፀውና በስሜቱ የሚታወቅበት አርበኝነትን የማፅናት ወኔ እና ሞራል ይታይበታል፡፡

በዚህም መሰረት የአገርንና የማህበረሰብን ማንነት ለማስጠበቅ ሲል ወደ አገራችን ከገባው "ነጭ" ጋር ከተፋለሙት ቀደምት ጀግኖች ታሪክጋር የሟች ግለሰብን የለቅሶ አጋጣሚ በመጠቀም ያለፈውን ማህበረሰብ ጀግንነት ዛሬ ላይ ላለው ማህበረሰብ ያወርሳል፡፡ በዚያን ወቅት የነበሩ የጦር መሳሪያ አይነቶችን ይጠቅሳል፡፡ ለዚያ ማሳያ የሚሆነን ግጥም "ሠ"ን ስንመለከት ሟች በርካታ ፈተናዎችን እንዳሳለፈና ማህበረሰቡም ከዚህ ግለሰብ የሚማረው ነገር እንዳለ ያሳያል፡፡ ይህን የጀግንነትና ያርበኝነት ታሪክ ሲፈፅም የሚገለገልበት የጦር መሳሪያ "ምንሽር" እና "አልቤን" ከመሆኑ ጋር ተያይዞ እነዚህ መገልገያዎች የዚህ ጀግና መጠሪያዎች ናቸው፡፡ እንደፋርሶ የሚያርስ ገበሬ መጠሪያው "እርፍ" እና "ሞፈሩ" ሲሆን የአዝማሪ ደግሞ "ማሲንቆው" ነው፡፡ ለምሁር ወረቀትና እስክብሪፕቶው ሲሆኑ ለዚህ አርበኛ ደግሞ "አልቤን" እና "ምንሽሩ" ናቸው፡፡ እነዚህ መገልገያዎች የግለሰቦችን የስራ ድርሻ እና ሚናቸውን ያሳያሉ፡፡

በሌላ በኩል ፉከራ ግጥም 'ሐ'ን በቁሙ ስንመለከት ከአካባቢው ማህበረሰብ ሃይማኖታዊ ማንነት አንፃር ሲታይ የሚጣረስ ይመስላል፡፡ ነገር ግን በትርጓሜ ዙሮ የሚገተምበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህም ከሰው ልጅ ስነ ልቦናዊ ፍላጐት መካከል አንዱ ሃይለኝነት ነው፡፡ በመሆኑም ደም የማፍሰስ ጉዳይ አብሮት የመጣ ነው፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነን የቆሌ ደም፣ የደንቃራ ደም፣ በሌላ በኩልም ብር አምባር ሰበርልዎ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በመሆኑም ይህ ከቡር የሆነው የሰው ደም በሽለቆ ፊሶ ሲሄድ ከአውዱ (context) አንፃር ትክክል በመሆኑ የሚቹ ጀግንነት ሚዛን ይደፋል እንጅ አያጎድልም ወይም ውግዘት አያስከትልም፡፡



ምስል 10፡ አርበኛ ግራዝማች እምሩ በስተግራ እና አቶ እንዳልካቸው ተሻገር በስተቀኝ ሲፎክሩ

በአጠቃላይ የጦር ሜዳ ውሎ ጀግንነትን መሰረት አድርገው የተገጠሙት የቀረሉ ግጥሞች አብይ ጉዳያቸው ሟች በህይወት ዘመኑ ያከናወናቸውን ተግባራት ገልጦ ማሳየት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የዚያን ማህበረሰብ የጀግንነት ደረጃ ከፍ ለማድረግ ሲባል አለም አቀፋዊ እውቅና ያላቸውን የጀግንነት ታሪኮችን የሚያወሱ ተረኮች በመጨመር ያጠናክራል፡፡ ትልቁን ድርሻ ይውሰድ እንጅ የግል ተነሳሽነቱም ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም፡፡

ከምንም በላይ ፉከራ ከማህበረሰቡ ልብ ውስጥ ገብቶ በማህበሰቡ ውስጥም ለየት ያለ ማህበራዊ ደረጃን ለማግኘት በጀግንነት ሰንድ ላይ ስሙ ሊሰፍር የግድ ነው፡፡ የሟቹ ማህበራዊ ደረጃ ብቻ አይደለም ከፍ የሚለው የሚስቱ፣ የልጆቹ፣ የወላጅ ቤተሰቦቹ፣

የእሁት ወንድሞቹ እና የእከስት፣ የአጎቶቹ ሁሉ ማህበራዊ ደረጃ ከፍ ያለ ነው፡፡ ከዚህ የቤተሰብ አባል ውስጥም አንዱ በሞት ሲለይ ከለቅሶው የሚቀር ሰው የለም፡፡ ከሌላው የማህበረሰብ ክፍል በተለየ ሁኔታ በእንደነዚህ አይነቶች ታላላቅ ሰዎች ለቅሶ ቀን መትረት ትልቅ ስነ ልቦናዊ ቀውስን ያስከትላል፡፡ ምክንያቱም ከፈጣሪው ቀጥሎ ለነዚህ አካባቢያዊ ጀግኖች እራሱን አስገዝቶ ስለሚኖር ነው፡፡ በነዚህ ትላላቅ ሰዎች ለቅሶ ላይ መገኘት ደግሞ ትልቅ ክብር ነው፡፡ ምክንያቱም በክዋኔው ላይ ተገኝቶ ስለነበረው የለቅሶ ሁኔታ በአይናቸው ያዩትን ለሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ ይጠበቃልና፡፡

በአሁኑ ሰዓት ጥይት ተኩስ እየቀነሰ ቢመጣም የሚፎክርለት ጀግና ሲሞት ምግባሩ ወይም ጀግንነቱ ከጦር መሳሪያ ጋር የተያያዘ በመሆኑ በርካታ ጥይት ይተኮስለታል፡፡ በርግጥ ዛሬም ቢሆን ከጥይት ትኩስ ውጭ ሌላው የለቅሶ ክዋኔ አለ፡፡ ጥይት ተኩስ አሁን የቀረበት ምክንያት መንግስት ሌላውን ሰው ታስደነግጣላችሁ፣ ሰው ትገድላላችሁ እና ፀጥታ ታደፈርሳላችሁ በማለት ማንም ሰው ጥይት እንዳይተኩስና ተኩሶ የተገኘ እንዲቀጣ መወሰኑ እንዲሁም ፍቃት እንዳይደረግ በመወገዙ ምክኒያት ነው፡፡

### 4.2.2. የስራ ጀግንነትን የሚገልፁ ግጥሞች

ሥራን ስናንሳ የተለያዩ የስራ ዓይነቶችን እንድናስታውስ ያደርገናል፡፡ በዚህ ክፍል የሚተንተኑት ግጥሞች የሥራ ታታሪነትን የሚገልፁ፣ የሥራ ውጤትን የሚገልፁ፣ እና እንገዳ ተቀባይነትን የሚገልፁ ተብለው በሶስት ምድብ ቀርበዋል።

#### 4.2.2.1 የስራ ታታሪነትን የሚገልፁ ግጥሞች



[illegible]

ሀ. በሁዳዴ ፆም በዚያ ቀልቀሎ በዚያ ገዳዳ

እርሻውን እርሶ ያለሰልሳል

ሰኔ ግንቦት ላይ ዘሩን ይዘራል

ፃምሌ ነሃሴን ሰብሉን ያርማል

ህዳር ተቅምትን ያሰባስባል

ጥር የካቲትን ወቅቶ ያገባል፡፡

ለ. አዳምጥ አገሬ አዳምጥ ዘመዴ

የእውነቱ ታሪክ ቀርቧል ሰንዴ

ያልገደለውን ገደልኩ ለምን ነው

ያልዘመተውን ዘመትኩ ለምን ነው

የእኔስ ውሎየ ከነኮልባ ጋር ነው ይላል እውነቱ ዘለቀ፡፡

ሐ. እውነቱ ዘለቀ የምርቱ ጌታ

የበሬው ጌታ፣ የቀፎው ጌታ

ጀሪቶ ጥይት ሰሪው በታንታ

ላይበላው ሲለው የኮልባ ጌታ

በኩልባ በሬ አንድ እርጉ ቢያርሰው

ጨፍ አበቀለ ሰንጋማይጥሰው፡፡

መ. እውነቱ ዘለቀ የበሮቹ ዘር

በሬው ከርሻው ላይ ከፍከፍ ሲል

ግረኛው ወጥቶ ዘንዶ ሲመስል

አሽከር ጉልጓዩ ቢቴን ቢቴን ሲል

አብቃይ ነዋ ጨፍ እርጉሚመስል፡፡

ሠ. የበሮቹ ዘር የቆንጆይቱ ባል

የቆንጆይቱ ባል ያውም ያጅሪት

እግር ቀልጣፋ እንደ ሽረሪት

ስትጠምቅ ማታ ስትጋገር ሌሊት

ወፍ ጭጭ ሲል ሲነጋ ሌሊት

ድምጿ ይሰማል እንደጋሪት ይላል እውነቱ፡፡

(አቶ ማሩ አስፋ፡፡16/05/2004 ዓ.ም)፡፡

ግጥሞቹ የሟች እውነቱ ዘለቀን የግብርና ታሪክ በመተረክ ለጀግንነቱ መገለጫ የሆኑትን ጉዳዮች ይገልፃሉ፡፡ በማንኛውም የስራ ዘርፍ ውጤታማ በመሆን ጀግንነትን ማስመስከር ይቻላል የሚል አንድምታ አላቸው፡፡ በለቅሶው እለት ግለሰቡ በህይወት ዘመኑ የሰራቸውን ስራዎች በቀረበ ግጥም በመግለፅ ከጦር ሜዳው ጀግና ጋር ያልተናነሰ ጀግንነት እንዳለው ይ ጠቁማሉ፡፡ እነዚህ ግጥሞችም የግለሰቡን የስራ ተነሳሽነትና ታታሪነቱን ያሳያሉ፡፡ በግጥም "ለ" ጀግንነት ጦር ሜዳ በመዝመትና በመግደል ብቻ እንዳልሆነ በመ ጠቆም ጀግና ለመ ባልም የ ሱ ያልሆነውን ታሪክ ማውረስ ትክክል እንዳልሆነ በመግለፅ የሟች ማንነት ምን እንደሚመስል ያሳያሉ፡፡ ማንኛውም ሰው በሚሰራው ስራ እና በትክክል የሱ በሆነው ታሪክ ሊኮራ ይገባል የሚል እውነት ከፍተኛ ቦታ እንዲኖረው ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ምክንያቱም ይህ ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ የህዝብ ሀብት እንደመሆኑ መጠን ቀጣዩ ትውልድም ካለፈው ትውልድ መማር ያለበት እውነትን እንጅ ማስመሰልን እንዳልሆነ ያሳስባሉ፡፡ ከግጥሞቹ መጨረሻ ላይም ሟች ዛሬ ቢሞትም እምነቱና አስተሳሰቡ ምንጊዜም ካደገበት ማህበረሰብ እንደማይጠፋ ያሳያሉ፡፡ የሟች ጀግንነትም የሚገለፀው ከነ ኮልባ ጋር በመገኘቱና በነሱ በሚያመርተው ምርት መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ የሟች ጀግንነት የሚገለፀው ፀሀይ ሀሩሩን እሾህ እንቅፋቱን፣ ብርድ ውርጭን፣ ዝናብ በረዶውን፣ ውሃ ጥም ርሃቡን፣ እባብ አጋሩውን ሳይፈራ ወትቱን ጠብቆ በሰዓቱ እያረሰ፣ በሰዓቱ እየዘራ፣ በሰዓቱ እያረመ፣ በሰዓቱ እያጨደ፣ በሰዓቱ እየወቃ፣ ወደቤቱ በማስገባት ከሌሎች ገበሬዎች በተለየ ሁኔታ ከፍተኛ ምርት የሚያመርት በመሆኑ ነው፡፡

ይህም ሥራው ደግሞ ሟቹን ጀግና ከሚያስብሉት ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡ በአገራችን ያሉትን የምርት ማምረቻ ወቅቶች መሰረት አድርጎ በሰዓቱ ማድረግ የሚገባውን ሁሉ ያለምንም መሰልቸት ሥራውን ያከናውናል፡፡ በርግጥ ሁሉም ገበሬ ያርሳል፣ ይዘራል፣ ያርማል፣ ያጭዳል፣ ይወቃል፡፡ ይህ የስራ ጀግናም እዚህ ደረጃ ላይ

ለመድረስ እንደ ጦር ሜዳው ጀግና ብዙ ፈተናዎችን ማለፍ ይጠበቅበታል፡፡ የስራው አድካሚነት እንዳለ ሆኖ ሌሎች በርካታ ፈተናዎችም አሉበት፡፡ ይህን ሁሉ ችግር ፈተና ተቋቁሞ ለውጤት መብቃት ከጦር ሜዳ ድል አድራጊነት ጋር ይመሳሰላል፡፡ የገጠሩ ገበሬ ጠንክሮ ካላረሰ እና ካላመረተ የከተሜውን ቂንጠኛ ጨምሮ የጦር ሜዳው ጀግናም በህይወት አይኖርም፡፡ ይህ ደግሞ የጀግናው ገበሬ የልፋቱ ውጤት ሲሆን ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ ከበሮቹ ጋር፣ ከቤተሰቡና ከአሽከሮቹ ጋር ስሙር ሆኖ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል የመስራቱ ምስጢር ነው በማለት የጀግናውን ገበሬ ታታሪነት ያሳያሉ፡፡ የበሮቹ አይነት፣ የጅራቱ ድምፅ፣ የአራሹ ገበሬ እርፍ አነቃንቅ እንዲሁም ከበሮቹ ጋር በድምፅ መግባባቱና በወኔ መስራቱ ለውጤቱ ምክንያት ሆኖ ይታያል፡፡

ይህ የሚች ገበሬ ታታሪነት በሱ ብቻ አልቆመም፡፡ ቤተሰቡና ማህበረሰቡ ከዚህ ጀግና ገበሬ የሚማረው በርካታ ነገር አለ፡፡ ለምሳሌ ግጥም "ሥ"ን ስንመለከት የዚህ ጀግና ሚስትም ጀግና ናት፡፡ የስራዋን ታታሪነት ከሽረሪት ተግባር ጋር በማመሳሰል ሌት ተቀን መስራቷ ብቻም ሳይሆን የሙያ ብቃቷንም ያሳያሉ፡፡ ይህ ደግሞ ለስራዋ ያላትን ክብርና ፍላጎት ያሳያል፡፡ ያታሪክ እና የልምድ መወራረስን በጦር ሜዳው ጀግና እና ቤተሰቦቹ እንደተመለከትነው ሁሉ በዚህ የስራ ጀግና ማንነት ውስጥም ይንፀባረቃል፡፡

የሱ ደከመኝ ሰለቸኝ አለማለትና ጠንካራ ገበሬ መሆን ሚስቱንም እንቅልፍ ለምኔ አስብሏታል፡፡ ለጀግናው ገበሬ ሌሊት ተነስታ ቁርሱን ማብላትና ምሳውንም መቋጠር እንዲሁም ጠላውን መቅዳት የጥንካሬዋ መገለጫ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አሽከር ኮልኅዩን መመገብ ለገበሬው የስኬት ወሎ ጉልህ ድርሻ አለው፡፡

ከዚህ ግጥም ማህበረሰቡ ብዙ ነገር ይማራል፡፡ ስንፍናን አስወግዶ ቀን ከሌት እንዲሰራና ሰነፉ ገበሬ ከጀግና ገበሬ ጋር ተወዳዳሪ እንዲሆን ከእንቅልፉ እንዲነቃ ያደርገዋል፡፡ በዚህ ማህበረሰብ ውስጥም አራሽ እንደፋራሽ ገበሬ ትልቅ ከበሬታ ይሰጠዋል፡፡ እሱ ብቻም ሳይሆን ቤተሰቡ እና ሚስቱ ትልቅ ክብር ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ ሰው በህይወት ዘመኑ እንዲህ ያለ በማህበረሰቡ አዕምሮ የማይጠፋ እና በእርአያነቱ የሚጠቀስ አርሶ አደር በመሆኑ ከእለታት አንድ ቀን በሞት ሲለይ ማህበረሰቡ ከልቡ ያዝናል፡፡ ለቅሶውም ከሌሎች ሰዎች ለቅሶ የተለየና ሁልጊዜም ሌላ ሰው በሞተ ጊዜ የዚህ ጀግና ስራዎች እየተነሱ በስራ እኩያ የሆኑትም ከሱ ጐን ለጐን ስማቸው እየተነሳ

ማስለቀሻ ሆነው ይውላሉ፡፡ ይህ ደግሞ ማህበረሰቡ እንደዚህ ላሉ ጀግና ገበሬዎች ከፍተኛ ክብር እንዳለውና ሌሎችም በሱ እግር እንዲተኩ ጭምር ያሳስባል፡፡

### 4.2.2.2 የስራ ውጤትን የሚገልፁ ግጥሞች



ምስል 12፡ አቶ ኒታሰው አወቀ ከአቶ እውነቱ ዘለቀ ለቅሶ ላይ ሲፎክሩ

ሀ. ትንሹ ሸርቱ ይደላል ሃምሳ

ትልቁ ሸርፉ ይደላል መቶ በብዙ አህያ ያን ከቶ ከቶ

ከአውድማው ሂዳ አለችው ሚስቱ ሸርፋው ፈንዳ

ተይው ይፈንዳ ይተረትረው

ይወስደው የለ የቸገረው ይላል እውቱ፡፡

ለ. በሬው እንጊታም ላሙ እንብርታም

በሬው እሺታም ላሙ ወተታም

እውነቱ ሞተ እንዴት ያለ ሃብታም፡፡

ሐ. እውነቱ ነበር ጥሩው ገበሬ

ያመርት ነበር ልምና ጥሬ፡፡

መ. እረ ገበሬው ማሩ

ለካም እንተነህ የእለም ሞተሩ፡፡

ሠ. ገበሬንና የጦር አርበኛን ቢያዋዳድሩ

የጦር አርበኛው ሊበላጥ አሰበ

የሱማ ስራ መግደል ብቻ ነው እየተሳበ

ታዲያ ከገበሬው ቤት ካልበላ ማታ

እናጦ እያመለጥ ተኩሶ አይመታ፡፡

ረ. በገር ሲሄዱ በርበሬው ሸንኩርቱ፣

በጓዳ ሲገቡ ማርና ወተቱ፣

ከቤቱ ሲገቡ አታሳፍር ሚስቱ፣

ሃብታሙ ገበሬ ሞተ እሉ እውነቱ፡፡

(አቶ ጌታሰው እወቀ፣ 05/06/2004 ዓ.ም)

ቀድም ባሉት ግጥሞች ውስጥ የጀግናውን ገበሬ ታታሪነት፣ ያሳለፈውን ስቃይ መከራ እና ልፋቱን የሚያሳዩ ግጥሞችን የተመለከትን ሲሆን ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት አምስት ግጥሞች ደግሞ የጀግናውን ገበሬ የልፋት ውጤቱን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በተለይም ግጥም 'ህ'፣ 'ለ' እና 'ሐ'ን ስንመለከት በቀጥታ የገበሬውን የድካም ውጤት የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ይህ ጀግና ገበሬ በእያይነቱ ከማምረቱም ባሻገር የምርቱ መጠን ከፍተኛ ነው፡፡ ምርቱም የሚከተተው በሸርፋ ወይም ጎተራ ነው፡፡ ሸርፋውም ፍንድቶ ምርቱ ቀዬው ላይ ፈሷል፡፡ የጀግናው ገበሬም የልቡ ደርሷል፡፡

በዚህ ጀግና ገበሬም ብቻ ሳይሆን ለዚያ ማህበረሰብም ከዚህ በላይ ጀግንነት የለም፡፡ ቀዬው ላይ የፈሰሰውን ምርትም የቸገረው ይውሰደው ተይው አትጨነቂ ሲል ሚስቱን ያፅናናል፡፡ ምናልባት ወንዱ የሰራውን ሸርፋ ስሙን ጠናት እንጅ በሚስቲቱ እጅ የተሰሩ በርኳታ ጉታዎችም ሙሉ እንደሆኑ ያሳያል፡፡ የምርቱ መጫኛ አህያ ቂጥሩ በርኳታ ነው፡፡ ምርቱ ተጭኖ ወደ ቤት የሚገባበት አቅማዳ፣ መጫኛ እና የሚጭነውን እሸከር ብዛት ማሰብ ይቻላል፡፡ የዚህን ሁሉ አዝመራ ግርድና ገለባ የሚበላው በሬው እና ላሙም፣ ፈረስና አህያውም እንጊታም እና እንብርታም ናቸው፡፡ ከሌላው ሁሉ በተለየ

ሁኔታ ለአይን የሚማርኩ እና አሸትና ወተት ናቸው፡፡ በሬው ጉተራ እስከሚፈነዳ ምርት ይመረትበታል ላሙ ቅቤው ጉረቤትን በሽታ እስኪያነውጥ ድረስ ይታለብበታል፡፡ አህያው ጀንበር እስክትጠልቅ ድረስ ምርት ይጫንበታል፡፡ እነዚህን ጥጋበኛ በሬዎችና ላሞች የሚጠምድ እና የሚያልብ አሽከር ጥጋበኛ ነው፡፡

በመሆኑም የዚህ ጀግና ገበሬ ጀግንነት ደረጃው ከፍ ያለ ነው፡፡ ማንም ጀግና ነኝ ቢል እንደ ገበሬ ጀግና የለም የሚል ይዘትም አለው፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነን ግጥም "መ" እና "ሥ"ን ስንመለከት በነዚህ ሁለት ግጥሞች ውስጥ የሚተላለፉ አብይ ጉዳይ በጦር አርበኛ እና በገበሬው አርበኛ መካከል ያለውን ልዩነት አግዝፎ ማሳየት ነው፡፡ የቱንም ያክል ተኩሶ ቢገድል፣ የቱንም ያክል አየር መኪና ቢያበር፣ የቱንም ያክል ቢማር ቢመራመር፣ የቱንም ያክል ጀግና ነኝ ብሎ ቢፎክር እንደ ገበሬ ጀግና የለም የሚል ትርጉሜ ይዞ እናገኘዋለን፡፡

የገበሬው ህይወቱ በእጁ ነው፡፡ የሌላው ጀግና ነኝ ባይ ግን ህይወቱ በሱ ላይ የተመሰረተ ነው የሚል አንድምታ አለው፡፡ ሁሉም ነገር በእህል ላይ ነው ወታደሩ ለመግደልም ይሁን ሮጦ ለማምለጥ እህል መብላት አለበት፡፡ ያን እህል የሚያመርተው ደግሞ ጀግናው ገበሬ እንጂ ጀግናው ወታደር አይደለም፡፡ ታዲያ የጀግኖች ሁሉ ጀግና ገበሬ ነው በማለት ያረጋግጣል፡፡ ለዚህ አርሶ አደር ትልቅ ክብር እንዲሰጠው በማድረግ ገበሬውም ለካም ማረስ እና ማምረት የጀግና ስራ ነው በማለት ከጊዜ ወደ ጊዜ የስራው ፍቅር እያደረበት በወኔና በሞራል እንዲያመርት፣ እንዲሰራ ይረዳዋል፡፡ ሰነፉም ብርቱ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

በማህበረሰቡ ዘንድ እንደዚህ አይነት ግለሰቦች ትልቅ ቦታ ይሰጣቸዋል፡፡ ማህበራዊ ደረጃቸውም ከፍ ያለ ነው፡፡ ሲሞቱም ለቅሷቸው ከሌላው በተለየም የሞቀና የደመቀ ሆኖ እንባ ሲያራጭ ይውላል፡፡ ከመላቀሱ ባለፈ ያ ማህበረሰብ በነዚህ ግጥሞች አማካይነት የስራ ሞራሉንና ተነሳሽነቱን ይጨምራል፡፡ የለቅሶው ዋና አላማውም የቀረውን ማህበረሰብ ኑሮ ማጠናከርና ክባዱን ኑሮውን ማቅለል ነው፡፡



ምስል 13፡ አቶ ማሩ አሰፋ ከአቶ እውነቱ ዘለቀ ለቅሶ ላይ ሲፎክሩ

### 4.2.2.3 እንግዳ ተቀባይነትን የሚገልፁ ግጥሞች

ሀ. ከፍ ከፍ ያለ ከምር ከግሬ
ሠላማ እንግዳ ቤት አሳዳሪ
ወረዳ እውራጃ ቤት አሳዳሪ።

ለ. ምን ኢህአዴግ፣ ምን ደርግ ቢሆን ምን መቶ አለቃ
ከነ እውነቱ ቤት ካልበላ ማታ
ፋኖ እያመልጥ ተኩሶ አይመታ።

ሐ. ከነ እውነቱ አዳራሽ እረ የኪዳነምህረት
እረ የማርያም ዕለት ሞልቶ ነበር ብዙ ዝልል
በል ብላ ጠጣ በል ተዛለል
ከፉ መሰረት ነው ነብስ መግደል
እያነፍርም ሰርቶ ማደር ይላል እውነቱ ዘለቀ።
(አቶ ማሩ አሰፋ፣ 16/05/2004 ዓ.ም)።

መ. ሞሰቡ ዘገር ባለ ወትራት

ምግ ተበልቶ ሲደገም እራት

በይ አክደበት ጨምሪ ሲላት

ሚስቱም ሸጋ ናት ታከራዋለች

ሁሉን በዓይኑ ተሸኛዋለች፡፡

ሠ. እውነቱ ዘቀለ የላመ ጌታ፣

የበሬ ጌታ የቀሮው ጌታ

ገባ ከማጀት አሰለሰለ

ጠላ ሊያመጣ ጠጅ የመሰለ፡፡

ረ. የምን ሰዎች ናቸው ይጣራሉ አለ ወይዘሮ በለጡን

ብቅ በይና ግቡ በያቸው

ፈገግ ፈገግ በይላቸው

በእይነት በእይነቱ አቅርቢላቸው

ይብሉ ይጠጡ ይስ ካላቸው

ይዘው ይሂዱ ከቸገራቸው ይላል እውነቱ ዘቀለ፡፡

ሰ. ከነ እውነቱ ቤት እንግዳ መጣ

ስንት እንገዳነው አለች በለጡ አሸናፊ

ስንት እንግዳነው አምስት እንግዳ

እንኳንስ አምስት ይሁን ሃምሳ ሰው

አይጠፋብኝም እኔ ያንተ ሚስት ስጠነስሰው፡፡

(አቶ ያረጋል ተመስገን፣ 16/05/2004 ዓ.ም)፡፡

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ግጥሞች ይዘት ስንመለከት የሚችን እንግዳ ተቀባይነት ያሳዩናል፡፡ ጀግናው ገበሬ የቱንም ያህል ይድከም፣ የቱንም ያህል ያምርት የጀግንነቱ ልክና ደረጃ የሚታወቀውና የሚመሰከርለት በቤቱ በያይነቱ ሲያበላ ሲያጠጣና ለቸገረው ሲሰጥ ነው፡፡ ይህውም በሚስተናገደው የእንግዳ ብዛት፣ በሚስተናገደው የእንግዳ

ማህበራዊ ደረጃ፣ በሚቀርብለት የምግብ አይነት እና በሚሰጠው አክብሮት ይመዘናል፡፡ አሁንም በነዚህ ግጥሞች ውስጥ ጎልቶ የሚታየው የገበሬው ጀግንነት ነው፡፡

የሚስተናገደውን የእንግዳ መጠን ስንመለከት በአንድ ጊዜ ከሠላሳ በላይ ሊሆን ይችላል፡፡ የእንግዶችን ማህበራዊ ደረጃ ስናይ ደግሞ የተከበሩ፣ የታወቁና የወረዳ አውራጃ ገዥዎች ናቸው፡፡ የሚስተናገዱትም ለአንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ይችላል፡፡ ምሳ በልቶ እራት ወይም እራት በልቶ ምሳ ሊደገም ይችላል፡፡ ለዚህ ደግሞ ምንም እንኳን የጀግናው ገበሬ ሃላፊነት ጥሮ ግሮ ምርቱን ከጐተራው ማስገባት ቢሆንም ሚስቱም የማጀቱን ሃላፊነት በመወጣት ታኮራዋለች፡፡ ሳይታሰብም እንግዳ ቢመጣ እሷ ሁሌም ዝግጁ ናት፡፡ ምክንያቱም የጀግናው ቤት ያለ እንግዳ ሊውል ሊያድር አይችልምና፡፡ ይህ ደግሞ የጀግንነቱ አንዱ መለኪያ መሆኑን ያሳያል ፡፡

የሚስቱም ጀግንነት የሚገለፀው በመልኳ እና በአካላዊ ቁመናዋ ሳይሆን ይችላል፡፡ ባላት ሙያ እና እንግዳ ስቦ ተቀብላ በማስተናገድ ብቃቷ ነው፡፡ ማንኛውም ወታደር ጠላት ሊገድልም ይሁን ሊማርክ የሚችለው ከገበሬው ቤት ያገኘውን አቅን ሲሸር ነው፡፡ ጥሬም ይቆርጥም፣ አተንትም ይጋጥ፣ ጉመንም ይጭመቅ ብቻ ያለ ገበሬ ሁሉም ነገር ከንቱ ነው የሚል ይዘት አለው፡፡

በተለይ በግጥም 'ሐ' የተገለፀውን ሃሳብ ስንመለከት የማህበራዊ ተሳትፎው ጥንካሬም ይሁን ደረጃው ከፍ ያለ ነው፡፡ እንግዳው የሚስተናገድበት ቀን ሲመርጥ የማርያምና የኪዳነ ምህረት፣ እንግዳው ከብዛቱ የተነሳ የሚስተናገደው በቤት ውስጥ ሳይሆን በአዳራሽ ውስጥ፣ የሚበላውና የሚጠጣውም በየአይነቱ ነው፡፡ በነዚህ ግጥሞች ውስጥ ከፍተኛ ማህበራዊ መስተጋብር ይገለፃል፡፡

ሌላው ደግሞ በግጥሞቹ ውስጥ የታየው ትልቅ የስነ ምግባር ትምህርትን መስጠት ነው፡፡ በርግጥ ጉዳዩ መብላት ማጠጣትና ደስታን ማድረግ ቢሆንም ለዚህ ትልቁ መሠረት ስራ ነው የሚል ትርጓሜ ይዘው እናገኛቸዋለን፡፡ መስረቅ ነብስ መግደልና መዋሸት አፀያፊ ድርጊቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህን ያልተፈለጉ እና በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸው ጉዳዮችን ባህሪይ እንዳይደረጉ ያሳስባል፡፡ በሌላ ምልኩ ለስራ ከፍተኛ ክብርና ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ይመክራል፡፡

## 5. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ትኩረት በደብረታቦር ከተማ በለቅሶ ላይ የሚገጠሙ የወየታና የቀከራ ግጥሞችን ከዋኔና ይዘት ትንተና ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ግጥሞቹ በሚከወኑበት ጊዜና ሥፍራ በመገኘት ተሰብስበዋል፡፡ መረጃው ከጽሑፍ መጠይቅ በስተቀረ ሌሎቹን ዘዴዎችን እንደየአስፈላጊነቱ መጠቀም ተችሏል፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ሥራ ላይ ሲውሉ በመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች እንዲታገዙ ተደርጓል፡፡ ጥናቱ የሁለት ሴቶችንና የአራት ወንዶችን በድምሩ የስድስት ሰዎችን የለቅሶ ከዋኔ ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ በሁለቱ ሴቶች የለቅሶ ከዋኔ የተቀባቀዘና አብዛኛዎቹ የለቅሶ መገለጫዎች ያልታዩበት ባንፃሩ በመዝሙርና ምስጋና የታጀበ ነበር፡፡ ለዚህ ደግሞ በምክንያትነት የቀረበው ሁለቱም ሴቶች የሚከተሉት እምነት የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት በመሆኑ ማልቀስም ሆነ ግጥም መደርደር በሃይማኖታዊ ስርዓቱ ከልከል መሆኑ ነው፡፡

በሌሎቹ ሁለት ወንዶች የለቅሶ ከዋኔ ላይም የተወሰኑ የወየታ ግጥሞች ከመደርደራቸው በስተቀር ከዋኔውም የተቀዛቀዘ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ የሚያሳየው የግለሰቦቹ ማህበራዊ ደረጃ ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡

የተረፉቹ የሁለት ለቅሶዎች ከዋኔ ደግሞ ከሁሉም ከዋኔዎች የተሻለና በርካታ የወየታና የቀከራ ግጥሞች የተሰበሰቡባቸው ናቸው፡፡ የእነዚህ ሁለት ወንዶች የለቅሶ ከዋኔና የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች በዚህ ጥናት የተተኮረባቸው ናቸው፡፡ ከነዚህ ውስጥም በአንደኛው የጦር ሜዳ ጀግንነቱን መሠረት ያደረጉ ግጥሞች የተደረደሩ ሲሆን በሁለተኛው ላይ ደግሞ በአርሶ አደርነት ጀግንነቱ ላይ ተመርኩዘው የተከወኑ ናቸው፡፡ በነዚህ በሁለቱም ሟቾች የለቅሶ ከዋኔ ላይ የአሊቃሹ መውደቅ መነሳት፣ ደረት መደለቅ፣ ፊት መቧጠጥና ጉጣጊዎቹም ተራ ሳይደርሳቸው እኔ እገጥም እኔ እገጥም እያሉ ሲሽቀዳደሙ የታዩባቸው ስለሆኑና የተሻ ለ ፎክሎራዊ ከንዋኔዎ ችን ማሳየት የቻሉ በመሆናቸው ለዚህ ጥናት በማሳያት ተመርጠዋል፡፡ ይህ ደግሞ ሟች ግለሰቦች በማህበረሰቡ ዘንድ ምን ያክል ተቀባይነት ያላቸውና ማህበራዊ ደረጃቸውም ከፍ ያለ መሆኑን ያሳያል፡፡

ከግጥሞቹ መረዳት እንደተቻለው የወየታ ግጥሞችም ሆነ የፉከራ ግጥሞች የመከወኛ አጋጣሚያቸው ለቅሶ በመሆኑ አንድ ይሁኑ እንጅ የአከዋወን ሂደታቸውና በታዳሚው ላይ የሚፈጥሩት ስሜት የተለያየ መሆኑን ጥናቱ ጠቁሟል፡፡ የወየታ ግጥሞች ከሃይማኖት አባቶች በስተቀር በማንኛውም ሰው ለቅሶ ላይ ይከወናሉ፡፡ ነገር ግን ይዘታቸውን ስንመለከት አልቃሿ አፏን ከፍቶ "ዋይ" ብሎ በማልቀስ ሃዘኑና ብሶቱ እንዲወጣለት የሚያደርጉ ናቸው፡፡

በአንፃሩ የቀረራ ግጥሞች ደግሞ የሚገጠሙትም በአብዛኛው ለጀግና ወንዶች በመሆኑ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች አይወክሉም፡፡ ጀግኖች የሰሯቸውን ስራዎችና የፈፀሟቸውን ጀብዶች እንዲሁም ያሳለፏቸውን ውጣ ውረዶች በማንሳት ታዳሚው ጀግንነትን፣ አርበኝነትን፣ እንዲሁም ፅናትንና ብርታትን በዕዝነ ልቦናው እንዲያስብና ከማዘን ይልቅ ወኔና ሞራልን በውስጡ እንዲያሳድር የሚያደርጉ ናቸው፡፡

በእነዚህ የለቅሶ ቀረራ ግጥሞች አማካይነት ከተለያየ አካባቢ የመጣው አልቃሽ የሟችን ቤተሰብም ይሁን ሟች ያደገበትን ማህበረሰብ ቢጋብዝ፣ በክርስትና፣ እና በተለያዩ ግንኙነቶች ዝምድና ለመፍጠር ይፈልጋል፡፡ በሟች ቤተሰብና በዚያ ማህበረሰብ ስምና ዝና መጠራትም የማይፈልግ የለም፡፡ በመሆኑም የቀረራ ግጥሞቹ በዚያ ማህበረሰብ ውስጥ በአብዛኛው የሚፈጥሩት ስሜት የጀግንነት፣ የአርበኝነት፣ የተፈሪነት፣ የአዋቂነት፣ የታታሪነት ነው፡፡ እነዚህን ስሜቶች በዚህ የለቅሶ አውድ አማካይነት በመተላለፋቸው ሰው ሆይ እንዲህ ሞት ሳይቀርልህ ሀገርክን፣ ወገንክንና ቤተሰብክን ከጠላት፣ ከርሃብና ከሌሎች ችግሮች ጠብቅ፣ አለኝታ መከታ ሁን የሚል አንድምታ እንዳላቸው ጥናቱ አመላክቷል፡፡

የለቅሶ ቃል ግጥም ሲነሳ የወየታ፣ የሙሾና የቀረራ ግጥሞች በግንባር ቀደምትነት ይታወሳሉ፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥም ትኩረት የተደረገባቸው የወየታና የፉከራ ግጥሞች ቢሆኑም በቃለ መጠይቅ ላይ በተገኘው መረጃ መሰረት የሙሾ ግጥሞችን ምንነትና ከወየታና ቀረራ ግጥሞች ጋር ያላቸውን አንድነትና ልዩነት ለማየት ተሞክሯል፡፡

የሙሾ ግጥሞች የከዋኙ ሂደታቸውም ይሁን የሚያስተላልፉት መልዕክት ከወየታና ከቀረራ ልዩነት አላቸው፡፡ ልዩነቶቹም ግጥሞቹ በወንዶች ብቻ የሚወርዱ እና በቡድን የሚከወኑ መሆናቸው፣ የግጥሞቹ ይዘት በቀጥታ ሟችን ሳይሆን በአጠቃላይ የሰው ልጅን

ክንቱነት የሚያሳዩ፣ ይህን ክንቱነት ተከትሎ ፈጣሪን የሚያማርሩና በአንድ የለቅሶ ክዋኔ ሦስት ጊዜ ብቻ የሚከወኑ መሆናቸው ነው፡፡

ይህ ጥናት በደብረታቦር ከተማ የለቅሶ ክዋኔ ምን እንደሚመስል፣ የወየታና የቀከራ ግጥሞች የሚያስተላልፉት ቁም ነገር ምን እንደሆነ፣ በወየታ፣ ሙሾና ቀከራ ግጥሞች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ምን እንደሚመስል፣ ለቅሶ በዚያ ማህበረሰብ ውስጥ ያለውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ፋይዳ ምን እንደሆነ ገልጿል፡፡ በወየታና ሙሾ ግጥሞች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በማሳየት የለቅሶ ቃል ግጥሞች የወየታ፣ የሙሾና የቀከራ ግጥሞች በሚል በሦስት መንገድ ከፍሎ ማጥናት እንጂ ሁሉንም በሙሾ ግጥም ጠቅልሎ ማጥናቱ ተገቢ አለመሆኑን ጠቁሟል፡፡ ገጣሚዎችን በተመለከተም ከከተማው ነዋሪዎች ይልቅ በከተማው ዙሪያ የሚመጡ የገጠር ነዋሪዎች ሚናን እንደሚይዙ አመላክቷል፡፡ ነባሩ የማህበረሰብ ማንነትም ሆነ የፎክሎር ተግባራዊነት የሚንፀባረቀው በዚሁ የገጠር ነዋሪዎች መሆኑን በክዋኔዎቹ አከዋወንና በግጥሞቹ ድርደራ ላይ መገንዘብ ተችሏል፡፡ በዚህም የከተማውና የገጠሩ ማህበረሰብ ማህበራዊ ትስስር እጅግ ጠንካራ መሆኑን ጥናቱ ጠቁሟል፡፡

ሌላው የለቅሶው ክዋኔ ከ10 ሰዓት ወደ 4 ሰዓት እንዲያጥር መደረጉ የፎክሎር ሃብት በሆነው የለቅሶ ስነ ቃል መፈጠር ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያለው መሆኑን መመልከት ተችሏል፡፡ ምክንያቱን ሲገልፁም መንግስት ጊዜንና ጉልበትን ከመቆጠብ ጋር አያይዞ ጊዜው እንዲያጥር መወሰኑንና ከአራት ሰዓት ካለፈ የንስሃ አባቶች ፍታት እናደርግም፣ እንቀብርም እያሉ እንደሚያስቸግሩ ጭምር መረዳት ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮችና በሌሎቹ የሙስሊምና የአድቬንቲስት ተከታዮች መካከል የለቅሶ ክዋኔ ልዩነት መኖሩን መገንዘብ ተችሏል፡፡ ምክንያቱም በሙስሊምና አድቬንቲስት እምነት ተከታዮች የሙሾ፣ የወየታም ይሁን የቀከራ ግጥሞች አይደረደሩም፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት በሃይማኖታዊ ሥርዓቱ ክልክል መሆኑን ተከትሎ ነው፡፡

# ቀቢዎች


ጌሙልስ አክሊሉ፣ "የቋሬት ወረዳ የለቅሶ ሥነ ሥርዓትና የለቅሶ ግጥሞች ይዘት ትንተና"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ ዲግጽ፣ 1997፡፡

ባህሩ ዘውዴ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847-1983*፣ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማተሚያ ቤት፣ 2003 ዓ.ም፡፡

ታደሰ መንግስቱ፣ "የጎጃም የለቅሶ ግጥም"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ዲግዕ፣ 1963፡፡

ኪዳነ ወልድ *ክፍሌ፣ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ*፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣148፡፡

ካሳው ደሳለው፣ "የደብረሲና ወረዳ የለቅሳ ሥርዓትና የሙሾ ግጥሞች ይዘት ትንተና"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ዲግጽ፣ 1997፡፡

ደስታ ተክለወልድ፣ *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት*፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962፡፡

ወርቁ ማንደፍሮ፣ "በሊቦ ከምከም ወረዳ የለቅሳ ስነ-ስርዓትና የሙሾ ግጥሞች"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ ዲግጽ፣ 1987፡፡

ወርቅነሽ ደምሰው፣ "ጀግና ወንዶችና ሴቶች ሲሞቱ የሚደረደሩ የለቅሶ ግጥሞች /በእቺፈር ፀሬያ ወረዳ"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ ዲግጽ፣ 1992፡፡

ጌጤ ታደሰ፣ "ከዋኔ በጎንደር ከተማ ለቅሶ ስነ ስርዓት"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ ዲግጽ፣ 1989፡፡

ዘሪሁን አስፋው፣ *የሥነ ጽሑፍ መሰረታውያን፣ ሦስተኛ ዕትም*፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1998፡፡

ፈለገ ሕይወት ዘገዬ፤ "በንጂ ጄኬዳድ ወረዳ የቀብር ሥነ ሥርዓትና የለቅሶ ግጥሞች ስብስብ ይዘት ትንተና"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፤ዲግሪ፤ 1997።

ፈለገ አስምሮ መጽሔት፤ የደብረታቦር ከተማ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ያሳተመው 1991።

ፈቃደ አዘዘ፡ ለፋዊ ሲንት ቃል፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ መጽሔት ቁ. 2፤ 1984።

__________ ፈቃደ አዘዘ፤ የስነ ቃል መምሪያ፤ ኢንተርናሽናል ጀመርናዊ የጎልማሶች ትምህርት መረጃ ተቋም ታተመ፤ 1991።

Bauman, Richard. *Story, Performance, and Event: Contextual Studies of Oral Narrative.* 1986. USA: Cambridge University Press, 1988.

__________. *Cultural Performances and Popular Entertainments.* New York, New York University Press. 1992.

Ben-Amos, Dan. *Introduction: Folklore in Africa Society.* In Bernth Lindfors, ed. Forms of Folklore in Africa: Narrative, Poetic Gnomic, Dramitic. Austin: University of Texas Press, 1977.

Dorson, Richard M. ed. *Folklore and Folk Life:* An Introduction. Chicago Press. 1972.

Fekade Azeze. *Unheard Voices*: Drought, Famine and God in Ethiopia Oral Poetry Addis Ababa. Addis Ababa University Press, 1988.

Finnegan, Ruth *Oral Poetry, Its Nature, Significance and Social Context.* New York: Cambridge University Press, 1977.

_____ *Oral Literature in Africa.* Nairobi: Oxford University Press, 1998.

Goldstin, Keeneth. S.A *Guide for Filed Workers in Folklore.* Pennsylvania: Folklore Associates Inc, 1964.

Hertiz, Robert. *Death and the Right Hand.* Trans. Rodney and Needham, Claudia. Aberdeen: Aberdeen University Press. 1960.

Hufford, Mary. *The Journal of American Folklore*, Vol. 108, No. 430, Common Ground; Key Words for the Study of Expressive Culture. (Autumn, 1995), pp. 528-549.

Lord, Albert B. *The Singer of Tales*. Cambridge: Harvard University Press, 1960.

Sims C. Martha and Martine Stephens. *Living Folklore: An Introduction to the Study of People and their Traditions.* Ohio: Utah state University Press, 2005.

Okpewho, Isidore, *African Oral Literature: Backgrounds, Character and continuity.* Bloomington: Indiana University, Press 1992.

## የቁልፍ መረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

| ተ.ቁ | ስም | የመኖሪያ አድራሻ (ቀበሌ) | ዕድሜ | የስራ ሁኔታ | ፆታ | መረጃ የተሰጠበት ቀን | የተሰጠው መረጃ ዓይነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ሞላ ተረፈ | 03 | 52 | የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ባለሙያ እና የሰሞ ገበያ እድር ሊቀመንበር | ወ | 12/05/04 ዓ.ም | ስለ ወየታ፣ሙሾና ፉከራ ቃ/መጠይቅ መረጃ የሰጡ። |
| 2 | አቶ ተሾመ ወበቱ | 02 | 47 | ነጋዴ | ወ | 20/05/04 | ስለ ወየታ፣ሙሾና ፉከራ ቃ/መጠይቅ መረጃ የሰጡ። |
| 3 | አቶ አለምነው አሉላ | 02 | 76 | ጡረተኛና የአጀባር እድር ሊ/መንበር | ወ | 20/05/04 | ስለ ወየታ፣ሙሾ፣ ፉከራና ስለሚገጠምላቸው ሰዎች መረጃ የሰጡ |
| 4 | አቶ ሳህሉ መለስ | 02 | 53 | ነጋዴ | ወ | " | ስለ ወየታ፣ሙሾ፣ ፉከራና ስለሚገጠምላቸው ሰዎች መረጃ የሰጡ |
| 5 | አቶ ብርሀን መንግስቱ ተሻገር | 02 | 76 | ጡረተኛ እና የሕብረት እድር ሊቀመንበር | ወ | " | ስለ ወየታ፣ሙሾና ፉከራ ቃ/መጠይቅ መረጃ የሰጡ። |
| 6 | አቶ አርቅይሁን በላይ | 02 | 47 | የወረዳው ባህልና ቱሪዝም የልማት አፊሰር | ወ | " | ስለ ወየታ፣ሙሾ፣ ፉከራና ስለሚገጠምላቸው ሰዎች መረጃ የሰጡ |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | አቶ ያረጋል ተመስገን | ፀጉር ኪዳነምህረት | 55 | አርሶ አደር | ወ | " | ቃለ መጠይቅ እና ግጥሞችን የሰጡ |
| 8 | አቶ ታከለ ንጋቴ | ሰላምኮ ጊዮርጊስ | 52 | አርሶ አደር | ወ | 05/06/04 ዓ.ም | ቃለ መጠይቅ፣ የቡድን ውይይት እና የወየታ ግጥሞችን የሰጡ |
| 9 | አቶ ሃብታሙ ሙላለ | 04 | 40 | ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የስነ ጽሑፍ ኦፊሰር | ወ | 05/06/04 ዓ.ም | የቃለመጠይቅ መረጃ የሰጡ |
| 10 | አቶ ጌታሰው አወቀ | ፀጉር ሚካኤል | 65 | አርሶ አደር | ወ | 16/05/04 ዓ.ም | ቃለመጠይቅ እና ግጥሞችን የሰጡ |
| 11 | አቶ ማሩ አስፋ | ፀጉር ኪዳነምህረት | 63 | አርሶ አደር | ወ | 16/05/04 ዓ.ም | የወየታ እና የፉከራ ግጥሞች የሰጡ |
| 12 | አቶ አብርሃም ዘለቀ | ሰላምኮ ጊዮርጊስ | 47 | አርሶ አደር | ወ | 05/06/04 ዓ.ም | ቃለመጠይቅ እና ግጥሞችን የሰጡ |
| 13 | አቶ መኮንን ከፍአለ | 02 | 56 | የደቡብ ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ሃላፊ | ወ | 05/06/04 ዓ.ም | ስለ ወየታ፣ ሙሾ እና ፉከራ ቃለመጠይቅ የሰጡ |
| 14 | አቶ መሳፍንት ማስረው | 04 | 65 | ደ/ታቦር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ባለሙያ | ወ | 05/06/04 ዓ.ም | ቃለመጠይቅ መረጃ የሰጡ |
| 15 | አቶ ነጋ ዘላለም | ሰላምኮ ጊዮርጊስ | 54 | አርሶ አደር | ወ | 05/06/04 ዓ.ም | ቃለመጠይቅ መረጃ የሰጡ |

# ቁልፍ ያልሆኑ መረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

| ተ.ቁ | ስም | የመኖሪያ አድራሻ (ቀበሌ) | ዕድሜ | የስራ ሁኔታ | ፆታ | መረጃ የተሰጠበት ቀን | የተሰጠው መረጃ ዓይነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ አዱኛው አብቴ | ፀጉር ኪዳነምኅረት | 62 | አርሶ አደር | ወንድ | 16/05/04 | የወየታና የፉከራ ግጥሞችን የሰጡ |
| 2 | አቶ ባንታየሁ የማታ | አባእረጋይ | 45 | አርሶ አደር | ወንድ | 16/05/04 | የወየታና የፉከራ ግጥሞችን የሰጡ |
| 3 | አቶ ሞገስ ፀጋው | መልዛ | 47 | አርሶ አደር | ወ | 05/06/04 ዓ.ም | የወየታ እና የፉከራ ግጥሞችን የሰጡ |
| 4 | አቶ ለገሰ እምሩ | መልዛ | 52 | አርሶ አደር | ወ | 05/06/04 ዓ.ም | የወየታ እና የፉከራ ግጥሞችን የሰጡ |
| 5 | አቶ ወንድወሰን አበበ | መልዛ | 62 | አርሶ አደር | ወ | 05/06/04ዓ.ም | የወየታ እና የፉከራ ግጥሞችን የሰጡ |

## አባሪ -1 የግጥሞች ስብስብ

### I. የወየታ ግጥሞች

1. አፋልጉኝ ወገኔ በገ በገላ ተከዜ ድረስ
   መፈለጉን እማ ፈልገን ነበር
   እንደ ወረደ ያለ ሰው አጥተን ቀረን።
2. እንቺ አለም ዋሾ እንቺ አለም አታላይ
   ከነ ወረደ ቤት አልነበረሽም ወይ።
3. ጠላው ተዘንብሎ እንጀራው ተቀረቦ
   ሲባላ ሲጠጣ ሰምቼ የታሉ
   እረ እነውነቱ እነ አሻገሬ ሁሉ።
4. ኧረግ አባ ነብሮ ተሰበረ እንደ ቅል
   ጀግና እንደማሻላ ቢዘሩት አይበቅል።
5. ኧረ አባ ነብሮ ያወገዱ ያ ወገዱ
   ታጥቆ ተቀምጧል ባሬም ከጉድጓዱ።
6. ኧረ አባ ነብሮ ወዴት ሄደህ ይሆን
   አገሬ ገላጣ መጫዎቻ ሲሆን።
7. ጠላቶችህ መጡ ከዚያ ላይ ደረሱ
   ተነስ አባ ነብሮ አፍረው ይመለሱ።
8. አንድ ጊዜ ተንስተህ ሁለተኛ መት
   በታውን አይተኸው እንዳደረጉት።
9. ትላት መንፈስ ታሰሮ ከቤቱ ድምድም
   ባጥር በቅሎ ሄደ የኛማ ወንድም።
10. ነፋስ ነፈስ ካባይ እስከ አባይ
    የጀግና ማለቂያው ዘንድሮ ነው ወይ።

11. አባት እየሞተ እናት እየሞተች አንጀት እየሳሳ

ወንድ አልቃሽ ይሆናል በዚህ የተነሳ።

12. አገር መነመነ እረ አገሬ ሳሳ

እንደ ጤፍ እንጀራ እንዳንዱ ተነሳ።

13. የጌማ ዘመዶች ፀጉራቸው ማማሩ

ወዲያው ለመቆረጥ ምነው ባልተሰሩ።

14. አንት የወንድም ዋሾ አንት ቃል አባይ

አብረን እንከርማለን አላልከኝም ወይ።

15. አንድም የወለደ ሁለትም የወለደ

አላሳደገውም እየማለው ሄደ።

16. አንበሳውን ጉበዝ አንበሳ ታግሎት

ሳይነሳ ቀረ ከወደቀበት።

17. የዘንድሮው ወራት የሳት የገለባ

የታመመው አይድን የወጣው አይገባ።

18. የመስከረም አደይ የጥቅምት አበባ

የታደለ መሬት አንተን የሚበላ።

19. ከቤተክርስቲያን ከሆን ዱለቱ

እኛም ወደዚያውነን ሰው ወዳለበቱ።

20. ሞትማ ሙት እንጅ ከማን ትበልጣለህ

እንዲያው እሚሚትህ ታሳዝነኛለህ።

21. እስቲ ቀስ እስቲ ቀስ ምን ያስቸኩልሃል

እንዳይመሽብህም ማለደህ ተነስተሃል።

22. እንግዲህ አልዘራም ደህና ጤፍ በአገሬ

እየሞተ አለቀ ደኛደኛው በሬ።

23. ቤት ሰርተው ነበር ለመሸጋገሪያ

ጥለውት ሄዱ እንጅ ለእሞራ ማደሪያ።

24. ጊዜ መቸገዲስ ነው ያድሳል ያፈርሳል

እንዱ ሲያሸበርቅ እንዱን አፈር ያለብሳል።

25. እረ አገሬ ፀጉር በወይፈን ታረስ በጥጃ ታረስ
አንድ በሬ ነበር ዛሬ ተጨረሰ።

26. እንደዚያም እንደዚያም እንዳካባቢያችን
እንደ ጎረቤት
አመትባል ሲመጣ ይከጻል አባት።

27. በኃይለ ስላሴ በበሬ ታረስ
እረ በመንግስቱ በግናኝ ታረስ
እረ በኢህአዴግ መሬቱም አነሰ
በወይፈን ታረስ በጥጃ ታረስ
አንድ በሬ ነበር እወኑቱ ነበር ዛሬ ተጨረሰ።

28. አይን አልነበረም ወይ የናፍቆት መገለጫው
ወንድሜ የትሄደ ከመቀመጫው።

29. ሙግት አይደኗን ታማ፣ ስርዓት አይደኗን ታማ
ወላለች ከመንደር
መላኩ ከበደ መንግስቱ ከበደ እነሱ ተቀብረው የስርዓቱ መምህር።

30. በላሲታ አንድ ሰው መጣ
በፈርማ አንድ ሰው መጣ
ቢጎደንትአንድ ሰው መጣ
በነገደር አንድ ሰው መጣ
በደብረታቦር አንድ ሰው መጣ
ከግልቀስ በስተቀር ሞት የሚያድን ታማ።

31. ምንም ሃብታም ቢሆን ቢያበላ ቢያጠጣ
አወይ የሰው ነገር ተመልሶ ጭቃ።

32. መኪታዋ ብየ እኔ ባኖርህ
በየትኛው መብራት ፈልጎ አገኘሁ።

33. አደባባይ ቆሜ የሚዋሰኝ ባጣ
ምድርምድርእየሁቆፍሬላወጣ።

34. ገልገል በቅሎ ገዛሁ ከዋጋ ቀጥዬ
መቼም አባት በቅሎ አላገኝም ብዬ።

35. ባቴላው ነቀዘ የእህሉ ንጉስ
ማን ይነግረን ይሆን የኛ ቀን ሲደርስ።

36. መንግስት ልክ ነበር አድርጎ በእቆጆ
እንዲያው ውስጥ ለውስጥ አይጥፈጀው እንጆ።

37. ጀግናነኝ አላልከኝ የታል ጀግንነቱ
እንግዲያ ከር አይደል የታሰርክበቱ።

38. ይህንን ማርገጃ በበሬ እንረሰው
በመቆፈሪያውስ አላበቀለም ሰው።

39. አንድ ገንቦ ጠላ አትፌያለሁ ከቤት
እረ እናንተ ሆዬ ሰውን ጠማው መሬት።

40. እናንት ወዳኛ አትጠረጥሩም
እኛ ወዳናንተ ምን ቢሆን አንቀርም።

41. አባት የሌለው ልጅ ንብ የሌለው ቀፎ
እኛጋር ይታያል አበባው ረግፎ

42. አዲስ ልብስ ግዛልኝ ብላ እንደማስቸገር
ሰኔል ለብሳ ሄደች ከማታውቀው አገር።

43. ከላይ ቤት መስራት ነው እልፍኝ አዳራሽ
የመሬቱስ ነገር ቀሪ ነው ፈራሽ።

44. እኛና መሬትስ ታረቅን በመላ
ዛሬ እኛ በልተናት ኋላ እሷ ልትበላ።

45. እግሬንም በወጋኝ፣ እጅንም በወጋኝ
ዛሬስ መዋጫዬን ጉሮሮዬን ዘጋኝ።

46. ወየው ወይ እድሌ ደረሰብኝ ቀኑ
ነብሌና ሲጋዬ ሳይመዛዘኑ።

47. ዘወር ብዬ ባየው ከበስተኋላዬ
አፈር መስሎ ታየኝ የገዛ ገላዬ።

48. የዘንድሮ ሰውስ ምንኛ አዳገባ

ሊትሰም ወንፈል ሆነ እንደ ጤፍ አጨዳ፡፡

49. የአባታለም ችግሮች እነዚያው ሁለቱ

አንዱ የማሩ ነው አንዱ የወተቱ፡፡

50. እረ ሰው ሞኝ ነው ይባላል ከመንጋው

በመከራ ጊዜ አብሮ ከሚያነጋው፡፡

51. አይኔ አለቀሰ ሆዴም ምን ይበጀው

በዛ ትልቅ ቁንጫ አስፋን የፈጀው፡፡

52. አልቅሳለሁ እንጅ ደግሜ፡ ደግሜ

ቀን ያልታወቀ እድሜ ተሸከሜ፡፡

53. ኧረ እነዚህ ቄሶች ማገን ያቀኛሉ

አሥረው እየጎዱ ፈታት ነው ይላሉ፡፡

54. በል እንባየ ውረድ ከመሬት ድረስ

አይሁዳን መሆን ነው በልቶ አለማልቀስ፡፡

55. በርየውም ይጠመድ ጀምበርም ይጠመድ

እነስ የምወደው ኮከብ ባይጠመድ፡፡

56. እገሌ ቢንቀጠቀጥ አይኔ ሰው ቢፈራ

እንዴት አደርጋለሁ ዝለሌ ነውና ሥማየ ነውና፡፡

57. አደራሽ ትልቅ እርሻው ወለሉማ

ዘር የለሁም አሉኝ ዛሬማ ብሥማ፡፡

58. የቤተስኪያን ጓሮን በበሬ እንረሥው

እኛ የቆፈርነው አላበቀለም ሰው፡፡

59. ሥዋ መዳኒአለም ማክሰኛ ማነው

ቀኑን አያውቀውም ያኸ ሁሉ ሰው፡፡

60. እረ የሰው ጉዳይ ምን ይታመናል

ትናንት ያየነው ሰው ዛሬ ይቀበራል፡፡

61. አብዝቸው ነበር ደጅ አዝማችንቱን

ማይጠማኝ መጠጣት ማይርበኝ መብላቱን፡፡

62. እየመለመልን እየሠደድናቸው
   በኋላ በጠባ ይመጣል ምርጂቸው፡፡

63. ወገራን ለስንዴ ወሎን ለገብስ እሸት
   ምን ያደርግልሃል ሁል ጊዜ መዋሸት፡፡

64. ምነው ከቆሻሻው ከጭቃው ወድቃችሁ
   የተጠረገው ቤት ከዚህ አለላችሁ፡፡

65. ወሊዱ ወልደ እግዚአብሔር ሸማኔ ነሪሃል
   ያውም ሸማኔነት ምኑ ይደንቅሀል
   ባንድ ወገን ሥትሰሪው ባንድ ወገኑ ያልቃል፡፡

66. ኧረ ተው ታሪቁ ኧረ ተፋቀሩ
   ወዳጎነት መገቢያው እንዲከፈት በሩ፡፡

67. ከጭሪ ይቀጥናል የሲወል መንገዱ
   ከዚህ ተለቃልቀው ታጥበውት ካልሄዱ፡፡

68. እንዲህ ብለህ ብለህ ና ያልከኝ እንደሆን
   አንተ ብትጠይቀው ምን ይመልስ ይሆን፡፡

69. መቆም አይቀረንም ከሰላሴ ፊት
   መንገዱን ሳናበጅ ግንሰራ ቤት፡፡

70. እስቲ ተመልከቱት የሥላሴን ሥራ
   መልሶ ሲያፈርሰው ጥሩ አርጎ እየሠራ
   ባፈረሰው አትፍሩ ባፈርሰው ሳልኮራ፡፡

71. ሰው ኗሪ ይመስላል ትከ ብለው ሲያዩት
   ለካ አፈር ለአፈር ነው የምንጓጓወት፡፡

72. ስሙኝ ወገኖቹ ስሙኝ ልንገራችሁ
   አፈር ሰው ሁኘነው ቁሜ እምንገራችሁ፡፡

73. አዳም ጭቃ ነሮ የጭቃ ምስሶ
   ሁሉም ሰው ይፈርሳል በፈት አዳም ፈረሶ፡፡

74. አሁን ምን ቢሆን ነው ገነዘብ መያዝ በእጅ
   የዳቢሎስ እራት ለመሆን ነው እንጅ፡፡

75. ምንኛ ደግ ነው መስጠት መመጸወት
ነብሳችን ማትቆም ከስላሴ ፊት።

76. ያንንማዶ ዋርካ ማነው የቆረጠው
እንግዲህ እሸህ ነው የሚያቆጠቁጠው።

77. ያሁን ግዜ ወጣት ዕድሜው አጭር ነው
ገና በእሸቱ ነው የሚታጨደው
ደህንን እያዩ እያዘንም ወይ ሰው።

78. ገና ማያፈራ ወጣት ከታጨደ
አዩ ጉድ የሰው ዘር እየጠፋ ሄደ።

79. በዓለም በኢትዮጵያ የሰው ዘር ነበረ
እየሞተ አለቀ እየተቀበረ።

80. ዝናቡ ዘነበ፣ ዘንቦ ሰማዩ ሲያጠራ
ቡቃያው አረረ ገና ሳያፈራ።

81. ሰው ይሄዳል እንጂ ከመውደቂያው ድረስ
አፈር መቼ ይመጣል ተጭኖ በፈረስ።

82. የላይኛው መንደር ተራማጅነው እሱ
የመጣልን የለም ከሰደድነው ሁሉ።

83. ወንድም ተገንዞ ሲወጣ ተራራ
የዚህ ጊዜ አይደለ ጠላት የሚኮራ።

84. እህል ሆኗአል አሉ ዘንድሮ አገራችን
ማን ይበላው ይሆን አለቀ ሰዎችን።

85. መካን አስማተኛ በኖረኝ ዘላለም
ኧረ እናቴ እናቴ የሚላት ልጅ የለም።

86. አገሬ ምን ሆነ ዘንድሮ አዝመራው
ዛላ ዛላው ወድቋል በየ ጉዳናው።

87. ባትፈው ደንዘዘኝ ምላሴን እንደ እግር
ለካስ ወንድም ኑሯል የልብ የሚናገር።

88. የሞተው ሰው ሳለ የሚበሰብሰው
ምን ያስቸኩለዋል ቀብር የሚመለሰው።

89. ወንዶቹም እንሂድ ሴቶችም እንውጣ

በዚያው ቀሪ ሰው ነው በኛ ቀን እንምጣ።

90. ከቡተሰኪያን ጓሮ ወድቃችሁ ወድቃችሁ

ሲበሰብስ እንጆ ሲበቅልን አያችሁ።

91. ትናንት ጦም ገደፈን እንጀራ በዋዜ

እንዲህ ተሹ ብሹ ለሚደርሰው ጊዜ።

92. እንደ አይን እንደ ጆሮ እንደ እግር እንደ እጅ

የማይለይ ቢሆን እናትና ልጅ።

93. አባቴ እናቴ ወንድሙ እህቴ ለሞተ አላቃሹ ነኝ

እንደ እኔ እንደራሴ አየመሰለኝ።

94. ከባልሽ ተጣልተሽ ዱላ ቢወልብሽ

አባቴን ጥሩ ማለቴ ቀረብሽ።

95. ምንኛ ጥሩ ነው የአባት፣ የናት ጉረቤት

ተበድሮ በልቶ የለኝም ማለት።

96. ኧረ ሞት አጅሬ ሲመጣ በበሩ

ድንገተ ድንገተ ይላል መኳንንቱ ሁሉ።

97. እህት ወንድሞቼ አሌቃችሁ አሌቃችሁ

እኔን የሰው ያለህ ታሰኙኛላችሁ።

98. እባካችሁ ሰዎች ይህንን መከራ እንተጋገዘው

እዞር ይጥላል ብቻውን ለያዘው።

99. የማህሉ ሲያለቅስ የዱሩ ይሰቃል

እንባ ወር ተራ ነው ለሁሉም ይደርሳል።

100. መልካሙን እንገትህን በምን እንመስለው

በሊጋው ሸንበቆ ባልተመለመለው።

101. ጉረቤቱ ሲሞት ያልቅስ ጉረቤቱ

ከማን ይጫወታል ከተዘጋ ቤቱ።

102. ኑሮ በኑሮ ለብሶ ዳር ለዳር ቢዞሩ

ከማህል ያስገባል መከራ ደፋሩ።

103. አባት እናት እየሞተ ልጅ እየተተካ ይለኛል ሰው ሆዬ
አገር አሸጧጣጭ ነው ተተማጭ ካላዬ።

104. የጌግ ወገኖች ዘራቸው ታምስ
መልከም በትሉ ነበር ጠፍ ተመልሶ።

105. አረ ምንከን ምንከን ምንከን ይሰማሃል
ቢቸገር ነው እንጀ ማገስ ያስቀርሃል።

106. እኔ ላልቅስ እንጅ ማን ያልቅስ እላለሁ
መደብ ተደግፌ የጠማሁት ሳለሁ።

107. ባይበላ ባይጠጣ እግር ባያደርሰው
ከመሃል ይገባል የተወለደ ሰው።

108. እስኪ ወየ ልበል ምናልባት ባውቅበት
ሁሉ አሊቃሽ ይሆናል እየደረሰበት።

109. ሞት መጣ ይላሉ በበሩ ዘለቀ
ይሰናል የለም ስንቁን የሰነቀ።

110 ከደጅ አሳድሩት ሞት እንግዳውን
በየሁሉ ደጃፍ የሚያደርሰውን።

111 የመከራ ኸንዴ ተንጥፎ ከቤቴ
ይሀን ሊጠቀልል በኋላ መቅረቴ።

112 እናቱ ደሀና ሁኝ በቀስተ ደመና
እንገናኝ በምድር አትገኝም እና።

113. ኢታንንቀራንቀሩብኝ እንንርጉር አልወድም
በድንገት የወጣ አለኝና ወንድም።

114. እስኪ ሰፈድ ሰጡኝ አፈሩን ላንፍሰው
ምሁሩ ወንድሜ ያነን ሁሉ ቀለም ከምን አደረሰው።

115. ድንጋይ ጨምሩበት ካፈሩ በላይ
አፈርማ እራሱ ሁኖ የለም ወይ።

116. በርችህ ተጠምዶው ከበስለው ላይ
እንዱን ዘር ጥለኸው መሄድህ ነው ወይ።

117. እንጀራው ቢሆን እንደመፈትፈቱ
እንደጠላው ቢሆን እንደመጠጣቱ
ሞት ላንተ ባልሆን ለራብ መድሃኒቱ፡፡

118. እህልም ይበላል ባቂላ መሳይ
ልብስም ይለበሳል ነጠላ መሳይ
እኔስ የምቀና ወንድም ያለው ላይ፡፡

119. እረግ አባታለም ሥፍራ ይዘህ ቆየኝ የተደላደለ
እኔን አይተወኝም አንተን የገደለ፡፡

120. እኔስ ከሰዎቹ ቦታው አሳዘነኝ
ያሳግ መቆያ ሊሆን ነው መሰለኝ፡፡

121. ምነው በዝናቡ ምነው በክረምቱ
ከሰው ቤት ያበራል እንኳንስ ከቤቱ፡፡

122. አምላክ በአንድ ነገር አይጠረጠርም
የከፋው ሰው ሙቶ ደስ ያለው አይቀርም፡፡

123. ምን ነዋ ቢለብሱ ቢመስሉ ጨረቃ
እወይ የሰው ነገር ተመልሶ ጭቃ፡፡

124. የመቃብር ጉድጓድ ወርዷ ሥንዝር ሙሉ
የሚዘላት የለም ካለው ሰው በሙሉ፡፡

125. የተራበን ሁሉ የሚያበላው ገ
አፈር በላው አሉ አባ ባሕርን፡፡

126. የሩሙግዱን የፍትፍቱን ቤት አሞራ አፈረሰው
አይከለከሉም ወይ አብሮ የበላ ሰው፡፡

127. እንደኔት ጀግና ይሙት በምቢያ የሚደቆ
ባለቴቱ ተቀምጦ ወለል የሚያለፋ፡፡

128. በቅሎቹ ግልገሎች አልጨበጥ ባይ
በሮቹ ወይፋፍን አልጠመድ ባይ
እንግዲህ እስለምደህ መሄድህ ነው ወይ፡፡

129. መብላቱም ይቅርብኝ አፈሩን ልብላው
መጠጡም ይቅርብኝ ደሙን ለጠጣው
ከላጀፍ ቁጭ ብለህ ድምጽህን ልስማው፡፡

130. ሰው ከሞተ ወዲያ ከወረደ አንጋዳ
ወዳጁን አይጠቅም ጠላቱን አይጐዳ።

131. እስኪጠይቁልኝ ወንዙን ሳይሻገር
እንዴት ብሎ ሄደ የወገኑን ነገር።

132. በስከ ምስራቅ በኩል ፀሐይ ጨባረረ
ዘር ያላችሁ ዝሩ የኛስ ዘር አረረ።

133. ምስተ እጅህን ታጠብ እራትህን ትበላ
የመስከረም አደይ የመሰለ ገላ።

134. እኩሉ እየሳቁ እኩሉ ያለቅሳል
አለም ሊትቀበር ጉድጓዱ ይማሳል።

135. አባት የሌለው ልጅ ትል የወጋው ቀጋ
ሁል ጊዜ ይኖራል ጐን እንደ ተወጋ።

136. የቀደቁ በቅሎ ኮርቻው ሲመች
መቀመጥ አያውቁም የኛ ቤት ሰዎች።

137. በሉ እናቱም ሂዱ እኛም ወደዚው ነው
ወትሮም መንገደኛ ፊትና ኋላ ነው።

138. አልቅሱ እንላቀስ ለቅሶ ወንፊል ነው
ዛሬ የኛ ቢሆን ነገ የናንተ ነው።

139. አለቅሳለሁ እንጅ የዛሬን የዛሬን
እኔ ምን አውቃለሁ ነገማ መኖሬን።

140. ከላ መነመነ ቀጠነ እንደሰበዝ
ገና በሩቅ ሲያዩት የሚያስፈራው ጉበዝ።

141. ኧረ ወንድም አለም በደረስክ ከጓላዬ
እኩሌ ሳይቆስል ሳይደማ ገላዬ።

142. ወንድም አልኩሽ እንጅ ሲወድቁ የሚወድቅ ሲደሙ የሚደማ
ባድማ መቸ አማሁ እየበላ የሚያማ።

143. ከእኛውስ ባድማ መጃ ከወረሰው
እንዴት ተፈልጉ ይጠፋል አንድ ሰው።

144. ኧረግ አባት አለም ለወየታውማ አለሁህ ልጅህ

አላገዝሁም እንጅ ከአፈር ከድንጋዩ ካለው ከላይህ።

145. እባክህ ገናገሮ እንጀቱን አትሳበው

እሞታለሁ ብሎ ልቡም አላሰበው።

146. አልቅሱ እንላቀስ ልቦናችን ይዘን

መጨረሻው ከታች አፈር እስክትሆን።

147. አልቅሱ እናልቅስ ምንድን ነው ዝምዝሙ

ሙች ያልሞተበት አለ እህት ከወንድሙ።

148. ተቀማጭ ለቋሚ ቋሚ ተወገምጋሚ

ቀይ እገኝሻለሁ ከመሀል ግትቆሚ።

149. ሲወጣና ሲወርድ ሲያልፍና ሲያገድም

መከራ ይህን ቤት ግይረግጠው አያልፍም።

150. እሬሳ አይጫንም በበቅሎ በፈረስ

ሰው ይሄዳል እንጅ ከመውደቂያው ድረስ።

151. መቼ ነው የኔ ቀን ይላል ያዳምልጅ

ይህንን እያዩ መረዳት ነው እንጅ።

152. ብስል ያልቅሳል እንጅ በጣም ተጠንቅቆ

ሞኝማ ሞኝ አይደል ምንስ ጉዳት አውቆ።

153. እያንጎራጎርኩኝ ቃሌን እያበጃጀሁ

እንኳን ዘመዳችን ወዳጃችን ፈጀሁ።

154. በቅበላ ሺህር በትንሳይ መከት

በብሎት በቅቤ በያም በዘይት

የሚበላበት የሚጠጣበት

ፈረስ ይሉኛል የንእውነቱ ቤት።

155. አባቴ ብቻ በል ከፈለስሉ ድረስ
የከፋኝን ሁሉ ንገሬህ ልመለስ፡፡

156. እንጀቴን እንጀቴን ሲበላው አደረ
አባት የሌለው ልጅ እያንጐራጐረ፡፡

157. ማነው የከፈነው እማቴን ላኩልን
ልጆቹ ተጉላላን ጉርሻ ቀርቶብን፡፡

158. አባቴስ ሞተብኝ ልፍተል መቀነት
ሞሰና ጠቢቃ የምገባበት፡፡

159. ቢያለቅስ ቢተከን ምንም ቢከፋው
ልጅ አድማጭ የለውም አባት ከሌለው
አባት ያለውማ ነገሩን ከተተው
በስተኋላው ሆኖ እያመለከተው፡፡

160. ከጉረቤት ኃብታም የአባት ደሃ ይሻላል
የሚሰጠው ቢያጣ ሲመከር ያመሻል፡፡

161. አባት የሌለው ሰው ንብ የሌለው ቀፎ
ዘላለም ይኖራል ውቃቢው ተገፎ፡፡

162. እንኳን ወዬ ማለት እላውቅም መናገር
ቢጨንቀኝ ነው እጅ የአባትዬ ነገር
የልጆቹ አባት ነኝ እያለ ቢናገር
እስሩት ገነዙት አስገቡት መቃብር፡፡

163. አይቀርም ሞትማ መኖም ያለም ልጅ
የልፋቴን ዋጋ ሳያየው ሄደ እንጂ፡፡

164. የዛሬው በጋ እልፎ ለሚመጣው በጋ
ልጆችህ በሰው ቤት ሚስትህ በሰው አልጋ፡፡

165. ታላላቁ ሞት ያገር ከለላው

ሲቸገር የሚሰጥ ሲርብ የሚያበላው፡፡

166. ሲደዙት ቀላል ነው አባትና ብር

ሲጠፋ ነው እንጅ የሚቀረቁር፡፡

167. ልጆች ይንሚሚሉ ዋርካው ወድቆባቸው

ከእንግዲህ አፍርቶ ይበላ መስሏቸው፡፡

168. ተውት አትቅበሩት እንጉቱ በላይ

ሲወጡ ሲገቡ ልጆቹን እንዲያይ፡፡

169. ድሃ ሰው ነበር የተጠነቀቀ

አዳጠው መሰለኝ ግምኛ ወደቀ፡፡

170. ጊዜ ነው እያሉ አስመሸተውብኝ

በእናቴም በአባቴም ሰው ከታች ሆነብኝ፡፡

171 ያባትን እርጌ ያኖራል በጉታ

ቁንጥር እያረጉ ለችግሩ ለታ፡፡

172. አዝመራው ይወጣል በጠፋ በእሙቱ

አባት አይገኝም ከበላው መሬቱ፡፡

173. ባይበላ ባይጠጣ ባይገባ ከቤት

ከደጃፍ ሲቀመጥ ደስ ይላል አባት፡፡

174. አባት ከአለው ጋራ አልነራበትም

ሲወጣ ሲገባ በስስት አልሞትም፡፡

175. አባት እንደሞባ እየቀበራችሁ

ኋላ መመለሻው እንዳይቸግራችሁ፡፡

176. እንኳን ባጋም እጅህ ዝንት በቆርቆሮ

እያንነራገርኩኝ አልፋለሁ በጓሮ፡፡

177. አባትስ ባልሞተ አልጋው ላይ መንምኖ

ይመርቅ ነበር ውለህ ግባ ብሎ።

178. አረገ አባት ያለው በጣም ዕድለኛ

በረቱ አይከፈት እንቅልፉን ቢተኛ።

179. ማለዳ ማለዳ አባት ካለመረቀው

ማልዶ የሚነሳው ውቃቢ እንደራቀው።

180. አረገ የሌለው ሰው መሬቱ ከማድ

የሚያዝንለት የለም ሲወጣ መንገድ።

181. አርጌ ያለው አባት ግንድ የለው ምድጃ

እኔስ አይሞቀኝም የእናንተውን እንጃ።

182. ተበዳሪው መጥቶ ቆሟል ከደጅህ

አንተ ሰጠው እንጅ በለመደ እጅህ።

183. ቸንጫውም አለልኝ፣ መከቱም አለልኝ፣ ጠላውም አለልኝ

እኔን የጨነቀኝ የሚባርክልኝ።

184. ሰማይ ሙሉ ኮከብ ማን ቆጥሮ ይደርሳል

አባት የረገመው ዘላለም ያለቅሳል።

185. ወንድምን ለጥቃት አባትን ለምክር ከሰጠኸኝማ

እንኳን ላንቀራቀር ድምጼም ባልተሰማ።

186. ጥሩ ጠላ ጠምቆ ጥሩ እንጀራ ጋግሮ አባት ካልመረቀው

ሞሰቡ ይነሳል ውቃቢ እንደራቀው።

187. እንጀራ ይበላል ገበሬ ካረሰ

ልብስም ይለበሳል ንጉስ ከነገሰ

አባት የት ይገኛል አፈር ከለበሰ።

188. አይገኝም እንጅ ቢገኝማ እንደ ታ

ጠላን አዘንብለው ከአባት ጋር ጨዋታ፡፡

189. ይልማናና ደንሳ፣ ጎጃም በጊምድር

አሁን የት ይገኛል አባት የሚያበድር፡፡

190. አባት መርፌ ነበር ያውም ከነክሩ

ይሸፍነው ነበረ ሁሉን እንደ ግብሩ፡፡

191. እንኳን በስላሳ ቢጠመድ በሙቶ

አባት የሚያበቅል ምን መሬት ተገኝቶ፡፡

192. አባትና ሥራ አንድ ነው ሁለቱ

ሥራ ትወጣለች ሲነጋ ሌሊቱ

አባት አይገኝም ከበላው መሬቱ፡፡

193. ይታሰራል እንጅ ከንድን አበርትቶ

ተወሶ የሚያስፈታ ምን አባት ተገኝቶ፡፡

194. ያን ያበላኸኝን

ያን ያጠጣኸኝን

አለ ይዤዋለሁ

በራሴ አዘንብዬ

በእደኔ እቀዳዋለሁ፡፡

195. ስትሞት እሞትለሁ እያልከኝ ጠጥቼ

ስትሞት እሞታለሁ እያልከኝ በልቼ

ወየሁ አይላብ መሆን ቀረሁ ተጉልቼ፡፡

196. ከመሻል ነበር ከዳር ሆን ቤቴ

ዘላን ዘላን አልቆ ጉረቤቴ፡፡

197. እንጀራውን ለባዕድ ለምን አበላኸው
ጠላውንም ለባድ ለምን አጠጣኸው
መከራው ለዘመድ ሲሆን እያየኸው።

198. ድሃም ብቻ አይደለም አገሩ ተጉዳ
ይቀበል ነበር ከበድ ያለ እንግዳ።

199. ጠጁንም ጠጥቼ ሥጋውን በልቼ
ልገምገመው እንዴ ከመሃል ገብቼ።

200. ከነ ጉኔ መንደር ጠጅ እንጠጣ ነበር
ሥጋ እንበላ ነበር እየተከተፈ
እንዴት ያለው ጊዜ ሳናውቀው አለፈ።

201 ወዲያ ማዶ ገደል ወዲህ ማዶ ገደል
ከመሃል ቀን ጠፋ
እንኳን ብሉ ጠጡ ግቡ የሚል ጠፋ።

202. እንግዲህ ልጆቼን እንግዲህ ዘመዴን
እግዚአብሔር ያጥናችሁ
ታንኳው ተገልብጦ ማዕበሉ በላችሁ።

203. እንግዲህ አገሬ ደኅናሁን ብላ
እንግዲህ መጌ ማኽላሁን ብላ
እየሞተ አለቀ ንጉ እምራቼ ሁላ።

204 እንኳን ልጆችሁን ካራውን ጨንቀው
በዚያ መከት ሥጋ የሚጨንቀው።

205. ዋንጫችሁ ተገኘ ከገመየው ጉያ
ከቶ የት ደረሰ የቅቤው ገበታ።

206. ጉንቢን ተራራ የሚመስለው ምርቱ

የድሃው ጉሮሮ ቀረ መሠረቱ፡፡

207. የማድጋው ይቆይ የጋን ይጠጣ

አባ ባህር ለጌ መቼም አይቆጣ፡፡

208. በትቢው ተበሉቶ ማማጊያው በውተት

አሁን የት ይገኛል እንዳንተ ያለ አባት፡፡

209. የበላሁት ሲጋ የበላሁት ቅቅል

ለቢን ከፋፈለው እየቅል እየቅል፡፡

210. ጋቢታም ደስ ይለኛል ሲረግጠሙ መሬቱን

የማይሞት በሆን የማይለቀው ቤቱን፡፡

211. እህል ተበዳሪው ቆሟል ከደጅህ

ብር ተበዳሪው ቆሟል ከደጅህ

ተነስ ስጠው እንጅ በለመደ እጅህ፡፡

212. እንኳን አበላኸው እንኳን አጠጣኸው

አሉን ወለም ዘለም

እንዲህ ለሚፈርሰው ለሚቀረው አለም፡፡

213. በማጀቱ ገብተሽ ስትወጭ በወለሉ

ትዝ ትዝ ይለኛል አያያዝሽ ሁሉ፡፡

214. እስከ ዛሬ ድረስስው ይሞት ነበረ

የሞሰቡ እንጀራ ዛሬ ተቀበረ፡፡

215. ሲታበላኝ ብሎ እማኝ አሉ ሰው

እግር ባያደርሰው እጅኸን ባያየው፡፡

216. ኩራ ብየ ባለቅስ ምን ያሳፍረኛል

ካንተ ቤት ያልበላ ያልጠጣን ይገኛል፡፡

217. የኔ እጅሬ ዋንጫ እለን ተሰበረ

የኔ እጅሬ በልጅግ እለን ተሰበረ

የቸገረው ሁሉ ይዋሰው ነበረ።

218. መልካም ጥሩ እንጀራ የተዋናደለ

መልካም ጥሩ ጠላ የዋለ ያደረ

ካንተ ቤት ይበላ ይጠጣ ነበረ።

219. እባት የሌለው ልጅ ደረቀ እንደ ዋንዛ

ቢበላም አይጠግብ ቢጠጣም አይወዛ።

220. ጣልጣል ብዬ ልሂድ ሽንጌው ሳይፈታ

እባት የሌለው ልጅ ተጊገቶም አይረታ።

221. እረኛን አገኘሁ ምን እከል ምን እከል

ከጎደኞችህ ጋር የማይስተካከል።

222. አይንህን ጥርስህን ሰጠው ለቀረ ሰው

እንዳንተ አፈር ለብሶ ለማይበሰብሰው።

223. ውሃ ዋና ገብቶ አይቸው ነበረ

ኧረ እወይ ወንድሜ እወጣ ሲል ቀረ።

224. ወይ ያገሬ ወጣት ወይ ያገሬ ጉበዝ መዘዞመዘዞ

እለቀ እንደሰበዝ ተመዞ ተመዞ።

225. ያ ያልበላው ገኛ ያ ያልጠጣው ገኛ

ትጭት ብሎ ሄደ እንደዘነዘና።

226. ይመስል ነበር ብልጥ የቀርቀሃ መሬ

ሞቶ ተቀበረ በላው ነጭ እሞራ።

227. ጀግና መሄ ታጥቆ መቸ ሆኖ ሞቱ

እግዚያብሔር ይማርህ ሳይል ጉረቤቱ።

228. እህቱ በበቅሎ ወንድሙ በፈረስ፣

ይሽቀዳደማሉ እኔ እደር እኔ እደርስ።

229. የምድር ሳንቃ ሆኖ የሚከፈት ቢሆን፣

አይቻት በመጣሁ ተሸሊት እንደሆን።

230. መከራ ሲመጣ አይነገርም አዋጅ፣

በላይ በላዩ ላይ ይደርባል እንጅ።

231. እንጉራጉራለሁ እየጉደለብኝ፣

የላይኛው ጌታ አምጣና መላልኝ።

232. ኧረ መቼ ታመህ መቼ ሆንክ እሬሳ፣

እግዚአብሔር ይማርህ አላልንህም እሳ።

233. አታልቅስ ይለኛል የሰው ገላጋይ፣

የእሱ ወገን ለኔ ይሆነኛል ወይ።

234. የኔ ያ ላሞች ጌታ የኔ ያ በጎች ጌታ፣

እንዴት ሸርተት ሸርተት ከአፈር ላይ ምኝታ።

235. ኧረ ጉድ ነው እንጅ ሌላ ምን ይላል ሰው፣

የላይኛው ጌታ ፊቱን ካለመለሰው።

የሰው አገር አፈር በእንጨት የታመሰው፣

እንኳን ሰውነቱን አጥሩን አለበሰው።

236. መልካም ተለቀሰ እንግዲህ ይበቃል፣

የገደን አጥንት የለውም ወሀ ሁኖ ያልቃል።

237. የዚያን የሚጂ ላሞች በመድህን ሸጧቸው፣

ሊጅም አልደረሰ ማለዶ የሚያልባቸው።

238. አየ ጉድ ያወጣት የወፎቹ እባት፣

እንድ ተልባ እበባ የቀረ በቢጧት።

239. የዚያን ወጣት ጋኛች አባይና ጣና የታወቁ ናቸው፣

ከባሬው ደረሱ እሱ ቢጠፋቸው።

240. በስምንተኛው ሺህ አዘኑ በጠና፣

ነፋስ አስኘቶ ሊፈጀን ነውና።

241. እኔስ ከሰውየው ቦታ አሳዘነኝ፣

የአግግ መኖሪያ ሊሆን ነው መሰለኝ።

242. ፀሐይም ጠለቀች ጨረቃን ተኪታ፣

አሁን ምን ይሆናል ያለጀግና ቦታ።

243. ተቀበረ ቢሉኝ መች መሰለኝ እውነት፣

አይቀሬ መሆኑን ዛሬ ተረዳት።

244. መልኩም ተለቀሰ እሱም ተቀበረ፣

የዚያ ወጣት ወገን መብላት መጠጣቱ መጫወቱ ቀረ።

245. ከምር ከማሪና አግዜር አንድ ናቸው፣

መለሰው ሊያፈርሰት እየ ለፋታቸው።

እነሱ እየሄዱ እየሸኘናቸው፣

እንዴት ይትዘቡን የቀረን መሰሏቸው።

246. ማኛት ከዚያ ማዶ ገሬምጣ የምትቀጪው፣

የቆንጆ አንገት እለ እንዳትረግጪው።

247. ዘወር ዘወር ብላ እየችው ተሚይዷን፣

እረሳችውና ባፈር መለወጧን።

248. ለሰው አለቅሳለሁ ለራሴ እስመስየ፣

መቸም የእኔው ዕለት አላገኝም ብዬ።

249. እራሴን ብላጪው እንዴት አማረብኝ፣

ሰው ሆኖ መፈጠር ምነው በቀረብኝ።

250. የመሃን ምን እላት ያለ መቀነቷ፣

ቀባሪው ሲመለስ ይወረሳል ቤቷ፡፡

251. ይህንን እግሬን ብዞረው ብዞረው፣

ድንጋይ ብቻ ቀረ የማይናገረው፡፡

አታልቅሽ ይለኛል ያልተበላ ሰው፣

እንጀቴ አይደለም ወይ የተበጠሰው፡፡

252. ያ የማነው ስራ ታጥቦ የሰጣው፣

የእቶ እገሌ ይሆናል ባለቤቱን ያጣው፡፡

253. ደሀና ጉብዝና የነመን ዘር ፍሬ ሁለቱ አንድ ናቸው፣

ዘራቸው አይጠፋም ከሚዘራው ከቦታቸው፡፡

254. ኧረ እነዚህ ቁሶች ምንሰው ያሞኛሉ፣

ገተም አርገው አስረው ፋታነው ይላሉ፡፡

255. እኛ ወድናንተ ምን ቢሆን እንቀርም፣

እናንተ ወደኛ አትጠረጥሩም፡፡

256. ማለበላ ማልጠጣ ብሎ ከማለት፣

ዘም ብሎ ማልቀስ ነው ያገር ሰው ሲሞት፡፡

257. እናልቅሰው እንጆ በተራ በተራ፣

ቢጉዳ አይደለም ወይ ማልዶ የተጠራ፡፡

258. አገሬን ስማዳን ነፋስ ወዘወዘው፣

ለካ እጆሬ ኛዶል ገደቦ የያዘው፡፡

259. አገሬ ስማዳ ሴቱም አልፈተለ ወንድም አላረሰ፣

እሬግ በሞፎር እያመላለሰ፡፡

260. ከማ መነመነ ቀጠነ እንደ ሰበዝ፣

ጭንቅላት ለይቶ የሚመታው ጉበዝ፡፡

261. ደህና ጉብዝ ሲሞት ይሰቃል ሞኝ ሰው፣

አገሬ ሲወረር ደንበሩን ሲያፈርሰው።

262. ከቤት እቃሽ ሁሉ ገበታሽ ይድረሰኝ፣

እየፈተፈተ እንዳንቺ እንዲያጉርሰኝ።

263. አንቺ የኔ ፈትፋች እኔ ጉርስ ጉርስ፣

ወዴት ትሄጃለሽ ወንፈሉን ሳልመልስ።

264. የእደዋ እገሌን ቤት እሞራ አፈረሰው፣

አይከለከልም ወይ አብሮ የበላ ሰው።

265. ምን ያለው ሃገር ነው ከኛ ከኛ ሀገር የባሰው፣

ሕመሙን ስንሰማ ጥሬው የደረሰው።

266. እንኳቀስ እንጂ የባሰው ለባሰው፣

ያልባሰው ሰውማ ማቄም አያደርሰው።

267. አንተ ባለ ሽንጥ ሥጋ ወይድልኝ ከፊቴ፣

ባዷ ሞቀባታል ላላቅላት ለእሁቴ።

268. እናንተ ቅበሩ እኛም እንቀብራለን፣

ቀን የወጣ ለታ እናስለቅሳለን።

269. የዚያ ጀግና ልጆች እራስ ስራስ ናቸው፣

ግለዳ ግለዳ ሆኗል መንገዳቸው።

270. ወትሮ ነበር እንጅ ሰው አልሆንም ማለት፣

እዳምና ሄዋን የተፈጠሩለት።

271. ነጭ ልብስ ለብሳ ቢመስሉት ጨረቃ፣

እወይ የኛ ነገር ተመልሶ ጭቃ።

272. አባት ያልሞተበት እናት ያልሞተበት ቤቱ ያልፈረሰ፣

ከትንድብ ደርሳ እንባው ተመለሰ።

273. ዘንድሮ እቶ እከሌ አገመራው ስንዴ ነው፣
ዘመድ የመጣው እርሞ ሊሄድ ነው፡፡

274. ኧረ ለዚህ ነወይ ልጅ መወለድ፣
ከበዶ በድግ ጥሎ ለመሄድ፡፡

275. ጆ የሰኔው አራሽ የሃምሌው ጉልጋይ፣
እህሉን ሳትሸከፍ መሄድህ ነወይ፡፡

276. አፈር አበድሩት በቁና ሰፍራችሁ፣
አገሩ ሲገባ ይመልስላችሁ፡፡

277. እምዓክ በአንድ ነገር አይጠረጠርም፣
የከፋው ሰው ሞቶ ደስ ያለው አይቀርም፡፡

278. እስቲ ዋየ ልበል ይህን ሙያ ቢስ፣
የታመመ አይድን የሞተ አይመለስ፡፡

279. መሬት ተረገጥኩኝ መልሽ መልሽ፣
እታረቅሻለሁ መሉ እከሌን ከሽ፡፡

280. ማለዳ ሲጠሩኝ ሊያባብሉኝ ነው ብየ፣
ለካ ለዚህ ነው ወይ ለወየ ለወየ፡፡

281. እናቴ አፈር ሆና ካይኔ ገብታብኝ፣
እያደር እያደር ቁረቆረችኝ፣

282. ምስተ እጅህን ታጠብ ተነስ እራት ብላ፣
የታጠበ ስንዴ የመሰለ ገላ፡፡

283. ታዲያ እንዲህ ልንፈርስ ባይፈጥረን ምን ነበር፣
የኛ ይነውን ማኖውቅ ሊልክብን ነገር፡፡

284. እየ ጉድ እየ ጉድ የዚህ ዓለም ነገር፣
ትንሽ ማይኖርበት ወዶ አፈር መቶየር፡፡

285. በሬው ድንበር አይግጥ አፈር ሰው አይነካ፣

ኧረግ አቶ እከሌ ውሃህ ነው ለካ፡፡

286. የመሐሉ ሲያለቅስ የዳሩ ይስቃል፣

መከራ ከቶ ነው ለሁሉም ይደርሳል፡፡

287. በዚያ ቁጥር ዋንጫ ምነው ባልጣጣሁኝ፣

እየገነፈለ በዓይኔ ወረደብኝ፡፡

288. የሚያጉረመርመው እንደ እራስ ነብር፣

ወርዶ የሚጋረደው ከሜካው ከዱር፣

አየ ጉድ አጅሬ በላው ወይ አፈር፡፡

289. እንኳን ደህና ጉበዝ አውራጃ ወረዳ መሥሪያ ቤት የሚያጨው፣

ያማዝናል ጉመን በረቦ የቀጨው፡፡

290. እናት  የሌለው ልጅ ቀላል እንደ ጊሾ፣

ባይበላም በላ ነው ቢናገርም ዋሾ፡፡

291. አላቅሰኝ ወገኔ የባሰው ከባሰው፣

ያልባሰውማ ሰው ወጉም አያድርሰው፡፡

ጆሉ ሰው ሞኝ  ሰው ይጠላል ከመንጋው፣

በመከራው ሌሊት አብሮ ከሚያወጋው፡፡

292. እግዜር በገደለህ እንደእባት አደሩ፣

ገደል ባየ ቁጥር ከማንጉራጉሩ፡፡

293. ለትሱማ ምን ገዶ ከእንጀት ካለቀሱ፣

የሞተውን ወገን እየቀሰቀሱ፡፡

294. ምነው መቀነትሽን ከደጃፍ ጥለሻል፣

ቶሚ ልበኛነው ይታጠቀብሻል፡፡

295. የጌውስ ዘመዶች ሂዱ በከትቻ፣

ደግሞ በቤት በኩል አለ ወይ ዘመቻ፡፡

296. ምነው በቆዬልን ካባ እንደለበሱ፣

ምነው በቆየልን ጋቢ እንደለበሱ፡፡

ያገሬንበ መኳንት ፈጀቸው ቀሚሱ፡፡

297. መከት አይበቃንም ፍሬዳ እረዱ፣

በሌቶ እንዲሄድ ነው ቤተዘመዱ፡፡

298. የጠሳው ገንቦ በዚያው ወረደ፣

እንደመቤቱ እየተጋደደ፡፡

299. ለዛ ቀሬው እያስገደደ፣

ከመቃብር ሞት ይዞ እየሄደ፡፡

300. እኔስ ከሰውየው ቦታው አሳዘነኝ፣

የእህያ መቆያ ሊሆን ነው መሠለኝ፡፡

301. ኧረ ያሳዝናል በጣም ያሳዝናል፣

ሰውየው ከሞተ ቦታው ምን ይሆናል፡፡

302. የአንበሳውን ቦታ አሻገሬ ባየው፣

ድንጋይ ብቻ ቀርቷል የማይናገረው፡፡

303. ምን ያለ ጉብዝ ነው መንገድ ያሳወቀ፣

ገና ሲንጠለጠል ሲወጣ ወደቀ፡፡

304. ዋ ያለው ማነው ዋ ያለው ማነው፣

እናቱን አባቱን፣ ወንድሙን እህቱን የተጐዳው ነው፡፡

305. አትቅበሩኝ አለ ከአንገቱ በላይ፣

ልጆቼን ከብቶቼን አሻገሬ እንዳይ፡፡

306. አሁን ምን ይሆናል ገበያ ቢበዛ፣

አባት አይሸመት እናት አትገዛ፡፡

307. ከቤተስኪያን ጓሮ አንድ ጥጥ በቅላለች፣

ለልብስ አትሰቤ እመራለሁ አለች፡፡

308. ሲሞሽረ ብናይ በከ በኛሽ፣

አይመስለም ነበረ ገላችን ፈራሽ፡፡

309. እኛ የምናውቀው መሣት መጫወት፣

ሥጋ እየቆረጡ ጠጅ መጠጣት፡፡

310. የእጅሬማ እሬሳ በጉድጓድ ሞላ፣

የእናቱን የአባቱን አንጀት እየበላ፡፡

311. ጀግና ሰው ነበረ ጉበዝ ሰው ነበረ፣

አቀብራለሁ ብሎ እሱ ተቀበረ፡፡

312. ያ መልካሙ ጥርስ መሣቅ የለመደው፣

ያ መልካሙ እጁ መስጠት የለመደው፣

ያ መልካሙ ዓይኗ ማየት የለመደው፣

ያ መልካሙ ጉኗ አልጋ የለመደው፣

ካፈቀ ገበና አፈር መደመደው፡፡

313. የእናጅሬም እናት ከእንግዲህ አላቅሺ፣

የንበዝም እናት ከእንግዲህ አልቅሱ፣

ተመልሶ አይመጣም ያ ጀግናው ልጅሽ፡፡

314. በጠፍጣፋ ድንጋይ ከተዘጋ በሩ፣

ጀግናው አይገኝም እንደወፍ ቢዝሩ፡፡

አንድ የወለደው ሁለት የወለደ፣

አላነደገውም እየጣለው ሄደ፡፡

እናት እውድማናማት የተለቀለቀ፣
ብትሰጠው ብትሰጠው አትልም አለቀ፡፡

315. እናት ካለው ጋራ ብትጐራበቱ፣
አባት ካለው ጋራ ብትጐራበቱ፣
ሲወጡ ሲገቡ ይገኛል ስስቱ፡፡

316. አስረዋት ነው መሰል በቱቻ ገመድ፣
መች ትቀር ነበረ በእርያ ሰው መውደድ፡፡

317. አደባባይ ውየ የሚዋሰኝ ባጣ፣
ምድር ምድር አየሁ ቆፍሬ ላወጣ፡፡

318. ክፉ ሰው አይሞትም ተተክሎ እንደዋንዛ፣
ብሩክ ሰው አይቆይም ሠላምታ እያበዛ፡፡

319. እንማከን ባለሱሪ ባለጋሻ ወንድም፣
ለሌት አንድ እንጀራ ቢጠፋበት አትወድም፡፡

320. የሞሰብ እንጀራ ዝንብ እየወረረው፣
ምንን ይበላዋል አይ እናት የሌለው፡፡

321. በላይኛው ሀገር ስትመረመሪ፣
ሳላስበው መጣሁ ብለሽ ተናገሪ፡፡

322. ስፍራ ይዘሽ ቆይኝ የተደላደለ፣
እኔንም አይተወኝ አንችን የገደለ፡፡

323. አይ ሞት አጆሬ ጉች በየደጆ፣
አንድ ቀን ቤት ሠርተህ አትገኝም እንጆ፡፡

324. የዘንድሮው ወራት የሳት የገለባ፣
የታመመው አይድን የወጣው አይገባ፡፡

325. ኧረ እኛና ምድር ታሪክን በመላ፣

ዞሮ እኛ የበላን ኋላ እርሱ ሊትበላ።

326. የሰማይ እሞራ ወረደሽ ተናገሪ፣

እናት የሌለው ሰው የለውም መካሪ።

327. ለቀንጻላሽ ስሬት ሰሪ ስንስማማ፣

ተቆረጥሽው እሉ ዛሬማ ስንሰማ።

328. ፈረስ ምን ያደርጋል የመጋዣ ልጅ፣

ሰው በቅሎ ሲጠፋ ያዛናል እንጅ።

329. ዘወር ብዬ ባየው ወደስተኋላየ፣

አፈር መስሎ ታየኝ የገዛ ገላየ።

330. ሞት እጅሬ ነወይ ከእሊጋ የወደቀው፣

ስንቅ የያዘ የለም መንገዱን ያወቀው።

331. ያንቺ ቤት ወዲት ነው የኔ ነፋስ መውጫ፣

ከመመላለሻው ከመከራው መምጫ።

332. እስቲ ዝግ እስቲ ዝግ ምን ያስቸኩልሃል፣

እንዳየሽብህም ማልደህ ተንስተሃል።

333. ማዘን ለሞተ ሰው ማልቀስ ለሞተ ሰው፣

እስከወዲያው ድረስ ለማይመለሰው።

334. ለይለቀስ ነውይ ወትሮ ለበላ ሰው፣

ላይለቀስ ነወይ ወትሮ ለማማ ሰው

እጁ ወንፈት ሆኖ ሰጥቶ ለጨረሰው።

እስኪ ልሂድና ሞስብሽን ልዳሰው፣

ላይጋርር እይሄድም ልጅ የወለደሰው።

335. ይብላኝ ለሞተ ሰው ልጅስ ያጋል በጁ፣

እንደ አሮጌ ገሳ ወድቆ በየደጁ፡፡

336. ሞትን ፈልጉት ከሰፈር ገብታችሁ፣

የእንዱን ደጅ ሲዘጋ ታገኙታላችሁ፡፡

337. ሀገራችን እስቲ ሀገራችን ቆማ  እንጻቤት በሙሉ ጉዳ ሆኖአለ ላሙ፣

ወደየት ደረስ ያቀንጻመ ቀንጻሙ፡፡

## II. የቆከራ ግጥሞች

338. ወረዳ መኮንን ምን ይቆጭሃል

እግዜር ነው እንጅ ሰውን ደፍሮሃል፡፡

339. አተኳኩሱ ደሞ አለው ጣጣ

ምሽግ ተራምዶ የሚያቀናጣ፡፡

340. የማታ ሥራ ይመስላል ገላው

አምበሳው ወረዳን አፈሩ በላው፡፡

341. ወረደ መኮንን ገዳይ ተከዜ

አለም ቀሪ ኖት ለባለ ጊዜ፡፡

342. ወርዳ መላቱ

ከረምት ከበጋ አይድልም ቤቱ፡፡

343. እፎከራለሁ ዛሬ እንደልቤ

ጀግና ጀግናነውን ከዚህ ደርቤ፡፡

344. ወረዳ መኮንን እንደ ባላባር ወድቀህ ተነሳ

እንደ ተራ ሰው እንዳትረሳ፡፡

345. ወረደ መኮንን የኛ ወረዳ የኛ ምክትል ምን ገደለው

እግዜር ነው እንጅ ሰው አልገደለው፡፡

346. እረ አገሬ መልዛ እረ አገሬ እብናት መናመቀጠዋ

ታሚል አሉ አገሬ እንጃ የነካውን

ይፈልጋል አውሬ የማያገኘውን፡፡

347\. እረ አገሬ ጎንደር የታጠረው በእጋም
ጠላቱን ነው እንጂ መንግስትን አይወጋም፡፡

348\. አሻዝም በሉ እንደማመጥ አታውሩ ወሬ
አሊጋው አይጠናም ያለ ገበሬ፡፡

349\. እረ አገሬ ፋርጣ፣ እረ አገሬ ጋይንት፣ አገሬ ሃሙስ ወንዝ
ባንድ ጭንጫ ጠማ ባንድ ጭሰብ ብላ
እምላክ የሚወደው ይህንን ነውና፡፡

350\. 'ቸ' ይላል አቸራ
ወረደ ገሎ እሱ ሊበላ፡፡

351\. ገዳይ ጉለየ ገዳይ በለሳ
ሳት ሳት ይለቸል ጠቡ ሲነሳ፡፡

352\. እስቲ ለገዴ ንገሩለት
ለነ ሻለቃ ንገሩለት
እነሱ ናቸው የወረዱን ስሬ የሚያውቁለት፡፡

353\. ወረዱ የተጀነነው
የጎንደሬው ልጅ ማንም የሚያውቀው
ኩታ ተጋቢ ለብሶ የሚኖረው፡፡

354\. ከመንደር ሆኖ ከማጀ ሂጠዋ
ወረዶ መቅመስነው የወርዱን ወተ፡፡

355\. ምሽግ አልፎ ምሽግ ተራምዱ
አቆላለፈው የሬሳ ነዶ፡፡

356\. ወረደ መኮንን ብለው ያሉቱ
የተስማማነው ስሙ ከአባቱ
የጀግና ዘር ነው በእናት በአባቱ
ድባውን ሳያውልቅ ገና ከእንገቱ
በማለዳው ዘማች በልጅነቱ፡፡

357\. ገዳይ በኢምሮርቲ በሁለት ጀር
ገሎ ይመጣል ጋራውን ዞሮ፡፡

358. ወረደ መኮንን ጥሩው ወታደር
ጥሩው ወታደር እንደ ሰም ውሃ
ተፍንከንከ ጌታው ቢሰማ
ባንዲራው ሲቆም አሊጋው ሲስማማ፡፡
359. የአቢዎቱ ታማኝ የመልዛው ግማሽ
ከግለ የማይከዳ ተኩሶ የማይሸሽ፡፡
360. ፈረንጅ ሲመጣ ሱማል ሲመጣ
እስኪ ሰው ምረጡ እንደ ወረዴ ያለ ተታልሞ ሚመጣ
ያመናጢ ጠላት ተመልሶ እንዳይመጣ፡፡
361. እንሂድና ይለይለት
በቆራጥነት በሃይማኖት
ኢትዮጵያ አገሬን ደስ ይበላት፡፡
362. አይፈታማተብ አይወለት ሱሪያችን
ቸሩ መደሀኒያለም ሳለ ፈጣሪያችን
እንሰየፋለን ለእናት አገራችን
እንደ እናት እንደ አባት እንደሚሰታችን
ማር ቅቤ እኮ ናት ይህች አገራችን፡፡ (አልወረደ መኮንን)፡፡
363. ይህችን አራችን ይህችን ሃይማኖት
የውጭ አረመኔ እንዳይለውጣት
አትዘን አገሬ አትፍራ ለሞት
ምን ወረዳ አውራጃ ቢኩን ነገስታት
ብቻህን ብትሆንስ መች ያቀራል ሞት፡፡
364. አመሰግንልኝ ወላጅ እናቱን
በምን ቆርጠው ነው የጣሉት እትብቱን፡፡
365. ኛምበል አጥናቶ በለው ያለለት
አኛገር ተኳሽ በጥቆር ብረት፡፡
366. ሲተኩስ ውሎ ጠበቿውን ሲገል
ሃራም አለና ነጠመው ትገል፡፡

367. የእባብ እሬሳ በእጅ አይነሳ
እረተው ጥሊያን ና ጉልበቴን ሳም አለ ወረደ መኮንን፡፡

368. እሮብ ማለዳ ተጋጠማቸው
ሃሙስ ማለዳ ድል አረጋቸው፡፡

369. ገዳይ እርብ
አየር በሰማይ ሲያረበርብ፡፡

370. ገዳይ ቅዳሜ
የጀግና ነበዝ የለውም ዕድሜ፡፡

371. ገዳይ እሁድ
አገር ቆራሹን ያንን አይሁድ፡፡

372. ስሙ ከባድ ነው እንደ እባ ዝንጀር
ሲጠሩት ይሞቃል የትልቅ ሰው ዘር፡፡

373. ጀግና ሲፈጠር የተፈጠረ
ወረደ ነበር እጅሬ ቀረ፡፡

374. እረ ወረደ የጦሩ በሬ
ያገከባለለው ነበር ያን እረሙኔ፡፡

375. ገዳይ ትግሬ ላይ ገዳይ መቀሌ
ማደሪያው ዋሻ እራቱ ጥሬ፡፡

376. ዳገት ለዳገት ይበቅላል እሞጭ
ወይ ስምቶ መቻል ወይ ገሎ መሄድ ከመነሚነሞ፡፡

377. ወርዶ እፍጣጭ እሬጣጭ
የደሀና ነበዝ ነፈሬ ጨባጭ፡፡

378. ወርዶ መኮንን የጭንጫው ቃም
መሞት አይቀርም ሰው ታሞ ታሞ፡፡

379. እር ወረደ እንዴት ላርግህ
አይደለህ ጠፈር እልቀጥልህ
አይደለህ ብረት እላሰራህ
ፈጣሬ እምላኬ አይከለከል ወስዶ ያግባህ
መቺም እበኑ አይገኝብህ

ከነ አብረሃም ጋር ይሁን ኑሮህ።

380. ወረዳ መኮንን በፍቅርትቶ ወደ ጠብ ሲያፍር
እንደ አየር ኃይል ከሰው ጭንቅላት ዘሎ የሚሰፍር።

381. እስኪ ልጅምር ትንሽ ፉከራ
ድሮም ይህው ነው የጀግና ስራ
አጥንቱ ላፈር ስጋው ላሞራ።

382. በለው በለው ሲል ጦር ሲጉመራ
አልፎ ጉዳቢ ከጥላት ጋራ።

383. በለው በለው ሲል መልክም ሲናጋ
ተባውሮ ገዳይ ቆላና ደጋ።

384. ጥላት ሲመጣ እንደ ደንቡ ደርሶ
ጀግናው ቆያቸው ሥላሣ አጉርሶ
ሰላማውንም ቢዘረዝረው
የነዚያን ምሽግ በደም ነከረው።

385. አይ አተኳኩስ አይእደጋገን
እንደወስከምቢያ መንደል ነው ሁሉን

386. መጡ በዚህ ላይ መጡ በዚያ ላይ
የእህል ሰውና የጦር ሰው ተለይ።

387. እኒያም እነዚያም ይጠራቀሙ
ለሁላችንም እንዲያጠቅሙ።

388. ኧረ የቀውጢው እለት እነማን ነበሩ
እንደ ሊብሬ ሲሶህ ምንሽሩ።

389. የበሮቹ ስም ኛራና ቦራ
የማረኛው ስም ሥደህ አትራራ

የጅራፍ ስም ሣይመትር በላ
የገበሬው ስም ሲሣይ ገሞራ፡፡

390. ትንሽ ሽርፋ ይይዛል መቶ
ይትረፈረፋል ጉተራው ሞልቶ
እህያው እምሣ መጫኛው መቶ
ያስገባል በሩት ያገን ጉትቶ፡፡

391. የተበዳሪው ሞስ እንኳን የለው
በልቶ ጠጥቶ ጭኖ መሄድ ነው
ድግሩ ሠፋፊ ግረኛው አዲስ
አጅሬ ወንዱ የአርሻው መሀንዲስ፡፡

392. የሸንብሬ አርሻ የለውም ፈሠስ
የበሬው ጌታ የአርሻው ኢጋሰስ፡፡

393. ብሉ ጠጡ ባይ አሳፊ አግዳሚ
ከመንገዱ ዳር አዳራሽ ሠሪ
ወረዳ አውራጃ ባንድ አግዳሪ
አስራቱን ከፋይ ሀጉን አክባሪ፡፡

394. ጤፉን አጭዶው ዘሩት ዘንጋዳ
ሲኖር አይጠቅምም ቢሞት አይጉዳ፡፡

395. የጀግና ቀለብ ስንዴና ግር
ሲኖር ተገዳ ሲሄድ መሪር፡፡

396. ጀግናው ወታደር ካደረበቱ
ሲጋው ጠንካራ አጥንተ ብርቱ፡፡

397. ጋት ተከፍቶ ሲጠግ ጠጅ
ልቡን የያዛት እውጥቶ በእጅ፡፡

398. መልዛ ላይ ወጥቶ አፈር ቆራጩ

በአጭር ሚኒሽር አቆላማጪ።

399. ተጃ ስደዱ ላም እናገናኝ

አገሬ እንግዲህ ቸር እንገናኝ። አለ ወረደ

400. አየር በሠማይ ጭራት ሲመስል

ተንጋሎ ተኳሽ ከመዲናው ስር።

401. ገና ሲወለድ ራሱን ሲላጭ

ይቅለበለባል እጁ ከምላጭ።

402. ኧረተው አንተ ሰው አትለፍ በደጁ

እንደገለባ እሣት ትጠፋለህ በእጁ።

403. አደዞሽ ሚኒሽሬ አልሠጥሽም ለሰው

የወገቤን ጥይት በደም ማላርሰው።

404. አትውርድ ቢሉት ወረደ በገራ

ነትሮት ቀለ እንደ ባንዲራ

405. ከፍ ከፍ ያለ ከምር ከግሬ

ሰላሳ እንግዳ ቤት አሳዳሪ

ወረዳ አውራጃ ቤት አሳዳሪ።

406. የርሻው መምህር የርሻው ምሁር

እውነቱ ሞቶ አባ ባህር።

407. መልዛ ላይ ሆኖ ይታያል ምርቱ

ወርዶ መኮንን የወቃበቱ።

408. እውነቱ ዘለቀ አንተ የርሻው መሃንዲስ

ያውም ወንር ላይ ከድንቅ አገር

ያመርት ነበር ጥሩ ባቄላ አተር ጭምር።

409. አጻምቱ ወገኔ ስማኝ ዘመዴ
እውነቱ ዘለቀ ያመርት ነበር ጤፍና ስንዴ
ገበሬው ጨካኝ በሬው ወንበዴ፡፡

410. ልጅ ሲሳይ አባተ ደልቃቃው ገበሬ እግዜር የወደደው
ተወልዶ እስከሚሞት ጨማ ያልገደደው፡፡

411. ሰኔ ሲመጣ ገምገም ሲል
ይገኛል ሲሳይ ከነ ኮልባ ስር፡፡

412. ሲሳይ አጅሬ የበሳው ሞፈር
እንኳንስ ውሃ አይፈስም አፈር፡፡

413. በሮቹን መግረፊያ አያስነካቸው
እንዴት አርጐ ነው ያጠገባቸው፡፡

414. ተጋቡ ገበሬ እምራቹ ገበሬ
ካማይ በዛብህ ተለየን ዛሬ፡፡

415. ወረዳ እውራጂ ባንድ አሳዳሪ
ወረዳ እውራጂ ተው አታሳድር
ወረዳ እውራጂ ምነው ባሳድር
የእውነቱ ሚስት ነጭ ከተቁር ስለምትጋግር፡፡

416. በእህል ተይቶ በእህል ረሳስ
እንጀራው የጤፍ ጠላው የገብስ
ያበላው ያጠጣው ነበር ጋይንት ድረስ፡፡

417. ደህና ዋላችሁ ደህና አደራችሁ
እንዴት ያለ ወንድም ተለየባችሁ
እንዴት ያለ አባት ተለየባችሁ
እነስ ልሄድ ነው አላቅኛችሁ እንግዲህ ወዲያ ምን ላድርጋችሁ
እግዜር አይደለው አልሰራላችሁ፡፡

እንግዲህ ወዲያ ምን እናረገው
እሬ እቶ እውነቱን እፈርበሳው
እግዜር አይደለን እናስቀረው
እንኳን ዘመዱ ባዱ ያለቅሰው፡፡
ፍታት አብቶቶ ደርሷል ጉድጓዱ
እግዜር ያጥናችሁ ቤተ ዘመዱ
መለየት አይቀርም ምን ቢዋደዱ፡፡
418. እስቲ እንፎክር በጦር ሙያችን
እንዳትደፈር ውድ ሀገራችን፡፡
419. ታጠቅ ተሠለፍ የኢትዮጵያ ጀግና ምራን መንገድ
በጣሊያን ጊዜ ስላለህ ልምድ፡፡
420. ወጀግራ የሚነርስ አንድ ጥይት
እንዴት ይበላሻል በዚያ ጠላት
ያዝለከልካል እንጀት ጉበት፡፡
በደም በፀሎት በሃይማኖት
ፈረንጅ ቢሸከም ብዙ መትረየስ ብዙ ጥይት፡፡
ናስማስር ይዘው ሲማርኩት
በወንጭፍ ድንጋይ ሚያባርሩት
ዙሪያ መንገዱ መውጫው ጠፍቶት
ጀብድ የሠፈነበት በጀግንነት
በሃገር ታሪክ ተጽፎበት
ጎራዴያቸው እለ ከቤት
ያንን ነጭ ፈረንጅ የቀለበት፡፡
421. እሬ ጦር መጣ ማን ይሂድ ከቶ
አርበኛው ሁሉ አለቀ ሞቶ፡፡
422. አይወጣውልም ጀግናው ልኮህ
ለእናት ሀገርህ ለድንበርህ
ለወለድካቸው ለልጆችህ፡፡

የጀግኖች አባት ሚባል ስምህ
በጣም ደስ አላት ባለቤትህ
አትወላውልም ለጠላትህ
በለው ግምባሩን እንጣጥረህ፡፡
423. የጠላት ውሸት እንደሠሙት
አይነፍገው እንደ ወንፊት
ገደል እያለ አንድ ሜይሞት
የኢትዮጵያ ጀግና ፊሪ መስሎት
ግንባር ይመታል ተኩሶ አይስት፡፡
424. የጀግኖች እናት አይዞሽ ደህና ነው
ጠላት ደምስ ጃሌ እያለ ነው
ስሙ በታሪክ ሊጣፍለት ነው፡፡
425. የጀግኖች እናት ትበያለሽ
አንችም ታያለሽ ከቆየ እድሜሽ፡፡
426. ጀግናው አርበኛ ማልዶ ተነሳ
ምሽጉን ሊምስ ጦር ሳይነሳ፡፡

427. ይኸን ጊዜ ነበር አማላጅ ማብዛት
አፈር ሳይሜነው ሳይገባ መሬት፡፡
428. አምስት ሆነው መጡ አንድ ሆና ቆያቸው
አስር ሆነው መጡ አንድ ሆና ቆያቸው
ጀግንዬ በክንዱ አስተናገዳቸው፡፡
429. እባክህ ጌታዬ ጊዜውን መልሰው
የጀግናውን ሊጋግ ጀግናው እንዲያብሰው፡፡
430. የውጋዱ ዘማች ብሎ ቢቀባጥር
የእነ አጅሬ ወንድም ብሎ ቢቀባጥር
አስሩት ገነዙት አስገቡት ከምድር፡፡

431. ዘመቻ መጣ አሉ አዋጅ ተነገረ

ፈሪዎቹ ቀርተው ጀግኑ ተቀበረ።

432. ኧረ ምን ያደርጋል የሴት እህት ብዙ

ጠቅለል ያለ ጀግና አንድ ወንድም ሳይዙ።

433. ጀግና ኀበዝ ሲሞት ይስቃል ጅሉ ሰው

የታጉት ጥጃ የማያስመልሰው።

434. ባቱ ቀጠን ያለ ክንዱ መስር ጎጃ

እኑሬው በነበረ ለጠላቱ መጉጃ።

435. አንተ ባለ ወንድም አታንገራግረኝ

ጉድብ የሚያስለቅቅ የኔም ነበረኝ።

436. ይህን ያህል ጊዜ ግንባር ላይ ቆይቶ

ይህን ያህል አመት ስልጣን ላይ ቆይቶ

ኧረ ሞት አጅሬ ወሰደው ለይቶ።

437. ሰውየው ጀግና ነው ፊቱ የሚቆጣ

አገሩን ደስ አላት ጠላት ገሎ ሲመጣ።

438. ባያወቀው ነው እንጅ እየደነገጠ

ጀግና ወንድሙ ሲሞት ክንዱን ተቆረጠ።

439. ጀግና ጥሩ ነበር ሲንገማነኑበት

ታዲያ ምን ያደርጋል ይህ ሞት አለበት።

440. ጉፈሬና ስራ እንዲሁም ጠመንጃ

በሌላው መች ያምራል ጌታው በአንተ ብቻ።

441. ቁመቱ አጥር ብላ ወርዷል ሰፋ ያለች

ስራ ለአባ ነብሮ ተሰፋታ ነበረች።

442. ጀግናው ኅበዙ የድብ አንበሳ

የሚያስረግጸው ገና ሲነሳ

ገሎ ተራግጅ የነጭ ሬሳ

ሙተህ አትቅር ቶሎ ተነሳ።

443. ባህር ተሻገሮ እንደጉማሬ

ይዋጋ ነበር ጠላት ወራሪ።

444. የደራው ጀግና ያፈር ውሃ ናቱ

ሞቶ ተቀበረ ገባ ከመሬቱ።

445. ገዳይ በናስማር በዱሮው ብረት

ገዳይ በውጅግራ በድሮው ብረት

ነጥሎ ተኳሽ እንደወረቀት

የልጅ አይናፋር የማይፈራ ሞት

አባሮ ገዳይ ጅረት ለጅረት።

446. ተናንቆ ገዳይ ደረት ለደረት

ቀን እየበዛ ይሆናል ተረት።

447. አይ ጀግና አይ ወንዱ

አሁን ሊገባ ነው ከቃላይ ጉድጓዱ።

448. አለው አለው እና ሲያልቅበት ጥይቱ

ሙባ ደረሰለት ነብሮ መድሃኒቱ።

449. የማስፈራራበት ተሰበረ ጦሬ

እንግዲህ ምን ይዥ ልቆም ከሆገሬ።

450. ያጅሬን ጃባ ሽጠው ገበያ አውጥቶ

ስሪው ብቻ ቀረ የሚገጥመው ጠፍቶ።

# አባሪ - 2 ፎቶዎች



ምስል (ሀ)



ምስል (ለ)



ምስል (ሐ)



ምስል (መ)



ምስል (ሠ)



ምስል (ረ)





ምስል (ኘ)

ምስል (ነ)





ምስል (ኘ)

ምስል (አ)

የፎቶ መግለጫዎች

ምስል ሀ፣ለ፣ሐ፣መ፣ሠ፣ረ፣ቀ፣ቸ፣ኘ እና ነ የአቶ ወረደ መኮንን ለቅሶን የሚያሳዩ፣

ምስል መ፣ አቶ ታከለ ጎታቱን የሚያሳይ።

ምስል ፎ፡ አቶ መኮንን ከፍሌን የሚያሳይ።

ምስል ጀ፣ኘ እና አ የአቶ እውነቱ ወልቀን ለቅሶ የሚያሳዩ ናቸው።

# አባሪ - 3 የቃለመጠይቅ ጥያቄዎች

## ሀ. ለታላላቅ አባቶች የቀረቡ

1. ለቅሶ ለምን ይለቀሳል?
2. የለቅሶ ማህበራዊ ፋይዳ ምንድን ነው?
3. በደብረታቦር ከተማና አካባቢው ያለው የለቅሶ ስርዓትና ክዋኔ ምን ይመስላል?
4. የለቅሶን ስርዓት ስርዓት የሚያስብለው ከየት እስከየት ያለውን ነው?
5. ለቅሶውን በባለቤትነት የሚያስተባብረው ማን ነው?
6. ጊዜና ጉልበት ከማባከን አኳያስ?
7. ለቅሶ ሃይማኖታዊ ይዘት አለው ወይ?
8. የወየታና የቆከራ ግጥሞች በምን ይደረደራሉ ያላቸው ጠቀሜታስ ምንድን ነው?
9. የወየታና የቆከራ ግጥሞች ለማን ይገጠማሉ?
10. የለቅሶው ቆይታ የድሮው እና የዛሬው ልዩነት አለው ወይ በአካዋወን ስርዓቱ ላይስ ለውጥ አለ ወይ ምን ተለወጠ?
11. የወየታና ቆከራ ግጥምን የሚገጥሙ ሰዎች እንዴት ያሉ ናቸው ሰውስ ለነሱ ያለው አመለካከት ምን ይመስላል?
12. ግጥሞቹ ለጀግኖች ብቻ የመገጠማቸው ምስጢር ምንድን ነው?

## ለ. ለፎካሪዎች እና ወየባዮች የቀረቡ

1. ለቅሶ ምንድን? ነው እንዴትስ ይገለፃል?
2. የወየታና የቆከራ ግጥሞችን የሚገጥማቸው ማን ነው?

3. እነዚህ የለቅሶ ግጥሞች ተዘጋጅታችሁ ነው ወይስ በድንገት ነው የምትገጥሟቸው?

4. በድንገት ከሆነ እንዴት ፈጥሮ መግጠም ይቻላል?

5. በወየታ፣ ሙሾና ቆከራ ግጥም መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድነው?

6. የሚፎክርባቸው ሰዎች ምን አይነት ናቸው?

7. እናንተ የፎካሪነት ልምድን ከየት አገኛችሁት ?

8. ስትፎክሩ ወይም ወየ ስትሉ የሚሰማችሁ ስሜት ምንድን ነው?

9. የአልቃሹ "እውነት" እያለ መቀበል ለፎካሪዎች ምን ፋይዳ አለው ?

10. የወየታና የቆከራ ግጥሞች እየተፈራረቁ መከወናቸው ምን ጥቅም አለው?

11. ሌሎች ብዙ ፎካሪዎች አሉ ወይ?

12. እናንተም ለልጆቻችሁ ታስተምሯቸዋላችሁ ወይ?

13. አንዳችሁ ከሌላችሁ የችሎታ ልዩነት አለ ወይ?

14. ያለማቋረጥ ለምን ያክል ጊዜ ትፎክራላችሁ?

## ሐ. ለባለሙያዎች የቀረበ

1. ለቅሶ ለምን ይለቀሳል?

2. የደብረታቦር አካባቢን ለቅሶ ከሌላው አካባቢ ለቅሶ በምን ይለያል?

3. ቃል ግጥም በለቅሶ ላይ እንዴት ይገለፃል ምን ምን ናቸው?

4. የለቅሶ ቃል ግጥሞቹን ከመቀረስ እኪያ ምን ታደርጋላችሁ?

5. የለቅሶው ቆይታ ማጠር በስነ ቃል በመፈጠር ላይ ችግር እያመጣም ወይ?

6. ማህበረሰቡ ለለቅሶ ያለው አመለካከት ምን ይመስላል የተሳተፎ ደረጃውስ?

# አባሪ - 4 ካርታዎች




ደብረ ታቦር ከተማ

ፋርጣ ወረዳ

ምንጭ፡- የደቡብ ጎንደር ዞን አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም መምሪያ (10/06/2004 ዓ.ም)




ደብረታቦር ከተማና ቀበሌዎቹ

ምንጭ፡- ከደብረታቦር ከተማ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት (25/05/2004 ዓ.ም)